በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት
በአማርኛ
በየሁለት ወር የሚታተም

ሰኔ/ ሐምሌ ፲፱፻፹፰

፬ኛ ዓመት ቁጥር ፮
$2.75

# ላንዳፍታ




## አትላንታ የ1996 ኦሎምፒክ ከተማ




- አዳምና ሔዋን
  "ዕጣዬ"
- ኑሮ በአሜሪካ
  "እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!"

# LANDAFTA

*An Ethiopian Cultural Bi-monthly Amharic Magazine*
*(Amharic is the official language of Ethiopia)*
June/July 1996
Vol. 4. No.6

"በመስታወት ቤቶች የሚኖር በሌሎች ላይ
የመጀመሪያውን ድንጋይ ወርዋሪ አይሆንም!"
ክፍል 2
ረዳት ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና (ገፅ 24)

# የኢትዮጵያ መንደር





ETHIO VILLAGE

CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

# ኢትዮወርድ EthioWord

## ግዕዝና የዓለም ፊደላት በኢንተርኔት

የኢትዮጵያ ኮምፕዩተሮችና ሶፍትዌር ግዕዝ ከሌሎች የዓለም ፊደላት ጋር ኢንተርኔት ላይ እንዲጻፍ፣ እንዲታተምና እንዲነበብ አዲስ የኢትዮኔት ግኝት አቅርቧል ። በተሟሉና ባልተቀጠሉ እንዲሁም በተቀጠሉና በኅደሎ ፊደላት በቋፐታና በተዘዋዋሪ እርስ በእርስና ከሌሎች ቋንቋዎች ጽሑፎችና የመሳሰሉት ጋር ተያይዘው (Multi-lingual hyperlinked documents) ግዕዙ ለኢንተርኔት እንዲጻፍና እንዲነበብ ፈጥረናል ። ምሳሌ፦ ዐረብኛ/Arabic (جثجرغخثثث) ግሪክ/Greek (Σ'Ωϱ,ϋώεϑ) ሕብራይስጥ/Hebrew (ד׳״ן״ב׳) ጃፓን/Japanese (ムラモトメヤメト三) etc. ከአሁን ወዲያ ግን ግዕዙን በአንድ ዓይነት አጻጻፍና አቀማመጥ ብቻ መጠቀም ስላለብን ግኝታችንን ማንም እንዳይቀዳና አስመስሎ እንዳይሠራ እናስጠነቅቃለን ። <u>ኢትዮወርድን</u>ና <u>ግዕዝኤዲትን</u> ያሏቸው ለኢንተርኔት የሚያስፈልጓቸውን (Upgrade) በ$49.00 ቢያሟሉ ጠቃሚ ነው ። የግዕዙ ጽሑፎች የሚከፈቱት ልክ እንደላቲኑና በሰማያዊ ቀለም የተጻፉትንና የተሰመረባቸውን የግዕዝ ፊደላት ቃላት በመጫን ነው ። Now you can include Ethiopic texts and even hyperlink them with some other world alphabet texts in your Internet documents. This is another new innovation from the pioneers. You are limited only by your knowledge of the different languages and alphabets as you surf the multi-lingual **Ethionet** with the same browser. If you have <u>EthioWord</u> or <u>GeezEdit</u>, we encourage you to upgrade for only $49.00 and start surfing the Internet by just clicking on the Geez hypertext documents. Publishing on the Internet in Ethiopic requires Ethionet and some other products. Ethionet package includes EthioWord, GeezEdit, free software and manuals for $279.00. **See this first Ethiopic Internet text in our web page.** Please call for more information about server software, Internet access, building and hosting Ethiopic home pages. (Warning: Do not copy our methods since we will publish lists of any violators and institutions in different media even before we take legal actions.)

**የኢትዮጵያ ኮምፕዩተሮችና ሶፍትዌር**

**Ethiopian Computers and Software**

**9781 W. Fremont Pl., Littleton, Colorado 80123, USA**


Tel: 303/972-2186, 202/785-1618 and 301/270-3865

Fax: 303/973-4342 or 202/785-1626

E-mail:*Ethiopian@aol.com* – <u>ዶ/ር አበራ ሞላ</u> ፫/፹፰ (3/96)

*http://home.navisoft.com/ethiopian/index.htm*

# ኢትዮኔት



Back to Ethiopian Home Page ወደኋላ ለመመለስ


Copyright (©) 1985-1996 ABSHA/ECS (Dr. Aberra Molla)

# ማ ው ጫ

# CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

4 ሰላምታ ከአገር ቤት (ከወርቃየሁ)

5 ሰላምታ ከባህር ማዶ ከይግለጡ ለወርቃየሁ

8 ደብዳቤ ከባህር ማዶ ከገብርዬ ለወርቃየሁ

13 ከአንባብያን

15 የ1996 ኦሎምፒክ በአትላንታ
ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሚሳተፉበት ውድድሮች ፕሮግራም

ኢትዮጵያውያን የኦሎምፒክ ጀግኖች

"ዌልካም ዮል" (ሰይፉ መኩሪያ)

21 "ግልጽ ደብዳቤ" ከቺካጎ ኅብረት

24 የውይይት መድረክ
"በመስታወት ቤት የሚኖር . ." ክ.2 (መረራ ጉዲና)
"በእንግዳ አከባሪነት ስም . . ." (ሀከሮ)

36 አዳምና ሔዋን
"ዕጣዬ" (አብርኸት)
" የሲንግል ኑዛዜ" (ስፔራንቶ ዲያስፖራ)

40 ኑሮ በአሜሪካ
"እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ" (አትናትዮስ)

42 ከአበው
"ለንግግር ለጥበብ . . ."
(መጋቢ አዕላፍ መክብብ አጥናው)

44 ከዚህም ከዚያም (ከአገር ቤት ጋዜጦች)

46 እኔ የምለው
"የሚያበሳጭ ጠባይ" (ውሂብ ጥሩነህ)




ጀግናው አበበ ቢቂላ



የ1996 ኦሎምፒክ ከተማ አትላንታ



ሽፋን አትላንታ የ1996 ኦሎምፒክ ከተማ


"ላንዳፍታ" የግል መጽሄት ናት። የሚወጡ ጽሁፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሁፎቹን በሬዲዮ፣ በቴሌቪ ዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሃፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የገጠመኝና የፈጠራ ድርሰት ጽሁፎች ሀጋዊ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን እንገልጻለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1996

ላንዳፍታ
ሰኔ/ሐምሌ ፲፱፻፹፰
፬ኛ ዓመት ቁጥር ፭
LANDAFTA
June/July 1996 V. IV- No 5

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ
**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*
**Assistant Editor**
*Genet Wolde*
**Contributors**
*Girma Zegeye*
*Seifu Mekuria*
*Wuhib Tiruneh*
*Gebrie*
**Editorial Advisors**
*Lisanu Simret*
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Shop
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Dallas, TX
Maru Grocery
ET. Beauty Supply
Bati Grocery
L.A., CA
Merkato
Damera
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Diego, CA
Emebet Worku
San Jose, CA
St. Claire news Stand
Seatle, WA
Arat Kilo Grocery
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN - Merkato
Houston
Queen Sheba Rest.
Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Merkato Market
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone (404)508-4657
Fax: (404)508-2447
E-MAIL mgessesse@aol.com

# ከአዘጋጁ

## ድል ለአትሌቶቻችን !!

እንደምን ከረማችሁ። ከ1996 የኦሎምፒክ ከተማ አትላንታ የናፍቆት ሰላምታችን ይድረሳችሁ። ስለኦሎምፒኩ ዝግጅት አንዳንድ ነገር ታስሙናላችሁ ብላችሁ ስትጠብቁ እንደነበረ ተስምቶናል። በፎቶግራፍ የተደገፈ ዝግጅት አለን። ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሚሳተፉባቸውን ውድድሮች ፕሮግራም አውጥተናል። ሰይፉ መኩሪያ ስለአትላንታ ከተማ ዝግጅት ጥሩ ቅንብር አለው። አበበ ቢቂላ፣ ማሞ ወልዴ፣ ምሩፅ ይፍጠርና ደራርቱ ቱሉ አገራቸውን በወርቅ ሽልማት ያሽቆጠቆጡበት በአራት ዓመት አንዴ በሚካሄደው ኦሎምፒክ ... ዘንድሮ ደግሞ እነማን ይሆኑ ብለናል። ወደ አትላንታ ከተማ ለዚሁ ዝግጅት ለምትመጡ ሁሉ እንኳን ደህና መጣችሁ እንላለን። በድል ጣቢያ ደግሞ እንድምንገናኝ ይታወቅ። አትሌቶቻችንን በደስታ ተቀብለን ድል በድል እንዲያጎናፅፉን ምኞታችንን እንገልፃላቸዋለን።

ዘንድሮ በዋሺንግተን ከተማ ስለሚካሄደው የሰሜን አሜሪካ እግር ኳስ ዝግጅት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲሰጡንም ሆነ ስለዝግጅቱ ማብራሪያ እንዲሰጡን የፌዴሬሽኑን ባለስልጣናት በስልክ አነጋግረን በወቅቱ የደረሰን ነገር ስለሌለ ምንም ማውጣት አልቻልንም። በተለያዩ የእንግሊዝኛ መጽሔቶች ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሲሰጡ ለእኛ በአገር ቋንቋ ለምናዘጋጀው አንድ ገፅ ጋዜጣዊ መግለጫ (press Release) ቢልኩልን ጥሩ ነበር። የሆነ ሆኖ ቅሬታችንን ከመግለፅ ወደ ኋላ አንልም። ከየቦታው ለውድድሩ ለሚሄዱት ተጫዋቾችና ተመልካቾች መልካም ጊዜ እንዲሆንላችሁ ምኞታችንን እንገልፃለን።

ረዳት ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና በጦቢያ መጽሔት ያቀረቡትን ጽሁፍ ክፍል አንድ ዝግጅት ባለፈው እትማችን ማውጣታችን ይታወሳል። ክፍል ሁለትን በዚህ እትም ይዘን ቀርበናል። ከአንዳንድ የመጽሔታችን አንባቢዎች ስለ ፅሁፉ አስተያየት የደረሰን ቢሆንም ክፍል ሁለትን (የመጨረሻውን) እስከናወጣ ብለን ለጊዜው አቆይተነዋል። ስለዚህ አስተያየታችሁን በሚቀጥለው እትም ማውጣት እንጀምራለን።

በመስከረም (September 1991) የተጀመረችው ላንዳፍታ ይኸው አምስተኛ ዓመቷን ልታገባድድ ነው። በአምስት ዓመታት የልምድ ክምችቷ ያሳየችውን ዕድገት በተመለከተ አንባብያን አስተያየታቸውን እንዲልኩልን እንጋብዛለን። ከመስከረም 1989 ዓ.ም. ጀምሮ በየወሩ ለመውጣት ዝግጅቷን በማጠናቀቅ ላይ ናት። አስተያየቶቻችሁንና ጽሁፎቻችሁን ላኩልን።

**የላንዳፍታ መጽሄት ዝግጅት ክፍል**
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
Phone: (404) 508-4657
Fax: (404) 508-2447
E-MAIL- mgessesse@aol.com

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic.*
*. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## እንደምን አላችሁ?

ኧረ ለመሆኑ እንደምን ከረማችሁ? ይህ የፈረንጅ አገር ኑሮ ይቀልድባችኋል አሉ። ኑሮና ብልሃቱስ እየገጠመላችሁ ይሆን?

እኛም እንዳለን አለን። "ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል!" ይባል የለ። ችግር፣ ሰቆቃ፣ ፍርሃት፣ ሁሉም እንዳሉ አብረውን አሉ። አሁንስ ተላምደናል። እናንተስ ለመሆኑ እንዴት ናችሁ? አንዳንዴ ሆድ ሲብሰን ትናፍቁናላችሁ። ከዛሬ ነገ የነፃነት፣ የሰላምና የዕድገት ችቦ እያበራችሁ ትመጣላችሁ እያልን ደጅ ደጁን እናያለን። እስካሁን ተስፋ አልቆረጥንም። ሰውዬው ገበሬ ነው አሉ። ጋሻው ነው ስሙ። በጠና የታመመች ሚስቱ አልጋ ላይ ከዋለች ከርማለች፤ ተዳክማለችም። ጠበሉን፣ መድሃኒቱን ሁሉ ሞክሮ ተስፋ ቆርጦ ሞቷን ነው የሚጠብቀው። ያለ የሌለ ሐብቱን ለኋው በሽታ የምትድንለት መስሎት አሟጧል። እንደው ዝም ብዬ አይን አይኗን ከማይ ስትሞት ለምናምኑ እንኳ እንዲሆነኝ በማለት እርሻው ላይ ያለውን እህል ለማበጃጀት በጠዋት ተነስቶ ጎረቤቱን አደራ ብሎ ወደ እርሻው ይሄዳል። ትንሽም አልቆየ እቤቱ አጠገብ ካለው አፋፍ ላይ ሆኖ ሚስቱን የሚጠብቅለት ጎረቤቱ ስሙን ጮክ ብሎ ይጠራዋል።

"ጋሻው! ኧረ ጋሻው!"

በሬዎቹን አቁሞ ወደ ቤቱ አቅጣጫ ይመለከታል።

"ጋሻው! ኧረ ጋሻው!"

"አ...ቤ...ት!" ይላል እሱም ተራውን ጮሆ፤

"ጋሻው ሚስትህ አርፋለችና ቶሎ ና!"

ይለዋል።

"ምናልከኝ!" ይላል ሁሉ ነገር ዞሮበት

"ሚስትህ አርፋለች" ይለዋል ደግሞ

"ከረመች በለኛ!" አለው ይባላል።

ለከፈኗ የሚሆን ጨርቅ የሚገዛበት ገንዘብ ስለሌለው የታረሰው እስኪሸጥ ሳትቀበር ልትቆይ ነው ማለቱ ነው። "ከረመች በለኛ!" ማለቱ። ወዳጆቼ! ጽሁፌን በዚህ ለምን እንደጀመርኩት የገባችሁ ይመስለኛል። ባህር ማዶ ካላችሁ ወገኖቻችን በሽታችንን፣ ችግራችንን ለመፈወስ የተካናችሁት ቴክኖሎጂ፣ ጥበብና ዕውቀት በጊዜው አለመድረሱ እየሸተተኝና ከሞትን በኋላ ለቀብራችን እንኳ መድረሳችሁ እያጠራጠረኝ ነው።

ወንድም ይግለጡ፣ ኑሮአችሁ ምን እንደሚመስል ስታጫውተኝ ጊዜ ሆድ ባሰኝ። ተስፋ ቆረጥኩ። ድሮስ ከአሜሪካ የሚመጣ ከርካሽ ባህልና ሸቀጥ በቀር ምን ሌላ ነገር አለና ነው ተስፋ የነበረኝ? ለችግሬ ትደርሳለህ ብዬ የገመትኩህ ሰው "በጎሊና ተጉዝ ችግራችሁ ችግሬ፣ ጎ ዘቸሁን ጎዘኔ ለማድረግ ሞክሬ አልሆነልኝም!" ብለህ ዕጢዬን ዱብ አደረግኸው። ከሩቅ በወንጭፍ የምትልኩት ምክር አልገባን ብሎን ይሆናል፣ ካልሆነም ከምናልመውና ከምንገምተው በላይ መጥቆብን ይሆናል።

በያ ሰሞን ከዚያው ከእናንተው አገር ለዕረፍት የመጣ አንድ ዘመዴን አግኝቼ ያጋጠመኝን ላጫውትህ። ከዚህ ሲሄድ አንድ ፍሬ ልጅ ነበር። ድሮ እዚህ እያለ ከደጁ እንኳ የማይደርስበት ሒልተን ሆቴል ነው ያረፈው። ልጠይቀው ሄድኩኝ። አምሮበታል። አንተዬ ይሄ አሜሪካችሁ እንዴት ያሳምራል እባክህ? የናፍቆት ሰላምታዎች ከተለዋወጥን በኋላ የአገር ጉዳይ ወሬ ተጀመረ። መግባባት አልቻልንም። ይህች ድሃ አገር በዚህ በያዘችው ሂደት ከቀጠለች በአንድ ምሽት እንዴት አሜሪካ ልትሆን እንደምትችል ሰበከኝ። አሁን የያዘችውን ሂደት አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንዴት አድርጎ እንደገመገማት ገረመኝ። ኢትዮጵያን በግዮንና በሒልተን ሆቴል መነጽር እያዩዋት የዕድገቷን ደረጃ የሚተምኑ ጎብኚዎች በብዛት እየመጡ ነው ይባላል። የዚህ ዓይነቶቹ ጎብኚዎች ወደእናንተ ሲመለሱ የሚነግሯችሁን እያመናችሁ "የደላው ሙቅ ያኝካል!" ብላችሁ ጥልት እርግፍ አድርጋችሁን ይሆን? ከዚሁ ዘመዴ ጋር በመኪና ስንጓዝ ስለአሜሪካ ጎዳናዎች ማማር፣ ስለመኪናዎች መብዛትና በሕግና በሥርዓት መንቀሳቀስ፤ ስለአሜሪካ መኪናዎች ማማርና ምቾት አዳንቆ ያወራኛል። ስለቴክኖሎጂው መሰልጠን ለማመን የሚያስቸግረኝን ሁሉ አውግቶኛል። የኛን ደግሞ እንደማላውቀው ሁሉ እያንቋሸሸና በጣም ኋላ ቀር እንደሆንና አሜሪካንን ባለማወቄ ብዙ ብዙ ነገር እንደቀረብኝ ልክ ልኬን ነግሮኛል። አሁን ይሄ ሁሉ ለእኔ ምን ያደርግልኛል? ምንስ ይፈይድልኛል? እንደው "ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው" እንዲባል ነው እንጂ። መሄጃው ሲደርስ ከዚህ በኋላ ቶሎ ቶሎ መደዋወል እንዳለብንና አንዳንድ ቢዝነሶችንም አብረን ልንሰራ እንደሚገባ ቃል ገባልኝና ተሰናብቶኝ ሄደ። ይኸው እንግዲህ ጠላትህ እልም ይበል በደህና ደረስኩ እንኳ አላለኝም። እዛው ከደሰኮረለት አሜሪካው ሲገባ ያ ሁሉ ቃለ መሃላ ዲስኩር ሆኖ ቀረ እልሃለሁ። የእናንተ ነገር እንግዲህ እንዲህ ነው ማለት ነው? ወሬ ብቻ! ከሩቅም ያለው በቅርብም የተገኘው ወሬ ብቻ! ኪስ የማይሞላ ነገር!- "ኤዲያልኝ ኤዲያ፣ ከሌለ መተያያ" አለች ሴትየዋ!

ወዳጄ ይግለጡ በቅርቡ ከአንድ ወዳጄ ጋር አገራችንን በተመለከተ ወግ ቢጤ ይዘን ስናወጋ "የውድቀትና የውድመት ዘመን መጋጠሚያ ላይ መድረሳችን ወለል ብሎ ታይቶኛል" ቢለኝ እንደው ድንግጥ ብዬ "ምነው?" ብዬ ብጠይቀው "ጥንታዊትና የጀግና አገር የነበረች ኢትዮጵያ ክብርና ታሪክ መዋረድ መጀመሩ፣ ድሐ ው ወገን በመንግሥት ቅምጥሎች አማካይነት ያለአንዳች ምክንያት መረገጡ፣ የኢትዮጵያ ጥቅም በብልጭልጭ መኪና፣ በውስኪና በጋለሞታዎች መለወጥ መጀመሩ ነው። እነዚህ የመንግሥት ቅምጥሎች ለትንሽ ለትልቁ ቦታና ጊዜ

ሳይመርጡ ሽጉጣቸውን በየሰው ደረት ላይ ይመዝዛሉ። በመሸታ ቤቶች በግልፅም በስውርም እንደፈለጉ ይገባሉ። ሕግ አይዳኛቸውም። በአዲስ አበባ ከተማ ጥቂት በማይባሉ የምሽት መሸታ ቤቶች ለምን ታየኛለህ? በሚል ቅብጠት በባለጊዜዎች የተገደለ አቅመ ደካማ ዜጋን ቤቱ ይቁጠረው፤ እና ታዲያ ይሄ ምንን የሚያሳይ ይመስልሃል?" አለኝ።

ወዳጄ ይግለጡ! እናንተንም ያስቸገረው የአንዳንድ አድርባይ ምሑራን ችግር እኛምጋ አለ። ብዙ እውቀት፣ ልምድና ስልጠና የሌለን ሰዎች ብንጉደፈደፍና ብናረጠርጥ በይቅርታ ልንታለፍ እንችላለን። ነገር ግን ማታ ማታ የሚያግበሰብሰውን ምግብ ብቻ እያሰበ የሚኖረውን ጌኛ ለመሆን ከሆነ፣ ምሁርነት በአፍንጫዬ ይውጣ። ከጠላትና ከአገር አጥፊዎች ጋር አብረው የሚርመጠመጡ እነኚህ ተባዮች ናቸው ያስቸገሩን። ,ኤሎሄ! ይሁዳ እንኳ በሰራው ሥራ ተፀፅቶ ጌታውን (ኢየሱስን) የሸጠበትን ገንዘብ ሳይጠቀምበት ራሱን ገድሏል። እነዚህ ሰዎች ግን ለመሪዎቹም ጠንቅ ለሕዝብም መዥገር ናቸው።

በሉ እንግዲህ በቸር ይግጠመን! የናንተው ወርቃየሁ ከሸገር

# ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ

## ከይግለጡ ለወርቃየሁ

ያገር ልጅ ወርቃየሁ እንዴነህ በአያሌው። እንኳን ካለማስጠንቀቂያ ከሚጠርገው ጎርፍ ያተረፈህ። መቼም ሳዘነ ሰው "እንኳን ያተረፈህ ወይም እግዚያብሔር ያጥናህ" ማለት ተገቢና ተጎጂውን የሚያፅናና የመጀመሪያ እርዳታ በመሆኑ አቅሜ ችሎ ወንዙን መገደብ ባልችል እንኳ ለደረሰው ብርቱ አደጋ ከርቀት ሆኜ ሃዘኔን መግለጼ አደጋውን በመንፈስ የተካፈልኳችሁ ያህል ይሰማኛል።

ጉዳታችሁ ከምድርም ከሰማይም መሆኑ ይህች አገር የተጣላችው ከመሪዎቿ ብቻ ሳይሆን ከፈጣሪዋም ጋር ሳይሆን እንዳልቀረ በየጊዜው ከምስማውና ከማየው ተዓምር ጥርጣሬ ውስጥ ገብቻለሁ። ዋናው ነገር በለመደ ጎናችሁ ሁሉንም እንደአመጣጡ ማስተናገድ መቻላችሁ "የደከመው ብርቱ ዜጋ" የሚል ስም ሳያሰጣችሁ አይቀርምና ለአገዛዙም ሆነ ለፈጣሪ ቁጣ የማትበገሩ፣ እየሞታችሁ የምትዋሹ፣ እየራባችሁ የምታገሱ፣ እያለቀሳችሁ የምትስቁ፣ መሆን መቻላችሁ እንኳን በዓለም ሕዝብ ፊት ቀርቶ "በፍርድ ቀን" በሰማይ ቤት ወሮታችሁ ቀላል እንደማይሆን እገምታለሁ።

ወንድም ወርቃየሁ በዱላ ከመቀጥቀጥ፣ በጠመንጃ ከመረሸን፣ በእስር ቤት ከመታጎር አልፎ ለየት ያለና ለማመን የሚያስቸግር ቅጣት በህዝባችን ላይ በቅርቡ እንደተፈፀመ ሰማሁ። ለእውነትነቱ ከፍተኛ ጥርጣሬ ስለገባኝ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ የዜና ምንጮች ትክክለኛውን ለማረጋገጥ ሞክሬ በዕሁፍ የሰፈረ ማስረጃ በማግኘቴ በእጅጉ ዘገነነኝ። እውነትነቱን ካረጋገጥኩ በኋላ ለብዙ ቀናት በሃሳቤ የወገኔ ጩኸት አይምሮዬ ውስጥ ተቀር ጾ ከረመ።

ደግሞ እኛ የማናውቀው ምን ሰምተህ ይሆን? ማለትህ አይቀርም። የሰማሁትን አሳጥሬ ልንገርህ። ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ በዲሞክራሲ ምርጫና በእናንተ ድምፅ አሸንፎ ስልጣን የያዘው መንግስታችሁ ከየጎዳናው ጥግ ተጠልለው የሚኖሩትን ዜጎች ከተማውን ለማፅዳት የተወሰደ እርምጃ በሚል ሽፋን በአፈሳ መልክ ጠራርጎ በውድቅት ጨለማ የዱር አውሬ እንዲበላቸው ጅብ ይበዛበታል በሚባሉት ጫካዎች እያራገፈ ተመለሰ መባልን ሰማሁ። ጉልበታቸው በርትቶ አምልጠው ወደ ሕዝብ ለመቀላቀል የሞከሩ እየተለቀሙ ወደ ዘብጥያ ሲወርዱ ሮጦ ማምለጥና ራሱን ከዱር አውሬ ማዳን ያልቻለው የዱር አውሬ ቀለብ ሆነ አሉ። ይህ ግፍ ቀደምት በሆኑ ግፈኝነታቸው በአደባባይ በተወራላቸው መንግሥታት እንኳ ያልተፈፀመና ያልታሰበ ሲሆን እነዚህኞቹ ሕዝብን ለመቀነስና ከተማ ለማፅዳት ለምን እንደአማራጭ መፍትሔ እንደወሰዱት ለሁላችንም ድፍን እንቆቅልሽ ነው። ለወደፊቱም መልስ የሚያገኝ አይመስለኝም። ምነው እንዲህ ተጨካከናችሁ? ደርግን ከስልጣን ለማውረድ ጠበንጃ አንስተው የነበሩት እንኳን ዛሬ ትግላቸውን ቀንሰው በየጎሳቸው ስለተሰገሰጉ ይህንን ያህል አዲሱን መንግሥት ብዙ የሚያስፈራው ነገር ያለ አይመስለኝም። ታዲያ ምን ጎደለብኝ ብሎ ይሆን ኑሮ የጎዳውን፣ ዕድል ፊት የነሳችውን ሕዝብ ስልቱን እየቀያየረ አይቀጡ ቅጣት የሚቀጣው? ጎ ዘንናሰቆቃ ልክና ወሰን ሲኖረው ይሻል ይመስለኛል።

ወገን ወርቃየሁ ሠላምታዬን አሳንሼ እናንተው ላይ የደረሰውን ግፍ ከሩቅ ሆኜ አወራልህ ገባሁ። እንዲያው ለነገሩ ሰምቼ ያዘንኩ፣ የእናንተን ጉዳት በርቀት ሆኜ የተገነዘብኩ መሆኔን ልግለጽ ብዬ እንጂ "ያዛኝ ቅቤ ..." መሆን ፈልጌ እንዳይመስልህ።

ለመሆኑ የሚወደንና የምንወደው ሕዝባችን ትሻልን ትቶ ትብስን ካገባ በኋላ ከምንሰማው እሮሮ ባሻገር ያስመዘገበው ድል አለ ወይ? ባለፈው ሰሞን የአድዋን ድል በከፍተኛ ድምቀትና እምዬ ምኒልክ ላይ በመደንፋት አከበራችሁት አሉ። ምነው የቆመው አንቧችሁ ሙት በአደባባይ የምትወቅሱት? ጣሊያንን መንገድ እየመሩ ያስገቡት ተመስግነው ለአገሩ ድንበር የተዋደቀውን ሠራዊትና ጦሩን የመሩትን መሪ ማንቋሸሽና መዝለፍ ደግ አይመስለኝም። ደግሞ የአድማጩ ጭብጨባ ምን ይባላል? የመሃል አገር ሰው ከበሮ ለሞኝበት ማጨብጨቡን አሁንም አልተወም? ዋጋው ነው ይበለው እንዳልል እኔም የግፈኞቹ ደጋፊ የሆንኩ እየመሰለኝ ነገ ለሚያልፍ ቀን ከእነሱ ጋር እንዳልደመር ፈራሁ።

ለመሆኑ በአሁኑ አገዛዝ የዘር አሰላለፍ የህዝባችን ረድፍ አያያዝ ምን ይመስላል? አንዳንዴ በሃገር ውስጥ ያለው ሁኔታ ራሴ በምፈጥረው የአይምሮ ስዕል ውስጥ እየታየኝ እንደመገረምም እንደመሳቅም ያደርገኛል።

እንደሚታወቀው በሃገራችን በጥናት የተቆጠሩ ሰማንያ ጎሳዎች እንዲሁም በጣም አናሣ የሆኑና ወደመጥፋቱ ወይም በሌላ እየተዋጡ ያሉ ቁጥራቸው ከሃያ ሶስት የማያንስ በድምሩ ከመቶ ሦስት ያላነሱ የዘር ዓይነቶች አሉ። እነዚህ ጎሣዎች ለዘመናት በዚች ኢትዮጵያ በምትባል ምድር ላይ የከረረ ጠብ ሳይፈጥሩ በአንድ አገር ዜግነት ኖረዋል።

ማዕከላዊ መንግሥት ለመፍጠር የስልጣኔ ደረጃ በፈቀደበት ጊዜ ከጎሣ መሪዎች ጀምሮ የሃይማኖትና የሃገር መሪዎች በጦርም ሆነ በህዝብ እምነት አገር ማስተዳደር እንደጀመሩ ታሪክ ይናገራል። እንግዲህ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሰውን ሰው መሸጥና በእሞሌ ጨውና በሌላ የሸቀጥ ዓይነት መለወጥ ሲጀመር ጎንደሬው ጎንደሬውን፣ ወሎዬው ወሎዬውን፣ ዶርዜ ዶርዜውን ወዘተ በአጠቃላይ ጉልበትና የተሻለ ንብረት ያለው ዘር ሳይለይ አንዱ አንዱን በባርነት መግዛትና መሸጥ እየተለመደ መጣ። በዚህ የባሪያ ንግድ አንዱ ጎሳ ባሪያ ገዥ ሌላው ሻጭ አልነበረም። የባሪያ ሸቀላ የተመሰረተው በጉልበተኛና በደካማ መካከል ነበር። ይህንን ለምን እልክ ምንስ አመጣው? ትለኝ ይሆናል። ምክንያት ስላለኝ ነው። የዛሬዎቹ መሪዎች አንዱን ዘር የበላይ ሌላውን የበታች ሆኖ እንደኖረ ሲሰብኩና ለስልጣን ዘመናቸው መራዘሚያ ዘርን እንደዋና መሣሪያ መጠቀሚያ አድርገው በእምነት የተንበረከኩላቸውን በደጋፊነት በማስጠጋት በመተሳሰብ ይኖር የነበረውን ሕዝብ ለመበታተንና ተዝቆ የማያልቅ የዘለዓለም በሽታ ሲያሰራጩ በማየቴ ነው። ምነው እልነጋብህም ወይ? እንደምትለኝ ይገባኛል። ግን የምለውን መዘክር ስላለብኝ የሚሰማኝን መግለፅ እፈልጋለሁ።

ሁሉንም ለማዳረስ ባይቻልም እስቲ በአሁኑ ወቅት እንደአባ ዋራ ዘር ተቆጥረው ለአዲሱ ክልል ምሥረታ ምክንያት የሆኑትን አማራ፣ኦሮሞ፣ ትግሬ የተባሉትን ብቻ እንመልከት። ለመሆኑ አማራ የሚባለው ዘር የትኛው ይመስልሃል? ጎንደሬ፣ ጎጃሜ፣ ወሎዬ፣ ሸዌ፣ ሐ ረርወይስ በአጠቃላይ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪው? አንዳንዴ ለዚህ ጥያቄ የምሰጠው መልስ በጣም የተሳሳተ ስለሚሆን በሁሉም ክፍለሀገሮች የሚኖረውን ሕዝብ በአማካኝ ለመደልደል እሞክራለሁ። ግን ይህም የአመዳደብ ስልት ከሚናገሩት ቋንቋ ከሚኖሩበት አካባቢ ጋር የሚተሳሰር ስለሆነ ለበለጠ ስህተት የሚገፋፋ ይሆንብኛል። በመልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ በባህልና በስነልቡናዊ ዘይቤ ጎንደሬውን፣ ትግሬና ወሎዬውን ለያይቼ አላያቸውም። አሁንም በሚታይባቸው ባህርይ ብዙ የሚመሳሰል ጠባይ ስላላቸው ተቀላቅለው የኖሩ ሕዝቦች ለመሆናቸው ብዙ ማመሳከሪያ መጥቀስ ይቻላል። ግን ጠባቸው እኔ ከአንተ እሻላለሁና የበላይነቱን መያዝ ይገባኛል የሚል ትዕቢት ይታይባቸዋል። እዚህም አሜሪካ ውስጥ በጎንደሬውና በትግሬው መካከል የሚታየው የእኔ እበልጥ ፉክክር ቀላል አይምሰልህ። እንዲያውም የፖለቲካው ትግል በአብዛኛው ሲከርና ጠብ ሲፈጥር የሚታየው በእነዚህ ሁለት ሰሜንተኞች መካከል ነው። ሌላው ደግሞ የራሱ የሆነ ከእነሱ የተለየ አጀንዳ ያለው ይመስላል።

የኤርትራውያኖች ደግሞ ከሁሉም ለየት ይላል። እንዴት መሰለህ። "ዋናቸውን ይዘው በትርፍ መጫወት" ይፈልጋሉ። "ኢትዮጵያ የጋራ ኤርትራ የግል ናት" የሚል እምነት አላቸው። ኧረ አይሆንም ብትላቸው አይሰሙህም። በመራራውና በረጅሙ ትግላችን ሀገራችንን ነፃ አውጥተናል እኛ ያለፍንበትን ጎዳና እናንተም መቅመስ አለባችሁ ባይ ለመሆናቸው በየጊዜው ከሚያሳዩትና በአደባባይ ከሚናገሩት ትረዳለህ። ደርግ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያደረሰውን በደልና የፈፀመውን ግፍ በእነሱ ላይ ብቻ የተቃጣ አድርገው ስለሚገምቱ ደርግ ለፈፀመብን ግፍ ብድሩን መክፈል ያለበት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ባይ ናቸው። በሰሜን ከተፈፀመው ግፍ ባላነሰ በሌላው የሀገራችን ሕዝብ ላይ የተፈፀመው በደል የእነሱ ቁስል አይደለም። እንዲያውም የሚያውቁት አይመስሉም። እንግዲህ በእነሱ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ የቆመው የደርግን ዕዳ በመክፈልና ራሱን በደለኛ አድርጎ በማቅረብ መካከል መሆኑን መገመት አያዳግትም።

ልጅ ወርቃየሁ ይህንን ካነሳሁ በጣም የሚገርም ትርዒት ላጫውትህ። በአሁኑ ሰዓት ወደአሜሪካ በጉብኝት መልክ ከሚገቡት ኢትዮጵያውያኖች መካከል ኤርትራውያኖች ይገኙበታል። ታዲያ በቋሚነት አሜሪካ ውስጥ ለመኖር የመንግሥት ፈቃድ ማግኘት ስላለባቸው ወደ ኢምግሬሽን ቢሮ ብቅ በማለት የፖለቲካ ጥገኝነት ፎርም በመሙላት የነዋሪነት ፈቃድ ይጠይቃሉ። እንግዲህ አስገራሚው ትርዒት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው። በአንድ ወቅት ለኤርትራ መገንጠል ድምፅ የሰጠው፣ ኤርትራ የኢትዮጵ ያ ቅኝ ግዛት ነበረች የሚል እምነት ያለው፣ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ በማሰባሰብ ለሻዕቢያ ድጋፍ የሚሰጠው ሁሉ በፖለቲካ ጥገኝነት ማመልከቻ ላይ የሚሞላውን ለማመን የሚያስቸግር ነው። "የኢትዮጵያን መገነጣጠል የማልደግፍና አለአግባብ የተደረገውን ውሳኔ በብርቱ በመቃወሜ በመንግሥት ተቃዋሚነቴ ተፈላጊ ነኝ። ስለዚህ ለህይወቴ ስለምፈራ የሻዕቢያ መንግሥት ካልወደቀ ወደሀገሬ መመለስ አልችልም።" የሚል ነው። ይኸውልህ ለጥቅማቸው ኢትዮጵያን መነገጃ ሲያደርጉ በእምነታቸው ደግሞ ለሻዕቢያ ረጅም እድሜ የሚፀልዩ በቁጥር ተዝቀው የማያልቁ የመንፈስ ድዊ ፍጡራን አሉልህ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በጣም የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ለሻዕቢያ የረጅም ጊዜ የውትድርና አገልግሎት በመስጠት ሜዳ በነበሩና አንድ ጥይት ሳይሞኽባቸው ከመሃል ከተማ በቀጥታ አለችግር አሜሪካ በገቡት መካከል የሚታየው ልዩነት ቀላል አይደለም። ተዋጊ የነበሩት በሥነሥርዓት የታነፁና የበላይ አካል በሚሰጣቸው መመሪያ ብቻ ከመስራት ባሻገር ተራ በሆነ ጭቅጭቅ ውስጥ የማይገቡ ሲሆኑ ይሄ ከመሃል አገር የመጣውና የኤርትራን መሬት በእግሩ ረግጦ የማያውቀው የድል አጥቢያ አርበኛ ግን የሚያደርጋቸውን ያሳጣቸው፣ ልታይ ልታይ የሚያበዙ፣ በትዕቢት ደረታቸው ያበጠ፣ በመሃል አገር ህይወታቸው በህዝቡ ላይ የደረሰውን ግፍ የሚያውቁ የማይመስሉ፣ በእድሜ ቢገፉም በአይምሮ ገና እንደህፃን በማሰብ ከበሰለ ውይይት ይልቅ ተራ ብሽሽቅ የፖለቲካ መሣሪያ

የሚመስላቸው ናቸው። እኔ እነዚህ አይነቶቹን ከመታዘብ አልፌ ንቄ ትቻቸዋለሁ።

ስለ ኦ.ነ.ግ. ብዙ የምልህ የለም። እኔም ሆንኩ መሳው የአሜሪካ ነዋሪ አበሻ ምን እንደሚፈልጉና የፖለቲካ አጀንዳቸውም ምን እንደሆነ ግልጽ ስላይደለ በመሣሪያነት መንግሥትን ለማገልገል የተቋቋመ ድርጅት ከምለው ባሻገር ዝርዝር የሆነ አስተያየት ለማቅረብ እቸገራለሁ። ለምን ብትል ራሳቸውን ሰድበው ለሰዳቢ የሚያጋልጡ፣ ጥቂት በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ከሚቀርቧቸው ጋር ተመሣጥረው ያቋቋሙት "ጭራና ቀንድ" የሌለው ማኅበር በመሆኑ ምን እንደሚፈልጉና የትግላቸው መነሻና ግብ እስከምን እንደሆነ እስከረዳ ድረስ መነካካት አልፈልግም።

እንግዲህ ወርቅአየሁ ለዛሬው በዚህ ላበቃ አስቤ ነበር። ግን ባለፈው መልዕክትህ በስተመጨረሻ ላይ ምን ለማለት እንደፈለግክ ባይገባኝም በጽሁፍ ወዳጂ ብዕር መሰደቤ ቅር ስላለኝ ትንሽ የምልህ ይኖረኛል።

አንተው በፅሁፍህ ካሠፈርከው ልጀምር "አንተ ደግሞ አሜሪካ እንዲህ ሆነች፣ እንዲህ ተመነደገች እያልክ ትመፃደቅብኛለህ" በአረፍተ ነገርህ መጨረሻ ላይ ቃሉን ለማሰሪያ የተጠቀምክበትን ቃል አልወደደኩትም።

የማነህ ተሣዳቢ እባክህ። ምን እንድልህ ፈለክ? አሜሪካን ተከፋፍላለች፣ ሕዝቡ በችጋር አለቀ፣ በረንዳ አዳሪዎችና ቤት የለሾች እየታፈሱ አማዞን ወንዝ ተጣሉ፣ ድርቅ የኒውዮርክን ሕዝብ ለስደት ዳረገው፣ ፕሬዚዳንት ክሊንተን ሕዝቡ በዘር ተከፋፍሎ ክልል እንዲያወጣ አዋጅ አስነገሩ፣ ካሊፎርኒያ በውሳኔ ሕዝብ ከአሜሪካ ተገነጠለች። ምን እንድልህ ፈለክ?

እኔን በግል መወረፍ አስኝቶህ ከሆነ እፈቅድልሃለሁ። መቼም ሆድ የባሰህ ነህና እኔን በማሸሚጠጥ ብሶትህን የምታስተነፍስ መስሎ ከታየህ ግፋበት። እኔ ግን እዚህ ከማየው ውጭ ጨምሬ ወይም ቀንሼ የምነግርህ የለም። ለምን እንደእኛ የሰቆቃ ኑሮ አትኖሩም፣ እኛ የቀመስነውን ግፍ እናንተም ጋ ሊኖር ይገባል የሚል ቅናት ከያዘህ ተንጨርጭረህ ትሞታታለህ እንጂ እኛ እንደሆነ ሲያልፍም አይነካካን። መንግሥታችንም ሌላውን እያጣላና እያቧቀሰ ዳር ሆኖ መሣቁን አያቆምም። ለአሜሪካ ከተፈጠሩት የመዝናኛ አይነቶች አንዱ በሌላው ሞት መሳቅና ለበረታው ከፍል ጠበንጃ ማቀበል መሆኑን አትዘንጋ። ብርታቱን ይስጥህ። ልዩነታችን የሠማይና የምድር የገነትና የሲኦል ያህል እንደሆነ ተረዳ።

እንግዲህ ለዛሬው ይብቃኝ በሚቀጥለው ዝግጅቴ ግን ሌላ ከዚህ ለየት ያለ ዝግጅት ይኖረኛል። በአሜሪካ የሚኖረውን የአበሻ ዘር "ፍቅርና ጋብቻ" በ ጾታዎች መካከል የሚደረግ ግኑኙነትን አስመልክቶ የሚታዩትን አስቂኝ ትርዒቶች በሰፊው ልተችባቸው ተዘጋጅቻለሁ። በመጀመሪያ ግን የአንተን መልስ የምጠብቅ ሲሆን በስሱ የጀመርከው የብዕር ጉንተላህን የምትቀጥልበት ከሆነ ጦሬን ከመምዘዝ ወደኋላ እንደማልል ተገንዘብ። ተግባባን።

በል እስከዛው ከነብሶትህ ደህና ሁንልኝ።

ይግለጡ ነኝ። ከነፋሲት (ቺካጎ)


**Allstate**
You're in good hands.

4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404) 299-7287 □ FAX: (404) 299-6266



AUTO
HOME OWNER'S
RENTER'S
LIFE
BUSINESS
COMMERCIAL AUTO

THEODROS HAILEGIORGIS
*Exclusive Agent*

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allstate Indemnity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

You're in good hands.

# ከገብርዬ ለወርቃየሁ
## (ደብዳቤ ከባሕር ማዶ)

ያገር ልጅ ወርቃየሁ እንዴት ሰነበትክ።

እኔና ይግለጡ በበላ አንጀታችን እየተፈራረቅን እንዳናጠቃህ የበለጠ እንድትመክትና አጋርም አዘጋጅተህ እንዳትቦዝን ከእንግዲህ በኋላ አስብበት። ውርድ ከራሴ ነውና "እንደለመዱት ለምን ይፎክራሉ" ሳትል እየታዘብከን ቀበቶህን ጠበቅ አድርገህ በሁሉም በኩል ፍልሚያህን አስፋው። አንተና ይግለጡ ላደረጋችሁት ተሳትፎ እድሜ ይስጥልኝ ከማለት በስተቀር ሌላ የምሰጣችሁ ምርቃት የለኝም። እናቶቻችሁንና አባቶቻችሁን ያፈራችው ኢትዮጵያ በእርግጥም መኩራት ይገባታል። ያስተማራችሁት ቀላል አይደለም። በእናንተ ተሳትፎና በማይታክተው አዘጋጅዋ ዛሬ ላንዳፍታን እንደኳስ እየተቀባበለ የማያነባት ወገን የለም። የሚገርመው ግን በዚህ በአሜሪካ አንዳንድ ቦታ $2.75 አውጥቶ መጽሔቷን ከመግዛት ይልቅ እየተዋዋሰ የሚያነባትና እንደሥልቻ በማልፋት ልባቧን የሚያሳሳት ጩቅ ሞልቷል። የሻገተ ዳቦ ባረረበት ውዲቱ ሀገራችን ተቀባብላችሁ ብታነቧት እንኳ አልፈርድባችሁም።

የሕዝባችን በጎሳ መራራቅ እጅግ እያሳዘነኝና ስሜቴንም እየጎዳው ነው፤ እንዴት አቀራርበን ወደ ፍትሐ ዊ ትግል እንደምናመራ አንዳንዴ ግራ ይገባኛል። የወያኔ አባላት ሁሉንም ነገር በራሳቸው መነፅር ከጎሳ አንፃር ሲያዩት፣ ይህንንም ለመለወጥ መደረግ ያለበትን የትግል ክብደት ስመዝን እጅግ ያሳስበኛል። አየህ! ከሕይወት ባሻገር ተስፋ ባይኖር የሰው ልጅ ኑሮ ትርጉም የለውም፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ጎሳዎች የኋላ ኋላ ከሚለያዩዋቸው አቋሞች ይልቅ አንድነታቸውን የሚያጎሉ ሁኔታዎች በልጠው ስለሚታዩ እነዚህም ላይ በማተኮርና በመደጋገፍ መልሰው አንድነትን እንደሚፈጥሩ ይታየኛል። ወያኔዎችን "ይህ የዘር መርዝ ሁላችንንም ይጎዳል፤ የትግራይ ሕዝብ በታሪካዊነቱና በወገንነቱ እንዲሁም በጥቁርነቱ የአማራው፣ የጉራጌው፣ የኦሮሞው ... ወዘተ ወንድም ነው። ላንዳፍታ እንዳለችው የኢትዮጵያውያን ምኞትና ዓላማ በፍቅር፣ በመቻቻልና በመደማመጥ አብሮ መኖርን ነው። የወያኔን መንግስት መቃወም ማለት ፀረ-ትግሬ መሆን ማለት አይደለም። አብዛኛው በምዕራቡ ዓለምና በኢትዮጵያዊ ምድር የሚኖር ኢትዮጵያዊ የመለስ ዜናዊን መንግሥት የሚቃወመው አገር ተነጣጠለ፣ ሀገር ፈረሰ፣ ሕዝባችን ለወደፊት እጅግ በሚያሰጋ የዘር መርዝ ተበከለ፣ ታሪካችን በአሳፋሪ ሁኔታ ተውገረገረ ከሚል እንጂ ትግሬ ለምን ገዛ ከሚል አይደለም" ስትላቸው ይህችማ ፖለቲካ ናት በማለት የውይይት በሩን ይዘጋሉ። ለዚህም ነው ትግሉ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሊሸጋገር እንደሚችል የማየው።

መቼም ለጉድ ነውና የተፈጠርነው ቀለም በማይነጥፈው ብዕርህ ባለፉት እትሞች ለይግለጡ የፃፍከውን የገበና ደብዳቤ በጥሞና ተመልክቼዋለሁ። የይግለጡንም አንጀት አርስ መልስ በተደጋጋሚ አንብቤዋለሁ። እኔም በበኩሌ ዕውቀት እንዲፈነጥቅልህ ስለአሜሪካና እዚህ ስለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እውነት የመሰለኝን በይግለጡ ላይ ላክልበት እወዳለሁ። ፈረንጆች ሲተርቱ ዕውቀት ኃይል ነው ይላሉ። ስለእውነት ከተነሳ አንድ የሚያስገርም ነገር ልንገርህ እያንዳንዱ መንግሥት እውነትን የሚተረጉመው ከራሱ አመለካከት አንፃር ነው። የአሜሪካ ፈረንጅ እንኳ ሳይቀር ላንጅሌ በሚገኘው የሲአይኤ በር መግቢያ ላይ "እውነትን እሹ፣ እውነትም ነፃ ታዋጣኃለች" የሚለውን የመጽሐ ፍ ቅዱስቃል ጽፎ ሳይ የመንግሥት ፖለቲካ እጅግ ይደንቀኛል። እስቲ በእግዚአብሔር ይሁንብህ ከስለላ ድርጅት የበለጠ የዲያቢሎስ ተቋም ከቶ የት ይገኛል?

ይግለጡም እዚህ አጠገቤ እየኖረ የአሜሪካ ኑሮ እናውዞታል መሰለኝ አንዳንዴ ላንተ ከሚጽፈው ደብዳቤ በስተቀር ይኸውልህ እተዋወቀዋለሁ እያለ እኔም ስጠብቀው የውኃ ሽታ ሆኖ ቀረ። ጭራው ባይያዝም አልፈርድበትም። አሜሪካ ጊዜ ብር ነው። ነገር ግን አቋሙን ስመረምር ይግለጡ ሰባት የእንጨት ሳጥን ብር ካጠራቀምኩ በኋላ ነው መሰሎቼን የምፈልግ የሚል አይመስለኝም፤ እንደሌሎችም ሁሉ ወደመካከለኛው የአሜሪካ መደብ ተስፈንጥሬ አንድ ቀን ቱጃር ሆኜ ነው ለሌሎች ወርቃየሁ መሰሎች ብር የማጎርሳቸው እያለ በህሳብ ጨጓራውን የሚመልጥ አይመስለኝም፤ ቢያንስ ቺካጎ አልካሲልዘር በቁና እንደሚሸጥ አውቃለሁ። ይኸንንም ስልህ ያንን ያህል ሞኝ አልምሰልህ። ይግለጡ እንዳንተ ልበደንዳናና በሀገሩ ታሪክ እምነቱ የጠነከረ መሆኑን ተረድቼአለሁ።

ምንም እንኳ የይግለጡ ደብዳቤ ቢያስመረቃኝም እኔ ደግሞ ትንሽ አልጠነከረም ባይ ነኝና ይኸኛውስ አክራሪ ነው ሳትለኝ ቢጨልም እንኳ የኮረንቲ ብርሃን ከሌለህ በኩራዝና በአጣናም ውጋጋን የእኔንም ደብዳቤ ጨርሰህ ተመልከተው። የአዲስ አበባም ባሕር ዛፍ ተቆርጦ ካለቀ ማታ በጨረቃም ቢሆን ገፅ በገፅ ሂድበት፣ ጨረቃም ካልወጣች ሥራ ከመሄድህ በፊት ጠዋት ጀምበር ስትፈነጥቅ እያገላበጥክ ተመልከተው። ስለሆነም ወንድም ይግለጡ ያልነካውን ወይም ምናልባት በአክባሪነትና በትሁትነት ረገብ አድርጎና ለአንባቢ ሳይጎረብጥ እንዲሰማው በፃፈው ላይ አክዬበት እኔም አንዳንድ ጨዋታ ላማውትህ።

በእርግጥ በአሜሪካ ከገንዘብና ከሀብት ፍትሕ በመለስ ሰብዓዊ መብት ይከበራል። ገንዘብ ካለህ በፊሻሌ ሽጉጥ አንዱን ትዕቢተኛ አዳፍነህ ዝነኛ ጠበቃ በመቅጠር ከእሥር ማምለጥ ትችላለህ። እሥር ቤቶችም ፍርድ ቤቶች መደባዊና ቀለማዊ ይዞታ አላቸው። ኮሌጅ ከሚሄደው የጥቁር ወጣት ይልቅ ወህኒ ቤት የሚማቅቀው ይበልጣል። አስተዳደርን በሚመለከት ማንም መላጣ ድሃ በአስተሳሰብ ብቻ ርዕሰ-ብሔር ወይም የምክር ቤት አባል የሚሆን አይምሰልህ። በእርግጥም ጥቁሮች በኮንግሬስና በሴኔቱ ውስጥ ባላፉት 30 ዓመታት ቁጥራቸውን በማሳደግ ቢሳተፉም በዘር መድልዎና በመደባዊ ይዞታው አሜሪካ አድሎአዊ ኅብረተሰብ ነው። መቼም ለኑሮ ከማንኛውም ሀገር ይሻላል ከሚል እንጂ ያ የምንኳንለት የሰው ልጅ ልዕልናና ክብር እዚህም ሀገር ገና ብዙ ይቀረዋልና በፊልምና በዓለም አቀፍ የሚተረክለት ዴሞክራሲ እንዳያጭበረብርህ ተጠንቀቅ። እንዲያው አንዳንድ ግልፅ ነገሮችን አለፍ አለፍ ብዬ ለመግለፅ እንጂ ኅብረተሰቡን

ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት ደካማና ጠንካራ ጎኑን ለማተት የዓለም ወረቀትም የሚበቃ አይመስለኝም። የሆኖ ሆኖ ባላት ሐ ብት፣ ሥልጣኔና የሰው ኃይል አሜሪካ ከግለኝነት ባህሏ ተላቃ ሞራላዊ አመራር ለዓለም ሕዝቦች ለመስጠት ያላት ችሎታ(potential) እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ እገነዘባለሁ።

ሌላው የሚደንቀኝና ላካፍልህ የምፈልገው እንደሥርዓተ ማኅበሩ አንዳንድ ፅንሰ ሀሳቦችና ቃላቶችም በቅራኔ ያሸበረቁ ናቸው። ለምሳሌ እዚህ ሀገር በጠረጴዛ ሥር የሚሸጎጥ ቀጥተኛ ጉቦ የለም። ነገር ግን ባለሥልጣንን ለማስመረጥና ባለሥልጣኑም ከተመረጠ በኋላ ሥራህንና ዓላማህን እንዲደግፍ ለምርጫ በሕጋዊ መንገድ የሚሰጥ ገንዘብ አለ። ስሙ ግን ጉቦ ሳይሆን የፖለቲካ ድርጊት ገንዘብ (Political Action Committe Money, PACMONEY) ይባላል። ባለሥልጣኑም ከተመረጠ በኋላ ለዓላማህና ለድርጅትህ ይታገላል፤ ውለታህንም ሳይውል ሳያድር ይመልሳል። ከከረረ የጎሳ የነፃ አውጪ የጠበንጃ ፖለቲካ በስተቀር ሦስተኛ ዓለም ያለ ሸር ሁሉ እዚህም አገር አለ። ማን ያውቃል እኛም እንደአሜሪካውያኖች ሀብታም ብንሆን ከእነርሱ እንብስ ይሆናል።

እዚህ ሀገር ቃሉም ሸሩም እንደሥልጣኔው የተራቀቀ ይመስለኛል። ለምሳሌ ትላልቅ ኩባንያዎችና መሥሪያ ቤቶች ሠራተኛን በገፍ ሲያባርሩ ዳግማዊ ማስተካከል (RESTRUCTURING) ይሉታል። አንዳንዶቹም መጠናዊ-ቅነሳ (DOWN SIZING) ብለው ሰይመውታል። ይህ የሚያሳየው የኅብረተሰቡን ደንታቢስነትና ርኅራኄ አልባነት ነው ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። እዚህ ላይ ለማስታወስ የምፈልገው አይኤምኤፍና ወርልድ ባንክ በሚሰጡት ብድር የተነሳ የሚደርሰውን የሠራተኛ መባረር በሶስተኛ ዓለም መዋቅራዊ መስተካከል (STRUCTURAL ADJUSTMENT) ብለው እንደሚጠሩት እናንተም የተረዳችሁት ይመስለኛል። በጦርነት ወቅት ሕፃናትን ሽማግሌዎችንና ሴቶችን በቦምብ ሲያቃጥሉና ሲጨፈጭፉ የተያያዘ እላፊ ጥፋት (Collateral Damage) ይሉታል። በሌላ በኩል ደግሞ ያኔ የደቡብ አፍሪካ ሰላም ሳይመሰረት የነጩን ዘረኛ መንግሥት በሚደግፉበት ወቅት ፖሊሲያቸውን ገንቢ መስተናግድ (Constructive engagement) ይሉት ነበር። በቀዝቃዛው ጦርነትና አሁንም ቢሆን የእነርሱን ኩልኩል ሠርጎ ገቦች የነፃነት ታጋዮች ወይም ሀገር ወዳድ ዴሞክራቶች ሲሉ ሌሎችን ከእንርሱ ኩልኩሎች በድርጊት ያልተናነሱትን ሽብር ፈጣሪዎች ይሏቸዋል። ለፖሊሲአቸው የከፋ ገፀ-ባህርይ የሚሰጡትን ፖለቲካዊና አመራራዊ ቃለ ፅንሰ ሃሳቦች በለዘቡና በሚያስደስቱ የሚመነዘሩ ከሀገሪቱ ፖለቲካ ጋር የተቆላለፉ ልዩ ልዩ መንግስታዊና የግል ድርጅቶች እንደአሸን የፈሉበትም ሀገር ነው። እንደካርኔጌ ኢንዳውመንት እንደ ኬቶ ኢንስቲትዩት ያሉትን ለምሳሌ መጥቀስ ይችላል።

በሌላ በኩል የሚያስደስትህ ሌላው ትልቁ ቁምነገር ሕገመንግስቱ ሰብዓዊ መብትን ከሌሎች ሀገሮች በተሻለ ሁኔታ ያከብራል። እንደኛ ሀገር ሕግን ሳይጠቅስ ማንም እሥር አለቃና የነፃ አውጪ ሹምባሽ በአደባባይ በጠረራ ፀሐ ይአይረሽንም። ሌላው ቀርቶ ወንጀል በፈፀምክበት ጊዜ ወይም ተጠርጥረህ ከተያዝክ ጥፋትህ ተነግሮህ ነው የምትታሰረው። ራስህን አጋልጠህ ላለመናገር መብት አለህ፤ የተናገርከው ሁሉ በህግ ፊት ስለሚቀርብ ራስህን የሚወነጅል ነገር እንዳትዘባርቅ መብትህ ይነግርሃል። ይህም የሚራንዳ ህግ (Miranda Law) ይባላል። በአምስተኛው አንቀፅ በተሻሻለው ሕገመንግሥት መሠረት ራስህ ላይ ላለመመስከርና የመስቀለኛን ጥያቄ ላለመመለስ መብትህ በሕግ የተጠበቀ ነው።

በኑሮም አኳያ ሲታይ ቢያንስ ለድሀው ሕዝብ በተተመነው መና (Minimum Wage) ተቀጥረህ ኑሮህን መግፋት ትችላለህ። ነገር ግን ያችን ከእጅ ወደ አፍ የዘበኛ ደመወዝ ሁሉም በዝባዥ ተምትሞ ስለሚቃመሳት ኪራይ፣ ኢንሹራንስና የመብራት ከፍለህ ትርፍህ የፊት መሸብሸብና የሽበት መብዛት ናቸው። ከተማርክም እንደ ችሎታህ ወጥ ሳትረግጥ ሌላ ከፍተኛ ሥራ ካልፈልግህና ከነጭ ጋር ካልተወዳድርክ ሥራ አታጣም።

"በአሜሪካ ጠንክረህ እስከሠራህ ድረስ ለዕድገትህ ሁሉ ወሰኑ ሰማይ ነው" (The Sky is The Limit) የሚሉትን አትስማ። ዳግመኛም ቁጥራቸው ይነስ እንጂ እነርሱ ወደላይ እንደመንኮራኩር በተተኮሱ ቁጥር በተትረፈረፈው የኅብረተሰብ ቁሳቁስ ሳይረኩ ራሳቸውን በሽምቀቆ ድብን አድርገው ሕይወታቸውን የሚያጠፉም አሉ። በእርግጥም እንደ ዱር አራዊት ተራግጠውና ተናክሰው ከዳርዊናዊ ህግ ፍንከች ሳይሉ ወገናቸውን የሚደፈጥጡ እያሌ ዜጎች ከተማረውም ከቦዘኔውም ከሀብታሙም ከድ ሐውምታገኛለህ። ትልቁ አሳ ትንሹን ሳያመነታ ከንፋን አጨብጭቦ ይውጣል። ይህን የማካ ትግል ነፍሳቸውን ይማረውና ማርክስም ሆነ ዳርዊን በሚያስደንቅ ሁኔታ አስቀምጠውታል። ማርክስ በአንዳንድ ጉዳዮች ቢሳሳትም ኅብረተሰቡን በመረዳት በኩል የዋዛ ጢማም ሽማግሌ እንዳይመስልህ። ሙት ወቃሽ እያደርገኝና ማርክስን ብቀየመውም አንዳንድ ቦርጫም መደዴ ከፍና ዝቅ ሲያደርገው ብሎም ሲያዋርደው የማይሰማኝ አይምሰልህ።

ሌላው የበለጠ የሚያስቀው አንዳንድ ጥቂት ባሕታዊ ሳይሆኑ ፀጉራቸውን የገመዱ፣ ጀግንነት ሳይሰሩ ሎቲ ያንጠለጠሉ ፈሳም ሁላ ይህ አሜሪካ ነው፣ ነፃነት አለን እንደሌሎች ኢትዮጵያውያን ሚሊዮነር እንሆናለን ሲሉ ነው። ባለፉት 25 ዓመታት ስንት ባለ ሚሊዮኖች (ቱጃሮች) አፈራን ብትላቸው ግን በዚህ እስቴት እገሌ 10 ሚሊዮን ብር አለው ከማለት በስተቀር የሚሰጡት መልስ የለም። አብዛኛው ሕዝባችን ግን ጥሮ ግሮ ጉልበቱን ሸጦ የሚተዳደር ነው። ጥቂቶችም ቀበቶአቸውን ጠበቅ አድርገው ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ ከፍተኛ ቦታ የደረሱ አሉ። በዚህ ኅብረተሰብ እየተውተረተሩ ብዙ የሚወራላትን የሀገሪቷን ምኞት (American Dream) ለማሟላት ሌት ተቀን የሚጥሩ ጠንካራ ሠራተኞች ብዙ ናቸው። ነገር ግን በገንዘብና ንግድ በመመሥረት ከሌሎች ንዑሳን ሕዝቦች ጋር ሲወዳደሩ ኢትዮጵያውያን ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ በትክክል የተደረገ ጥናት የለም።

ከላይ አንድ ቦታ እንደጠቀስኩት የአሜሪካ ኅብረተሰብ ያስፈለገው ልሽቀት፣ ድክመት፣ ቅራኔና መድልዎ ቢኖሩትም በአሁኑ ጊዜ ለኑሮ ከአሜሪካ የተሻለ ሀገር የለም። ወደፊት የበለጠ እንደሚሻሻል አልጠራጠርም። አሜሪካ የተያያዘችው ጎዳና አብዮታዊ ለውጥ ሳይሆን ዝግመታዊ ለውጥ ነው። እንደሚረዳኝ

ከሆነ የአሜሪካ ለውጥ በሕዝብ ነቀፋ፣ በፓርላማዊ ሕጋዊ ውሳኔ (Legislative remedy) እና በዙፋን ችሎት (Supreme Court) ላይ የተንተራሰ ነው። እንደሎዝአንጀለሱ የተወሰነ ግብታዊ አመፅ በስተቀር አሜሪካን በምንም ዓይነት አብዮት አይሞከራትም። በሌላ መልኩ ደግሞ ኅብረተሰቡ የሥልጣኔ መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ለኑሮ የሚያመቹ ነገሮችን ቢፈለስፍም የሰው ልጅን ግብረገብነትና አወንታዊ ገጾች ነፃ ስላላወጣ እንዲያውም ግለኝነትን ስላበዛ ኃጢአትን አጉልቶታል። ስለአሜሪካ ኑሮ ስናነሳ በሕፃናት፣ በሴቶች፣ በንዑሳን ዜጎችና በድውያን መብት ባለፉት 30 ዓመታት ትልቅ መሻሻል እንደመጣ መገንዘብ ይኖርብናል። ሴቱ እዚህ ሀገር ትልቅ ኃይል አለው። ከፈለገች ሴቷ ዋሽታ ማሳሰር ትችላለች። የእኛም ሴቶች የዚህን ኅብረተሰብ ባሕል ለመውሰድ በሚያደርጉት ትግል ብዙውን ጊዜ ከወንዱ ጋር አይስማሙም። እዚህ ላይ የወንዱ ስህተትና ትምክህት የለም ለማለት አይደለም። ስለሆነም ወንዱ ኢትዮጵያና ሱዳን እየሄደ አግብቶ መምጣት ጀምሯል። ይህ የባህልና ጾ ታዊ ክስረት (Crisis) በእውነቱ ጥናት እንደሚያስፈልገው አምናለሁ። ሳያገቡም እያረጁ የሄዱ ወንዶችና ሴቶች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

አባቶቻችንና እናቶቻችን 40 እና 50 ዓመት ተጋብተው እንዳልኖሩ ሁሉ ይህን ግንጥል ባሕል በመውሰድ በተጋቡ በአመታቸው የሚፋቱ ሞልተዋል። በርካታ ምሑራንም የዚህ ችግር በሥርዓተ-ማኅበሩ የሚታየው ሁለንተናዊ ንጥልነት (Allienation)፣ የቁሳቁስ ግብስብስነት (Excessive materialism)፣ የግብረ ሠናይ (Welfare) መስፋፋት፣ በማንኛውም ሁኔታ የምርጫ መብዛት (Availability of choice)፣ ግለኝነት (individualism) በወሲብ አለመጣጣምና የባህል መጥፋት (Lack of culture) ናቸው ይላሉ። ስለሆነም ካፒታሊዝም ከመቶ አመት በፊት የነበረውን ጠባይ አሻሽሎ በቁሳቁስና በገንዘብ ቢክሰንም በሌላ መልኩ ደግሞ ልባችንን ሠልቦ ሰብዓዊ ክብራችንና ርኅራኄያችንን በማዳሸቅ አደልድሞታል። ስለዚህም ነው ኅብረተሰባዊ ሳይንስ አንፃር ሲመረምሩት በርካታ ጠቢባን ይህ ኅብረተሰብ ከዚህ የተሻለ ነው የማይሉት ምርጫውን ላንተ ትቼ ስለአሜሪካ አጠቃላይ ሁኔታ ሌላ ጊዜ እመለስበታለሁና ሌሎች ይግለጡ በተቸባቸው ላይ ደግሞ ቁም ነገር ናቸው የምላቸውን ላክልበት። እንዳይሰለችህ አንዳንዴ ማንበቡን ቆም አድርገህ ብታንጎራጉር መልካም ነው። በኋላ ትመለስበታለህ።

እንደሰማኸው የአድዋን የድል በዓል በአሜሪካ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ሕዝባችን በመሰባሰብ በታላቅ ድምቀት አክብሮታል። እንደአባቶቻችን ደፋሮችና ጀግኖች ባንሆንም ያስተላለፉልንን እንቁ የታሪክ ቅርስ ለልጆቻችንና ለዚህም የሀገሪቱ ዜጎች አስተምረናል። አብዛኛው ሕዝባችን በሚያስገርም ሁኔታ አንድነቱንና ፍቅሩን ሲገልፅ በታሪኩም ሲኩራ እጅግ በጣም ጥቂትና የጭላዳ ጭንቅላት ያላቸው ደግሞ ሰበብ አስባብ በመደርደር "እነ እገሌ ካዘጋጁት ወደዚያ አንሄድም፣ እኛ መቼ ሰማን፣ ከእነዚህ እንክትክቶች ምን ትምህርት ይገኛል" በማለት ያንቋሸሹም አልጠፉም። እነዚህ ግለሰቦች ሽሚዝ ለብሰው ቢሄዱም እንደጠጣ የሚሊዮን ዓመታቸውን ዝግመተ-ለውጥ ያልጨረሱ ስለሚመስሉና ለሚጣርለት የጋራ ግምባር የጠላት መጠቀሚያ ስለሚሆኑ መቼም አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማምና እነርሱንም ለማስተማር ከፍተኛ ጥረት መደረግ አለበት። የአድዋው ድል አስተማሪና ወታደራዊ ቀያሽ(Military strategist) ሆኖ ሳለ ከኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ብራናቸውን ያገኙ ይመስል "ከእነዚህ ምን ትምህርት ይገኛል" በማለት ታሪክን ሳይገባቸው የሚያንቋሽሹ ግለሰቦች ወደፊት በሕዝብ መጠየቅ እንዳለባቸው ይሰማኛል። የኢትዮጵያዊነትንና የፓንአፍሪቃዊነትን ታሪክ የሚያጣጥሉ የኅብረተሰባችንን መሪዎች የሚንቁ የአሮጌ ዕቃ ሽያጭ(yard sale) አለ ሲሉአቸውና የአውሮጳውያን የጌታችን ልደት (Christmas) በዓል እዚህ ቤተክርስቲያን ይከበራል ሲሉአቸው ቀይ መብራት እየጣሱ የሚቻኮሉ ቆዳቸው ጥቁር ግን የአንጎላቸው አስተሳሰብ የነጣና የገረጣ ከእኛ በላይ ሀቀኛ ክርስቲያን ላሣር ነው የሚሉ ለማየት እንኳ የሚያቅለሸልሹም አሉ። እነዚህን ከጠላት ነጥሎ መመልከቱ ያስቸግራል። በአንፃሩም ኮሚኒቲን፣ አብያተክርስትያናትንና ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን በመገንባት የ10 እና የ15 ዓመት መራራ ትግል ያደረጉ፣ ለጋራ ግምባር የሚታገሉ፣ የተሸረበውን የዘረኝነት አደጋና ሀገሪቱ ያለችበትን ጥቃት ለመከላከል ሌት ተቀን የሚሠሩ፣ የወገኖቻቸውንና የሀገራቸውን ክብር በሚመለከት ለልጆቻቸውና ለቤተሰቦቻቸው ከሚሰጡበት ጊዜ ቆርሰው ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን የሚከሰክሱ፣ እነርሱም አናሳ ሆነው ለአናሳ ወገኖች (Minorities) በአሜሪካ የሥርዓተ-ማኅበሩን ሕግ በመጠቀም የሚፋለሙ፣ ለሀገር ጉዳይ ከሥራቸው በመቅረት በነጭ ግልምጫ የሚገረፉ፣ እነርሱ ቀድመው ተሸፋፍኖ የሚመጣውን ሤራ ሁሉ የሚያከሽፉ፣ "አካፋን አካፋ" በማለት ወገን መስለው በኅበረተሰባችን ውስጥ መርዝ የሚረጩትን መሀል አገር አደግ ተገንጣይ የነቁ ከረከሮዎችን የሚያሳፍሩ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች ሥፍር ቁጥር የላቸውም። በአሜሪካም በካናዳም ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ነው። ወርቃየሁ! ዛሬ ሕዝባችን አንገቱን የደፋ ቢመስልም ቆራጥነቱንና ኢትዮጵያዊ ስሜቱን ስታይ ደስታ ይሰማሃል። ሌላ አሰስ ገሠሥ ወሬ ሲኖር ጆሮአቸው እንደ ራዳር አንቴና የሚቀናና በእርግጥም ይግለጡ እንዳለው ሠርግና ለቅሶ ሲኖር ተኳኩለው የሚመጡ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርገው ሀገራቸውን የረሱ ቁጥራቸው ጥቂት ይሁን እንጂ በየአስቴቱ ይገኛሉ።

ከአዲስ መጤ ኃይማኖት ተከታዮችም ሀገር ወዳድ ዜጎች ቢኖሩም ጥቂቱ ደግሞ የመሠርሠሪያ ድጅኖውን አስልቶ በገለልተኝነት "የዘላለም ሕይወትን" በመስበክ በትግሉ ላይ ውኃ የሚደፋ በብዙ ልሳን የሚቀባዥር ቀያፋ ሞልቷል። "ያስፈለገኝን እምነት መከተል እችላለሁ፤ ይህ አሜሪካ ነው (This is America)" በማለት እርሱ ያልታገለለትን ሰብዓዊና ሕጋዊ መብት ከሰማይ እንደመጣ አድርጎ የሚናገርና አሜሪካኖችም ስለሀገራቸው እንደማይቆረቆሩና እንደማይቃጠሉ አድርጎ የሚያቀርብ የድንጋይ ዘመን ወጠምሻ ጥንቸል ታገኛለህ። ወርቃየሁ! እዚህ ላይ ስለአሜሪካኖች ሀገር ወዳድነት ትንሽ ሃሳብ ልጨምር። በአሜሪካ የሐ ይማኖት መሪ እንኳ ሳይቀር በሀገር ነክና በፖለቲካ ጉዳይ እንደኛው ሰዱቃዊ ገለልተኛ አይደለም። ምናልባት ታስታውስ እንደሆነ ከሳዳም ሁሴን ጋር በተደረገው ጦርነት አብያተ-ክርስትያናት

እንኳ ሳይቀሩ ያበሩት ከወገናቸውና ከመንግሥታቸው ጋር ነው። የናዝሬቱን እየሱስ ታጋይና ቆራጥ ዐብዮታዊ ነፃ አውጪ (Liberator) እንዳልሆነና ባሮችን ወይም የእሥራኤል ስደተኞችን ወደ አርነት ለማውጣት እንዳለፋ አድርገው የሚያቀርቡ የሐዲስ ኪዳንንም መልዕክት በገለልተኝነት ገፅታው (Neutral-ist) የሚያስተምሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን "ቅዱሳን" በአሜሪካ ታገኛለህ። የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ብቸኛ መልዕክት በሰው ልጆች ኃጢአት ላይ ተንተርሶ የአዳምን ልጅ ሁሉ ነፃ ለማውጣትና በተጨማሪም ድሆችንና ግፉዓንን በመደገፍ ወይም በመምረጥ (PREFERENTIAL OPTION FOR THE POOR) ፍትሕን ለመመሥረት መታገል እንዳልሆነ አድርገው የሚሰብኩ የእነርሱ ሰላም ብቻ እንዳይናጋ ራሳቸውን ኃጢአተኛ ነው ከሚሉት ኅብረተሰብ አግልለው የሚኖሩ "ብፁአን" ቁጥራቸው እየጨመረ ነው። ኃጢአት ግለሰባዊ ብቻ እንደሆነና ቀስ በቀስ ግለሰብን በመለወጥ ፍትሕን እናመጣለን የሚሉ ነገር ግን በምድራችን ጎልቶ የሚታየውን አውሮጳውያንና ምዕራቡ ዓለም የፈጠሩትን መዋቅራዊ ኃጢአት (STRUCTURAL OR INSTITUTIONAL SIN) ለመለወጥ የማያስተምሩ የዋህ ምዕመናን በአሜሪካ ታገኛለህ። ሌላው ቀርቶ እንደዚህ ለመፃፍ መብት የሰጠኝ ኅብረተሰብ ውስጥ በመሳተፍ የኅብረተሰቡን ችግር ለመፍታት በሚደረጉ ዴሞክራሲያዊ ውይይቶች እንኳ ለመሥራት ከቶ አይቃጣቸውም። ከወያኔና ከነጭ ጌታው የስለላ መረብ እንደመቅኑን እየተተመነ በኢርቱዕ መንገድ የሚረጭለትን ስሌተ-ውዥንብር (DISINFORMATION) የሚያሰራጭ አንዳንድ ያልጠረጠረ የዋህ ምሑርም ታገኛለህ። አየህ ወርቃየሁ እውነቱን ተናግሮ የመሸበትን ማደርን የመሰለ ነገር የለም። በእርግጥም ለጋራ ግምባር (UNITED FRONT) አንደኛው ችግር የዚህ ዓይነቱ ባዶነትና ጨለምተኝነት (Nihilism & Pessimism) ናቸው። በተለይም ብዙዎቻችን ከ10 ዓመት በፊት የመጣነው ዕድሜያችን እየገፋ ነው። ጊዜ በገፋ ቁጥር የመቃብር ስበት (gravity) እየጎተተን ስለሆነ የምንችለውን አበርክተን ለማለፍ እንደምንጥር ከሁሉም መረዳት ትችላለህ። ባዶነትን ወይም ጨለምተኝነትን ሳይታከቱ መታገል የጋራ ግምባር በአስቸኳይ እንዲመሠረት አስተዋፅኦ ያደርጋል። እንዳንጠናክር ያደረገን ፍርሐ ት ብቻ አይደለም። ወንድም ፀጋዬ ገብረመድህን አርእያ "ወኔና ሱሪ" በሚል ርዕስ የፃፈውን ታስታውሳለህ? የሚያስፈራው ሳይታከቱ ባዶነትን አለመታገል ነው። እየተሽመደመደ ለባላንጣ መሣሪያ ከሚሆን ወገን ይልቅ የለየለት ጠላት ይሻላል። የዚህንም ሥነልቦናዊ ሁኔታ መርምሮ መፍትሔ መሻት ለፍልሚያው መሳካት አንድ የምዕራፍ በር ይከፍታል። እንደዚህ ዓይነት ግለሰቦችን እንዴት ማወቅ ይቻላል ትለኝ ይሆናል። እኛ ኢትዮጵያውያን በሥልጣኔ ባንገፋም የሰውን ሁኔታ ገና ካነጋገሩ እናውቃለን። አባቶች ብልህ ናቸው፤ ሲተርቱ "እቋቋሙን አይተህ ጭብጦውን ቀማው" ይላሉ። ባያውቁት ነው እንጂ ዛሬ ኢትዮጵያዊነትን በማጣጣል የሀገር ስብሰባ ውይይቶችን ሳያውቁ በማንቋሸሽ የሚያዝረጠርጡ ጥቂት ወንድም ሆኑ ሴቶች የሚጎዱት የራሳቸውን ክብር ነው።

ይኸውልህ ወርቃየሁ ሌላው ደግሞ በቺካጎ የወያኔ ደጋፊዎችና አባላት በሰኔ 22, 1996 የአድዋን በዓል በእነርሱ ታሪክ ፀሐፊነትና ደራሲነት ባይሳካላቸውም ለማክበር ሞክረዋል። ምኒሊክን ከአድዋ ታሪክ ነጥለው ለማሳየት ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም። አንዱ የክብር እንግዳ የመለስ ዜናዊ አምባሳደር በዋሽንግተን ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ነው። እኛማ ለነጩም ለጥቁሩም ሁኔታውን አስረድተናል። ነገሩ "አድዋን ሲያነሱ ምኒሊክን አይርሱ" ነውና የኢየሱስን ተጋድሎ ከሐ ዲስኪዳን የወንጌል ታሪክ ለመነጠል እንደማይቻል ሁሉ እምዬ ምኒሊክንም ከጥቁር ሕዝቦች የትግል ታሪክና ከዝነኛው የአድዋ ድል ማንም ሊገነጥለው አይችልም። ባይገርምህ ብዙውን የአድዋ ታሪክ የፃፉት አውሮጳውያን ስለሆኑ ዓይናቸውን በጨው ታጥበው የወያኔን የታሪክ ማውገርገር ለመቀበል አይቃጣቸውም፤ ለጊዜው ምዕራቡ ዓለም የወያኔን ፖሊሲ ቢደግፍም በሌላ በኩል ደግሞ ታሪክን የማይሸፍጡ በርካታ የነጭ ፀሐ ፊዎችአሉ። እነዚህም ራሽ ሊምቦና ፓት ቢውካንን የመሳሰሉትን የራሳቸውን ሀገር በቀል ዘረኞች ወጥረው የያዙ ዴሞክራትና ሰብዓዊ አሜሪካውያኖች ናቸው። በመጨረሻም በተባበረ ደብዳቤና በተቃውሞ ድምፅ የቺካጎው የወያኔ የአድዋ በዓል እንደጠበቁት ሳይሳካላቸው ቀርቷል። አንዳንዶች ተናጋሪዎችም ተቃውሞው በማየሉ በመሸበር ራሳቸውን አግልለዋል። የዚህ ዓይነቱ ትብብር ሁሉም ለሚፈልገው የጋራ ግምባር በር እንደሚከፍት አንጠራጠርም። ብቻ እናንተ ጠንክሩ፤ ሁኔታው የጨለመ ቢመስልም መንጋቱ አይቀርም። ከጨለማ የበለጠ የከፋው ግን የአእምሮ ባዶነትና ግዴለሽነት ነው። ተስፋና የመንፈስ ጥንካሬ በለመለመ ቁጥር ብርሃን ይሠርፃል፤ ታሪክም እንደገና ይሠራል። ወርቃየሁ ነገሬን ከመቋጨቴ በፊት ባዶውንና ሀገር ወዳዱን በሚመለከት ትንሽ ሥንኝ ላውርድልህ። አየህ መቼም አንዳንዴ ግጥም ተገጥሞ እስከስታ ካልተወረደ ስሜትም አይገልም፤ ወኔም ይሸነፋል። መቼም ወኔህ ሲነሽጥህ ቼ በለውን ሳታንጎራጉር የምትቀር አይመስለኝም። የሆኖ ሆኖ በል እንግዲህ ያገርህን ዘፈን እየዘፈንክ በለመድካት ብዕርህ ፊደሎችን እያቀጣጠልክ እንደሥልክ ሽቦ ባጠላለፍካቸው ሐረጎችህ በሕያውነትህ አውጋን።

## ስማ በለው!

ስማ!
ሀገር ሲቃጠል ያልሸተተህ የሠርንህ ሥር የተረታ
እንጎልህ ዝጎ የጨጨበ ሰውነትህ ያልበረታ
ይብላኝ እንጂ እኔ ለአንተ
ሳይሞት በቁሙ ለሞተ።
ደምህ እንኳ ለብ ለማይል በዚህ የጭጋግ ሞቅታ
ሥጋህ ገንትሮ የማይገነፍል ወላፈኑ የማይማታ
ቃልኪዳንህን ያፈረስክ የእናት ያባትህን ስሞታ፤
ስማ!
የትግሌ ዝናብ እያባራም የእኔ ድርሻ የእኔ ፋንታ
እንኳን ለሰው ልጅና የኃጢአት ውጤት ከርታታ
ለሽለቆ ዝንጀሮ ለደኑ ለኮረብታ
እሸሼ ገዳሜ እስኪል ጦጣ እስኪወርድ እስክስታ
ጎራዴ ማረሻ ሆኖ እስኪወጣ ጡረታ
ዝግመተ ለውጡን አገባዶ ጉሬዛ ክራር እስኪመታ!!

ቸር ይግጠመን
ገብርዬ ከአትላንታ ጆርጅያ

# ሀናና ብንያም ሱቅ

# H & B SHOP

ጤፍ ዱቄት
በሶ
እልበት
ቡና
በርበሬ
ሚጥሚጣ
ሽሮ
ቅመም በያይነቱ

በተጨማሪ
የቪዲዮ ካሴቶች
የቴፕ ካሴቶች
የተለያዩ መጽሔቶችና
መጽሐፍት

የተለያዩ የአገር ባህል
ልብሶችም እንሸጣለን።

**ወለላ ወርቁ**
**WOLELA WORKU**

## የምግብ ክፍላችን
## ጥብስ፣
## ክትፎና
## ጐረድ ጐረድ
## ዘወትር ያቀርባል።
## ጎብኙን

ቆንጆ ጤፍ እንጀራም እንሸጣለን
በተጨማሪ ለሠርግ፣ ለቀለበት፣
ለክርስትናና ለመሳሰሉት ዝግጅቶች
በትዕዛዝ እንጀራ እናዘጋጃለን።

LEMO SERVICE
ለሠርግና ለልዩ ዝግጅት
የሌመዚን አገልግሎትም
እንሰጣለን።
1-800-679-1816
Pager- 738-7783
(770)481-2306

431 North Indian Creek Rd Suite E
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)296-2766

# ከ አ ን ባ ቢ ያ ን

## "እርስ በእርሳችን እንዋደድ!!"

የሺመቤት - ከሳንዲያጎ

ላንዳፍታዎች እንደምን ከረማችሁ? እኔ ከወዲሁ ቸሩ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ለመሆኑ የዘንድሮው summer እንዴት ተያይዛችሁታል? እኛ ጋ California የሙቁቱ ነገር ልነግርህ አልችልም። በደህናውም ጊዜ በስነስርአቱ ልብሳቸውን አይለብሱም። አሁንማ ሴቷ በጡት መያዣና በፓንት ብቻ ስትሄድ ወንዱ ደግሞ በቁምጣ መንዝ ከጀመሩ ሁለት ወራት ተቆጥረዋል። ሌላው ደግሞ የሚያስገርምህ በወንዱ ጡንቻ ላይ የሚሳሉት "ታቱ" ስታይ ሳትገረም አትቀርም። በዚህ ርዕስ ላይ ሌላ ጊዜ በሰፊው እመለሳለሁኝና ወደ ቁም ነገሬ ልመለስ።

ባለፈው እትማችሁ ላይ "በዴንቨር በግፍ የተባረሩ ክርስቲያኖች ተፈረደላቸው" የሚለውን ዜና አንብቤ በጣም ተገረምኩኝ። እውነት ትዘገይ እንጂ ህያው የምትሆንበት ቀን አለ። ዴን ቨሮች እንኳን ደስ አላችሁ። እንደዚህ ዓይነቱ ፈተና እናንተ ጋ ብቻ አይደለም የተከሰተው በእንደዚሁ ዓይነት ፈተና ያለፉትም በፈተናውም ላይ ያሉትን በትንሹ እንያቸው። በአትላንታ፣ በሳንዲያጎ፣ በሎሳንጀለስ ወዘተ ሁሉ ተከስተዋል። እንዲሁም አሁን በቅርቡ በከፍተኛ ፈተና ላይ ያለችው "የሳኖዜ የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን" ናት። እባካችሁ ክርስቲያን የሆንን ሁሉ በፀሎታችን እናስባቸው። ባይገርማችሁ ደግሞ ሁለት ቤተክርስቲያን እንዲሆን ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት ህዝቡ ሳይሆን የመፅ ሐፉን ቃል እናውቃለን፣ የቤተክርስቲያን ደንብና ስርአት እናውቃለን የሚሉ ሰዎች ናቸው።

የመፅሐ ፍ ቅዱስቃል የሚለው "እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ" መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ እሱ እኛን እንደወደደን እኛም እርስ በእርሳችን እንድንዋደድ ነውና። እባካችሁ በአንዲት እናት ኢትዮጵያ ማህፀን ውስጥ ሆነን እድገን ዛሬ በቀውጢው ሰአት የኤርትራ ቤተክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መባባሉ አንሶን የሸዋ አማራ፣ የመሀል የዳር አማራ እያልን ለምን ህዝቡን እንከፋፍላለን? ከቶ እግዚያብሔርን እንፈራምን? ለምን የዘር ቆጠራውን ትተን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ብለን በአንዲት ቤተክርስቲያን ውስጥ በፍቅር፣ በሰላም፣ በመተሳሰብና በመደጋገፍ ህዝቡ ወደቤተክርስቲያን የሚመጣበትን መንገድ፣ የራስ የሆነ ቤተክርስቲያን በመተባበር መግዛት፣ እንዲሁም በስደት አለም የተወለዱትን ህፃናት የራሳቸው የሆነ ፊደልና ባህል እንዳላቸው የሚያጠኑበት ት/ቤት መክፈት የመሳሰሉትን ብናደርግ። ያለነው በሰለጠነው አለም ያውም በአሜሪካ ውስጥ ሆነን ለእድገት ብናስብ ይሻለናል። እውነተኛውን የእግዚያብሔር መንገድ እንከተል። ጌታችን ለሐዋርያቱ በጎቹን ጠብቁ ብሎ ነበር። ስንቶቻችን ነን በጎቹን የጠበቅነው? ሌሎቹ ደግሞ የሁለቱንም ጭቅጭቅ አንሰማም በማለት ቤተክርስቲያን እርግፍ አድርገው የተዉና ወደ ሌላው ሃይማኖት የሄዱ ቁጥራቸው ቀላል አይምሰላችሁ። በጎቹ በግፍ ተበትነዋል። እባካችሁ ክርስቲያኖች ፀሎታችሁ ሁሉ ለግላችሁ ብቻ መሆኑ ይብቃና ለአገር፣ ለወገን፣ ፈተናው ለበዛባት ቤተክርስቲያናችንም ይሁን። የኢትዮጵያዊነታችን ታሪካችን ያለው ከተዋህዶ ቤተክርስቲያናችን ጓዳ ናትና። ቤተክርስቲያናችንን አጣን ማለት ባህላችንን አጣን ማለት ነውና እንንከባከባት፣ እንጠብቃት። የመንደር እቁብ ወይም ማህበር ይመስል በአንድ ስቴት ሶስት ማርያም ወይንም ገብርኤል ከማለት አንዲት የኢትዮጵያዊያን ቤተክርስቲያን መስርተን በእሷ ጥላ ስር እንኑር። ቸርነቱና ምህረቱ የማያልቀው ቸሩ እግዚያብሔር የቀናውን ልቦና ያድለን። አሜን።

ህያው እግዚያብሔር በነብዩ እንባቆም አድሮ በምዕ. 1 ቁጥር 5 ላይ *"እናንተ የምትንቁ ሆይ አንድ ቢተርከላችሁ እንኳን የማታምኑትን ስራ በዘመናችሁ እሰራለሁና እዩም፣ ተመልከቱም፣ ተደነቁም"* ብሎአል። እምባቆም በበኩሉ *"እኔ ሰምቻለሁ ልቤም ደነገጠብኝ ከድምፅ የተነሳ ከንፈሮቼም ተንቀጠቀጡ፤ መንቀጥቀጥ ወደ አጥንቶቼ ውስጥ ገባ በስፍራዬ ሆኜ ተናወጥሁኝ፣ በሚያስጠንቁኝ ህዝብ ላይ እስኪመጣ ድረስ የመከራን ቀን ዝም ብዬ፤ እጠብቃለሁ። ምንም እንኳን በለስ ባታፈራ፤ በወይን ሀረግ ፍሬ ባይገኝ፤ የወይራ ስራ ቢጎድል፤ እርሻዎችም መብልን ባይሰጡ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፤ ላሞችም በጋጥ ውስጥ ባይገኙ፤ እኔ ግን በእግዚያብሔር ደስ ይለኛል። ጌታ እግዚያብሔር ሃይሌ ነው።"* እንዳለ እኛንም በሃይማኖት በምግባር በፍቅር በአንድነት ያፅናን። አሜን። ወስብሐት ለእግዚያብሔር!!

---

## አብረኸት

ይድረስ ለላንዳፍታ አዘጋጅ! በቅድሚያ ከፍ ያለ ሰላምታዬን እያስቀደምኩኝ ምንም እንኳን የመጀመሪያ የዝግጅታችሁ ተሳታፊ ብሆንም ላንዳፍታ የተሰኘውን መጽሄት ገዝቼ ማንበብ ከጀመርኩኝ ግን ሁለት አመት ሆኖኛል። ታዲያ ከማንበብ አልፌ ለመፃፍ የተገደድኩት ከመጽሄቱ ካገኘሁት አንዱ "አዳምና ሔዋን" በሚል አርዕስት (ዓምድ) እውነተኛ ታሪክ ነው ተብሎ የቀረበው ነው። በክፍል 12 ላይ እንዳነበብኩት ከሆነ የብዕር ስሟ አብረኸት፣ የትውልድ አገርዋ ኤርትራዊ፣ ዕድገትዋ ደግሞ አ/አበባ ሆና ይህን የመሰለ ታሪክ በስደት ያሳለፈችው ፍቅር አዘል ፅሁፍ ሲታይ በእርግጥ አንድ በኩል የሚያሳዝን ሲሆን በሌላ በኩል ግን ፍቅር ተብሎ በተለያዩ ጾታዎች ላይ የሚመሰረት የተፈጥሮ ተግባሩን ሲጀምር ስደት ወይም ቦታ ለይቶ ሳይሆን አምሳያን ተገናኝተው በየትም ይሁን በየት የሚያሳልፉት የህይወት ፀጋ መሆኑን ለማንኛችንም ግልፅ ነው።

ፍቅር ይህን የመሰለ ቅርጽና ምስል ካለው በማንኛውም የሰው ልጅ የሚደረግ ሆኖ፤ አብረኸት በዚሁ መጽሄት ያሳለፈችው ወይም በማሳለፍ ላይ ያለችው የፍቅር ታሪክ በተለይ ሴት ልጅ ሆና ያውም በዚህ ቅጥ የለሽ አገር ውስጥ ያላትን የውስጥ ስሜቷ ካለአርስዋና ሰይፉ በስተቀር ሌላ የሚያውቅላት የሌለ መሆኑን እየተረዳች ለፍቅር ጓደኝነት በሌላ ሰው መጠየቅዋ ብን ብሎ ያሳዘናት መሆኑን ስትገልፅ ፅሁፉ ወደ ሌላ አዝማሚያ ብሎም ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ከማድረግ በስተቀር ሰዎች ከዚሁ ትምህርት አግኝተው ለጠቀሜታ ይሆናል ተብሎ ግምት የሚሰጥበት አይነት አይደለም።

በጠያቂውም ክፍል ቢሆን የሰው ልጅ ለፍቅር ያለውን ዕውነተኛ ስሜት ለመግለፅ ካሳለፈው ይሁን አሁን ካለው ደረጃ በመነሳሳት አግባብ ያለው ጥያቄ ጠይቆ መልስ ማግኘት አስነዋሪ ባይሆንም አስነዋሪነቱ መባል ከማይገባው ከዘር ከሀይማኖት ከቀለም ነው ብሎ ለይቶ ማስቀመጥ ፍቅርን ሳይሆን ጥላቻን መግዛት መሰለኝ። በተለይ አብረኸት ያላትን ውስጣዊ ስሜት ለማለት የፈለገችው ምን እንደሆነ ግልፅ ያለ ባለመሆኑ የተመሰረተውን ፍቅር የተፈጥሮ ፀጋውን በቃላት አውጥቶ ማስረዳት ያለመቻል መሆኑን ያስረዳል።

ስለዚህ ማለት የፈለግኩት በአምዳችሁ የሚፃፈው በተለይ ፍቅርን በሚመለከት ሰዎች ያላቸውን ስሜት ሲገልፁ ለማለት የፈለጉት ምን እንደሆነ እናንተም እንድትተባበሩዋቸው ሲሆን ይህ ፅሁፌ ግን ማንንም የሚነካ ያለመሆኑን በቅድሚያ እገልፃለሁ።

ተስፋ ተሻለ - ከዳላስ ቴክሳስ

---

## አማርኛ ወይስ "እማ-እንግሊዝኛ"

ከውሂብ ጥሩነህ

የ"ላንዳፍታ" አዘጋጆች በመጀመሪያ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ! የ"ፀደይ" መጽሔት በአንድ ወቅት እትሙ "እማ-እንግሊዘኛን" በተመለከተ ያወጣውን ቀልድ ለበስ ጽሑፍ የአማርኛ ፅሑፍ ለሚያቀርቡና አማርኛና እንግሊዝኛን ካልቀላቀሉ ፍንክች ለማይሉ ፀ ሐፊዎች ጥሩ ምክርን ያዘለ ነው። ሁለት በምንም ተዓምር የማይገናኙ ቋንቋዎችን አንድ ላይ እየቀላቀሉ መፃፍ እየተለመደ የመጣ አዲስ ፈሊጥ መሆኑን ልብ ብላችሁልኛል? በአማርኛ የቀረበ ፅሑፍ ውስጥ የእንግሊዝኛ ቃላትን እያስገቡ መፃፍ የፅሑፉን ውበት መቀነስ ብቻ ሳይሆን እንግሊዝኛቸው ብዙም የማያንደራድራቸው አንባቢዎች "የራሳቸው ጉዳይ" የሚል አዲስ ፈሊጥ ይመስላል። ፅሑፉን ወይ እንዳለ በእንግሊዝኛ መፃፍ ወይም ደግሞ እንዳለ በአማርኛ ማቅረብ አግባብ አይመስላችሁም? ዋናው ጥያቄ አንባቢው እንግሊዝኛ ያነባል ወይ? ሳይሆን ፀሐ ፊውሃሳቡን የሚገልፁለት የአማርኛ ቃላት እያሉለት ዘሎ እንግሊዝኛ መጠቀም ለምን አስፈለገው ነው? ፅሑፋቸው ውስጥ የእንግሊዝኛ ቃላት እንደ ማጣፈጫ ቅመም ካልጨመሩ የማይሆንላቸው ፀሐፊዎች ዓላማቸው ምን እንደሆነ ቢያስረዱን መልካም ነው! በአማርኛ!! "ላንዳፍታ" መጽሔት ላይ ሰይፉ ሙኩሪያ የሚያቀርባቸው ፅሑፎች ከበድ ያለ ቁም ነገር ማዘላቸው ፀሐፊውን የሚያስመሰግኑት ቢሆኑም እንግሊዝኛ እየቀላቀለ ስለሚፅፍ ግን የፅሑፎቹን ውበት ገፎአቸው ይታያል። ምሳሌ ልስጥ! በቅርቡ በሚያዝያ/ግንቦት 1988) የወጣው የ"ላንዳፍታ" እትም ላይ ሰይፉ "ታሪክ ከዜናዎች ሲፈልቅ" በሚል ርዕስ ያቀረበው ፅሑፍ የያዘው ቁምነገር ባያከራክርም አብሮ ያስተናገዳቸው የ"እማ-እንግሊዝኛ" ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች ብዛትም ለጥቅስ የሚበቃ ነው። ለምሳሌ በገፅ 29 ላይ "... ኢትዮጵያ ከImport/Export ታገኘው የነበረው ..." የሚል ዓረፍተ ነገር ተቀምጠዋል። "ኢትዮጵያ በአስመጭና ላኪነት(ጥሬ ዕቃዎችን በመላክና በማስመጣት)" ብሎ ዓረፍተ ነገሩን ሙሉ በሙሉ አማርኛ ማድረግ ለምን እንዳልተቻለ አልገባኝም! "Import/Export" ምን ማለት እንደሆና የማያውቅ አንባቢ ኢትዮጵያ ምን ከምን እንዳገኘች ግራ ገብቶት ጥርሱን ሲያፋጭ አይታያችሁም? እንደገና እዚሁ ገፅ ላይ "በመካከለኛው ምስራቅና በOAU ውስጣዊ ሥራዎች ተጣድፈዋል" የሚል ዓረፍተ ነገር አለ። "OAU" የእንግሊዝኛ ፊደላትን የያዘ ቃል እንደሆነ በግልፅ የሚታይ ነገር ነው። ነገር ግን ይሄው ቃል በሁለት መንገድ በአማርኛ መፃፍ ይችል ነበር። "ኦ.ኤ.ዩ." ቢባል ቢያንስ ፊደላቱ የአማርኛ ናቸው! ወይም ደግሞ በትክክለኛ የአማርኛ አጠራሩ "አ.አ.ድ." ማለትም "የአፍሪካ አንድነት ድርጅት" ተብሎ ዓረፍተ ነገሩን ለአማርኛ አንባቢዎች ግልፅ ማድረግ ይቻላል።

ሌላም "All history is current events እንደሚባለው . . ." የሚል አረፍተ ነገር እዛው ገፅ ላይ ይታያል። ይሄንን ዓረፍተ ነገር "ታሪክ ሁሉ ወቅታዊ ዜና ነው" ብሎ መተርጎምና ወደ አማርኛ መቀየር አይቻልም ነበር ወይ? ከሁሉም ፅሑፉ እንግሊዝኛ ለሚችሉ አንባቢዎች ብቻ የተዘጋጀ እንደሆነ የሚያመለክተው (የሚያስመስለው) በገፅ 31 ላይ ሰባት መስመር የፈጀውና በእንግሊዝኛ የተፃፈው ጥቅስ ነው። ጥቅሱ አንድም ቦታ በቀጥታ ወደ አማርኛ ሳይተረጎም ፀሐፊው "እንደተባለውም..." ብሎ ፅሑፉን ይቀጥላል። እንግሊዝኛ ባዳ የሆነባቸውን ሰዎች ፀሐ ፊወየዘነጋቸው ይመስላል። በፅሑፉ ውስጥ በቋሚነት የሚታዩት የእንግሊዝኛ ቃላት የወራት ስሞች የሚገልፁት ናቸው። "March" የሚለው ቃል በአማርኛ ፊደላት "ማርች" "April" - "ኤፕሪል" ተብለው መፃፍ አይችሉም ወይ? (የካቲት፣ መጋቢት፣ ወዘተ ... ለማለት ከተቸገርን ማለቴ ነው!) መተርጎም ያለባቸው ቃላት ካሉ እንተርጉማቸው! በአማርኛ ትርጉማቸው የማይገኝ ቃላት ከሆኑ ቢያንስ የአማርኛ ፊደላትን ተጠቅመን እንዳሉ እናስቀምጣቸው። ለምሳሌ "White House" የሚሉት ቃላት "ነጭ ቤት" ብለን ብንተረጉማቸው ስሜት ላይሰጡን ይችላሉ። ያም ማለት ግን ቃላቱን እንዳሉ ለመፃፍ የግድ የእንግሊዝኛ ፊደላትን መጠቀም አለብን ማለት አይደለም። "ዋይት ሐ ውስ"የአማርኛ ቃላት ባይሆኑም ቢያንስ የአማርኛ ፊደላትን እንደያዙ የተፃፉ የእንግሊዝኛ ቃላት ናቸው!! ሁለት በመልክም በዘርም የማይገናኙ ቋንቋዎችን እየቀላቀሉ መፃፍ የስነፅሑፍን የተፈጥሮ ህግ ለመቀየር መሞከር ብቻ ሳይሆን ዋናው የፅሁፉ አካል የሆነውን ቋንቋ (አማርኛ!) አካለ ጎዶሎ ማስመሰል ይሆናል። እንግሊዝኛና አማርኛን ካልቀላቀልኩ እስከርቢቶዬ እሺ አይለኝም የሚሉ ፀሐ ፊዎችካሉ ከፅሑፎቻቸው ጋር አባሪ ሆኖ የሚታተም የፍቺ መዝገብ ያቅርቡልን!! ሰይፉ ያለ ገላጋይ እንደወረድኩብህ ይገባኛል። አንተስ ምን ሀ ሳብ አለህ? "ሁ ኬርስ?" እንደማትለኝ ተስፋ አደርጋለሁ!!!

# የ1996 ኦሎምፒክ በአትላንታ

## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሚሳተፉበት ውድድሮች ፕሮግራም

1ኛ **የሴቶች** 5,000 ሩጫ *መጀመሪያ* ዙር
July 26, 1996 4:30 PM - 11:00 PM
ኦሎምፒክ ስታዲየም

2ኛ **የወንዶች** 10,000 ሩጫ *መጀመሪያ* ዙር
July 26, 1996 4:30 PM - 11:00 PM
ኦሎምፒክ ስታዲየም

3ኛ **የሴቶች** 10,000 ሩጫ *መጀመሪያ* ዙር
July 27, 1996 5:30 PM - 10:30PM
ኦሎምፒክ ስታዲየም

4ኛ **የሴቶች** 5,000 ሩጫ የመጨረሻ ዙር
July 28, 1996 3:15 PM - 9:45 PM
ኦሎምፒክ ስታዲየም

5ኛ **የወንዶች** 10,000 ሩጫ የመጨረሻ ዙር
July 29, 1996 6:00 PM - 10:30 PM
ኦሎምፒክ ስታዲየም

6ኛ **የወንዶች** 5,000 ሩጫ የመጀመሪያ ዙር
July 31, 1996 5:15 PM -10:55 PM
ኦሎምፒክ ስታዲየም

7ኛ **የወንዶች** 5,000 ሩጫ የማጣሪያ ዙር
August 1, 1996 2:00 PM -9:40 PM
ኦሎምፒክ ስታዲየም

8ኛ **የሴቶች** 10,000 ሩጫ የመጨረሻ ዙር
August 2, 1996 5:00 PM - 10:10PM
ኦሎምፒክ ስታዲየም

9ኛ **የወንዶች** 5,000 ሩጫ የመጨረሻ ዙር
August 3, 1996 6:30 PM - 9:55 PM
ኦሎምፒክ ስታዲየም

10ኛ **ማራቶን** (መዝጊያ)
August 4, 1996 7:05 AM - 11:00 AM
ማብቂያው ኦሎምፒክ ስታዲየም



ፎቶ - ላንዳፍታ

## ስለ 1996 አትላንታ ኦሎምፒክስ ለጎብኚዎች ማስታወሻ

- በዘንድሮው ኦሎምፒክስ ከ2 ሚሊዮን ጎብኚ በላይ ይጠበቃል። የሎስ አንጀለሱና የባርሴሎናው ኦሎምፒክ ተሳትፎዎች በአንድ ላይ ተደምረው ይኼኛው ከዚያ በላይ እንደሚሆን ይገመታል። በቀን ከ400,000 እስከ 600,000 ሕዝብ በመሐል አትላንታ (ዳውንታውን)እንደሚንቀሳቀስ ይገመታል።

- 75 በመቶ የሚሆነው የኦሎምፒክ ዝግጅት የሚከናወነው በአትላንታ መሐል ከተማ (ዳውንታውን) 1.5 ማይል ሬዲየስ ውስጥ ነው። የሎስ አንጀለሱ በ30 ማይል ሬዲየስ ውስጥ ነበር። የሚገጥመውን መጨናነቅ ከወዲሁ መገመት ይቻላል።

- ወደ አትላንታ ለዝግጅቱ የሚመጡ እንግዶች 81% በመኪና፣ 19% ብቻ በአይሮፕላን እንደሆነ ተገምቷል። ከፍተኛ የሆነ የመኪና ማቆሚያ ችግር ይኖራል። የአትላንታ ኦሎምፒክ ኮሚቴ በዝግጅቱ ወቅት ሰዎች መኪናዎቻቸውን እንዳይጠቀሙ ምክር ሰጥቷል። ለዚሁ እንዲረዳ ብዙ አውቶቢሶችና ባቡሮች ተዘጋጅተዋል።

- በመሐል ከተማውና ከመሐል ከተማው ጋር የሚያገናኙ መንገዶች (connectors) ከጠዋቱ 7:30 AM እስከ ቀኑ 12:00 ድረስ ለመኪና ዝግ ናቸው።

- የባክሄድ አካባቢ ከቀኑ 11:00 AM እስከ ሌሊቱ 12:00 PM ድረስ የዓለም አቀፍ ፓርቲ ቦታ እንደሚሆን ተነግሯል።

# ኢትዮጵያውያን
# የኦሎምፒክ ጀግኖች



አበበ ቢቂላ



ማሞ ወልዴ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ባርሴሎና | 1992 | በሴቶች | 10,000 ሜትር ወርቅ - ደራርቱ ቱሉ |
| | | በወንዶች | 10,000 ሜትር መዳብ - አዲስ አበበ |
| | | | 5,000 ሜትር መዳብ - ፊጣ ባይሳ |
| በሞስኮ | 1980 | በወንዶች | 10,000 ሜትር ወርቅ - ምሩፅ ይፍጠር |
| | | | 5,000 ሜትር ወርቅ - ምሩፅ ይፍጠር |
| | | | 10,000 ሜትር መዳብ - መሐመድ ከድር |
| በሙኒክ | 1972 | በወንዶች | ማራቶን መዳብ - ማሞ ወልዴ |
| በሜክሲኮ ሲቲ | 1968 | በወንዶች | 10,000 ሜትር ብር - ማሞ ወልዴ |
| | | | ማራቶን ወርቅ - ማሞ ወልዴ |
| ቶኪዮ | 1964 | በወንዶች | ማራቶን ወርቅ - አበበ ቢቂላ |
| ሮም | 1960 | በወንዶች | ማራቶን ወርቅ - አበበ ቢቂላ |



ፎቶ - ላንዳፍታ

የአትላንታ ከተማ



የኦሎምፒክ መንደር

ፎቶ - ላንዳፍታ

# ዌልካም ዮል!

ከሰይፉ ሙኩሪያ

አሥር ሺህ አትሌቶች የሚሳተፉበት የዘንድሮው ኦሎምፒክ ዝግጅት ሽርጉድ እስካሁን አላበቃም። አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሀገሮች ባንዲራቸውን እያውለበለቡ ወደ አትላንታ በመጉረፍ ላይ ናቸው። የመላው ዓለም ሕዝብ መንፈሱንም ዓይኑንም የሚያሳርፍበት የአትላንታ ከተማ ተፀዳድታ ተኳኩላ ዓለማችንን ለማስተናገድ ቀርባለች። ነገሮች ተሳክተውላቸው እዚህ መምጣት ለተሳካላቸው ሁሉ "Welcome Yall" እንላለን። አትላንታ መምጣት ላልተሳካላቸው ቢሊዮን ሕዝቦች ደግሞ እዛው ከሚኖሩበት አ ገር ከተፍ እንደምንል (በቴሌቪዥን) ጥርጥር የለውም። በየብስም ሆነ በአየር፣ በኬብልም ሆነ በሳተላይት ... እናንተንም "Welcome Yall" እንላለን።

የዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ (IOC) "... has awarded the 1996 Olympic games to the city of ... Atlanta!! የሚል ምሥራች ካበሰሩን ሰዓት ጀምሮ ሠርገኛ እንደመጣበት ባለሟል ሽርጉድ ስንል ሁለት ዓመት ሆነን። በከተማችን ውስጥ የተካሄዱት የመንገድ፣ የህንፃ፣ የፓርክ፣ የስቴድዮም፣ የድልድይ፣ ... ሥራዎችን የምናውቀው እኛ ነን። የከተማው ነዋሪ የደረሰበት ውጣ ውረድ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። መንገድ ሲዘጋና ሲከፈት፣ የተከፈተው እንደገና ሲዘጋ፣ የአውራ ጎዳና ጠጋኝ መስሪያ ቤት በየመንገዱና በየድልድዩ የሚያቆሟቸው ልዩ ምልክቶች (ቢጫ ፕላስቲክ ፒራሚዶች፣ በርሜሎችና ብልጭ ድርግም የሚሉ ቀስቶች) መንገዳችንን ሲያጠቡና ሲያሰፉ፣ አንዳንዴም ሲዘጉ በየመንገዱ ተገትረንና ባላሰብነው መንገድ እንድንሄድ ተደርገን፣ ያሰብነው Exit ተዘግቶብን፣ ... ኧረ ምኑ ቅጡ! ለሁለት ዓመት መጉላላታችንን እወቁልን። ለናንተው ብለን!!

የዘንድሮው ዝግጅት ከቀድሞዎቹ የኦሎምፒክ ዝግጅቶች ለየት ያለ ታሪክ አለው። በመጀመሪያ ከባርሲሎናው (1992) ኦሎምፒክ በፊት የ198 8 ኦሎምፒክ አስተናጋጅነቱ የተሰጣት አሜሪካ (ሎስ አንጀለስ) ነበረች። የኦሎምፒክ አፍላቂነቷ የሚነገርላት ግሪክ አንድ መቶኛ ዓመቱ የሚከበርበትን ይህንን በዓል እንድታዘጋጅ ይደረጋል የሚል ሠፊ ተቀባይነት የነበረው ወሬ ሰፍኖ ነበር። በተጨማሪም ዝግጅቱ አሰልሶ እንደገና አሜሪካ ውስጥ ይካሄዳል ብሎ የገመተ ሰው መኖሩ ያጠራጥር ነበር። ሆኖም Bill Pane የሚባል የአትላንታ ሰው ሀሳቡን በማመንጨት ከልዩ ልዩ የጆርጂያ/አትላንታ ባለስልጣኖች ጋር በመተባበር ኦሎምፒክን አትላንታ ውስጥ ለማምጣት ጥረት መደረግ እንደተጀመረና የተለያዩ ዓለም አቀፍ ኮርፖሬሽኖችም (ለምሳሌ ኮካኮላ) በነገሩ ተስማምተው ታላቅ የፕሮፓጋንዳና የsellsmanship ዘመቻ አድርገው የIOC ልብ ሊያገኙ ችለዋል። ዝግጅቱ አትላንታ ውስጥ እንዲሆን IOC ያስተላለፈው ውሳኔ ግሪክን ማስቆጣቱ ግልፅ ሲሆን፣ ይህ ውሳኔ አንዳንድ የታሪክ ባለሙያዎችንም ቅር አሰኝቷል።

> የዘንድሮው ኦሎምፒክ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የኮርፖሬሽኖች ተሳትፎ ስለሚታይበት የኦሎምፒክ መንፈስ የንግድ ካባ እየለበሰ ነው የሚሉም አሉ። በዚህ መሰረት የዘንድሮው ኦሎምፒክ "ኮርፖሬት ኦሎምፒክ" የሚል ቅፅል መጠሪያ አግኝቷል።

ከዚህ ጋር የሚዛመድና ሰፋ ያለ ምክንያት መኖሩን የሚጠቁሙ ሰዎችም አሉ። እነዚህ ሰዎች የዘንድሮው ኦሎምፒክ አሰልሶ አሜሪካ ውስጥ እንዲካሄድ የተደረገው "የፖለቲካ ውሳኔ"ነት አለበት ይላሉ። ሶቭየት ህብረትና የሶሻሊስት ካምፕ ከፈራረሰ በኋላ ዓለም ላይ ሰፍኖ የነበረው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግርግር ቀስ በቀስ እየጠራ፣ እየተስተካከለና እየተደላደለ በመሄዱና በእነዚህም ሂደቶች ሳቢያ የአሜሪካ ብቸኛ ሱፐር ፓወርነት ፍጥጥ ብሎ ሊታይ የበቃበት ወቅት በመሆኑ ነው ይላሉ። በማያያዝም የኦሎምፒክ ዝግጅት ድፍን ዓለማችን ሥራዬ ብሎ የሚከታተለው በዓል በመሆኑ ይህንን መድረክ በመጠቀም አሜሪካኖቹ አገራቸውን፣ ፖለቲካቸውን፣ ኢኮኖሚያቸውን፣ ባህላቸውን፣ ሽቀጦቻቸውንና ላይፍ ስታይላቸውን ለሠፊው ዓለም የሚያስተዋውቁበትና የሚሸጡበት

መድረክ እንደሚሆን ይተነብያሉ።

ያም ሆነ ይህ የዘንድሮው ዝግጅት ሠፋ ያለ መሆኑን አይጠራጠሩ። አትላንታ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ንፁህ ከተማ ሆናለች። ማጋነን አይሁንና እንዳውም እስከዛሬ ካየኋቸው ታላላቅ ከተሞች ውስጥ አትላንታ የበለጠ ንፁህና ዘመናዊ ሜትሮፖሊታን ነች ሊባል ይቻላል። ይህ ዝግጅት ያልዳሰሰውና ያልቀየረው የከተማዋ ዲስትሪክት አለ ለማለት ያስቸግራል። የአሁኒቷ አትላንታ ከአሥር ዓመት በፊት ያልነበረች አዲስ አትላንታ መሆንዋን ነዋሪዎቿ ይናገራሉ። "ከዕኩለ ሌሊት በኋላ በአትላንታ ሀ ይዌይ መንዝ futuristic experience ነው" የሚሉ ሰዎች አሉ።

ለእንግዳዎቻችን ማሳወቅ የሚገባን የከተማው ቦታዎች አሉ። ለአስረሽ ምቺውና ለ"አላውቅላችሁም!" ፓርቲ በከሄድን(Buckhead) የመሠለ ቦታ የለም። ከዳውንታውን ስምንት ኪሎ ሜትር ከፍ ብሎ(ሰሜን) የሚገኘው Buckhead የፓርቲ ሰፈር ነው። ቡናቤት፣ ምግብ ቤት፣ መጠጥ ቤት፣ ዳንስ ቤት ... ለሁሉም የሚሆን ቦታ ነው። የእሥረሽ ምቺው ቦታ ነው! አትላንታ ውስጥ ደርሰው Buckheadን አለማየት "ወንጀል ነው" ይባላል። ከዛ በተረፈ ለአበሻ ግርግር የአበሾችን ቦታ የሚስተካከሉ ተቋሞች የሉም።
(በጽሑፉ መጨረሻ ላይ አድራሻቸውን ተመልከቱ)

ከዚህ የሚጨመር ቢኖር እዚህ እስከሆኑ ድረስ እንደምንም ብለው (Southern Cooking) ደቡቡ የሚታወቅባቸውን ምግቦች - (Fried chicken, Collard greens, BBQ Ribs, Corn bread, Ice Tea, Grits ... ወዘተ) እንዴ እንኳ ለመቅመስ ጥረት ያድርጉ።

የአትላንታ ከተማ ልዩ መልክ ይዛ ኦሎምፒክን በመጠባበቅ ላይ ነች። በመኪና ወይም በባቡር ካልመጡ በቀር መድረሻዎ Hartsfield International Airport ይሆናል። ይህ ዝባዝንኬ አይሮፕላን ማቢያ እንዳይመስልዎት። በአውሮፕላን ትራፊክ ከዓለም ሁለተኛ (ከቺካጎው ኦሄር ቀጥሎ)፣ በትልቅነትም እንዲሁ ሁለተኛ (ከዳላሱ ኤርፖርት ቀጥሎ) የሆነና በውስጡ ከ30 ሺህ በላይ የሚሆኑ ሠራተኞችን አቅፎ የያዘ ዘመናዊ ኤርፖርት ነው። 2ት ሚሊዮን እንግዶችን በጥቂት ጊዜ ቀኖች ውስጥ ሊቀበል ተዘጋጅቷል።

በብዙ ሚሊዮን ብር እድሳት የተደረገለትን ይህንን ኤርፖርት ወጣ ብለው መንዝ ሲጀምሩ "We are glad Georgia is on your mind: ... The Site of the 1996 Olypmic Games" ይላል የ'Welcome' ምልክቱ። አንድ መቶ ሜትር ያህል እንደተጓዙ 85 North የተባለው ሀ ይዌይ ውስጥ ይገባሉ። አንድ ሁለት ማይሎች እንደተጓዙ ልክ "Lakewood Fwy ..." የሚለውን ጽሁፍ እንዳለፉ ... በነጣጭ መስመሮች ያሸበረቀ፣ ሰባት መኪናዎችን በአንድ ጊዜ ጎን ለጎን መያዝ የሚችለው የድንጋይ ወንዝ (Highway) ፊት ለፊትዎ ተለጥጦ

## አዲሱ የኦሎምፒክ ስታዲዮም



ፎቶ - ላንዳፍታ

ያገኙታል። ይህ መንገድ የከተማዋን መሀል አቋርጠው የሚሄዱት Interstate 85(I-85) እና Interstate 75 (I-75) በአንድ የገጠሙበት ነው። ወደ ሰሜን ሰባት ወደ ደቡብ ሰባት በድምሩ 14 መኪናዎችን በመደዳ የሚያስተናግድ የድንጋይ ባህር ነው።

በተለጠጠው የድንጋይ ባህር ሲጓዙ ወደ ከተማዋ እየገቡ መሆኑን ይገንዘቡ። ጥሩ ዓይን ካለዎት ቀና ብለው ቢመለከቱ በረጃጅም ብረት ዘንጎች ላይ ቂጢጥ ያሉ የቴሌቭዥን ካሜራዎችን ያያሉ። ለእናንተም ለእኛም ደህንነት ተብሎ በከተማችን ዙሪያ የተሰቀሉ ኃይለኛ ጥራት ያላቸውና የታርጋ ቁጥር ማንበብ የሚችሉ ካሜራዎች ናቸው። ከፊት ለፊትዎ አሻግረው ሲመለከቱ ኮረብታማ ቦታ ላይ የሚታየው የድንጋይና የመስታወት ክምችት ... አትላንታ ከተማ ነች! አምስት ማይልስ ያህል ይቀርዎታል። EXIT 91 አጠገብ ሲደርሱ በስተቀኝ በኩል የሚታየው ለኦሎምፒክ ተብሎ የተሰራው ታላቁ ድግስ የሚጣልበት አዲሱ ስታዲዮም ነው። ከፊት ለፊቱ ደግሞ እስከዛሬ ድረስ የአትላንታ ብሬቭሥ ቤዝቦል ቲም የሚጫወትበት "Fulton County Stadium" ሲሆን ይህ የቤዝቦል ስቴድየም ዕድሜው አጭር ነው። ከኦሎምፒክ በኋላ እንዲፈርስ ተፈርዶበታል! አሁን ዳውንታውን ገብተዋል ማለት ነው። (ለበዓሉ ሲባል የዳውንታውን መንገዶች በሙሉ ለትራፊክ ዝግ ይሆናሉ ስለተባለ የእግር ጉዞ ሊኖር እንደሚችል መገንዘቡ ጥሩ ነው።)

ዳውንታውን ሳይገቡ በዛው ሀይዌይ ሆነው (I-85/I-75N) መጓዝ ቢቀጥሉ በስተግራ በኩል የከተማው ሰማይ ጠቀሶች ተደርድረው ያያሉ። አንድ ማይል ያህል እንደተጓዙ EXIT 100 ሲደርሱ በግራ በኩል ሁለት አዳዲስ የሸክላ ህንፃዎችን ያያሉ። እነዚህ ህንፃዎች የአትሌቶቹ ማረፊያ "Olypmic Village" የሚባለው ነው። አጠገቡ ድርሽ እንዳይሉ። ዙሪያውን በኮረንቲ አጥር የታጠረ መንደር ነውና!

እዚህ ላይ ዳውንታውን አልፈው ሚድታውን ደርሰዋል ማለት ነው። ጥቂት ሄድ እንዳሉ መንገዱ ለሁለት ይከፈላል። ጥንድ ሆነው ከተማዋን ያቋረጧት I-85 እና I-75 የተባሉት ሀይዌዮች ሲለያዩ ነው። በቀኝ የሚገነጠለው I-75 ሲሆን ይህ መንገድ በNewt Gingrich ቀበሌ አቋርጦ ወደ ቴኔሲ የሚወስድ ነው። በስተግራ የሚቀረው I-85 ሲሆን (Buckhead) በክሄድ የተባለውን የአሥረሽ ምቺው መንደርን አቋርጦ ወደ ሳውዝ ካሮላይና የሚወስድ ነው።

አትላንታ ውስጥ ዋና የሚባሉት አራት አውራ ጎዳናዎች (Highways) ናቸው። ሦስቱ ቀጥተኛ መንገዶች ሲሆኑ (Directional Highways) አንዱ ግን ከተማዋን ዙሪያ የሚዞር መነሻም መድረሻም የሌለው ክብ(100P) መንገድ ነው። ይህ I-285 ይባላል። በአሜሪካ ውስጥ ለሚገኙት አውራ ጎዳናዎች በተሰጠው ምድብ መሰረት ሦስት አሀዝ ያላቸው (ለምሳሌ I-285) ሀይዌዮች ዙሪያ ክብ የሚሄዱ ሲሆን፣ ሁለት አሀዝ ያላቸው (ለምሳሌ I-75) ሰሜንና ደቡብ/ምሥራቅና ምዕራብ የሚወስዱ ናቸው። የሰሜን/የደቡብ መስመሮች የተሰጣቸው ቁጥር ጎዶሎ ሲሆን ምሥራቅ/ምዕራብ የሚወስዱት ደግሞ ሙሉ ቁጥር ያላቸው (ለምሳሌ I-20) ናቸው። የአትላንታ ዋና ጎዳናዎች I-75 እና I-85 ሰሜን ደቡብ፤ I-20 ምሥራቅ/ምዕራብ፣ I-285 ዙሪያ ክብ ሲሆን በከተማው ውስጥ ያሉት ሌሎች ጎዳናዎች ዋናዋናዎቹ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን ሀይዌዮች ይገናኛሉ።

የኦሎምፒክ ዋና ዋና ዝግጅቶች የሚከናወኑት በዳውንታውን ውስጥ ነው። በብዙ ቱሪስቶች የሚጎበኘው የማርቲን ሉተር ኪንግ ማዕከል የሚገኘውም እዚያው ነው። በአካባቢው Peachtree በሚል ስም የሚጠሩ ብዙ መንገዶች አሉ። ዋናውና አንጋፋው Peachtree Rd. ሲሆን ይህን መንገድ ተከትለው ከዳውንታውን ሰሜን ቢጓዙ መንገዱ ላይ መላቅጡ የጠፋ ሰማያዊ መስመር ተሰምሮበት ያገኙታል። የማራቶን ተወዳዳሪዎች እንዲከተሉት ተብሎ የተሰመረ ነው። ለብዙ ዓመቶች እንዲቆይ የተፈረደለት ታሪካዊ መስመር ነው። ይህ መስመር በጊዜ ብዛት እየደበዘዘ ካልጠፋ በቀር እንዳለ እንዲቆይ ተወስኗል ... ለታሪክ ቅርጽ!

በባርሴሎና የተካሄደው ያለፈው ኦሎምፒክ ላይ የቴሌፎን መስመሮች (Cellular Phones) በመተናነቅ (Jammed) የግኑኝነት መስመሮች ስብራት ደርሶባቸው እንደነበረ ተገል ጾአል። በአትላንታው ኦሎምፒክ ተመሣሣይ ችግር እንዳይመጣ አስፈላጊው ዝግጅት እንደተደረገ ቢገመትም አንዳንድ ችግሮች (በተለይ በሙቀት ሳቢያ) ሊከሰቱ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል።

እንደተጠቀሰው ከተማዋ ዝግጁ ናት። የኦሎምፒክን በዓል ምክንያት በማድረግ ወደ አትላንታ የሚጎርፈው ሕዝብ ብዙ ነው። በከተማዋ ውስጥ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የልዩ ልዩ ስቴቶች ሠሌዳ ያነገቡ መኪናዎች ይታያሉ። በዚህ ኦሎምፒክ በዓል ውስጥ ለመሣተፍ፣ ለመሥራት፣ ለመነገድና የታሪክ አካል ለመሆን የሚጠባበቀው ሰው ብዙ ነው። በአንዳንድ ጋዜጦች ላይ የፍጆት ዕቃዎች ዋጋ ከፍ እንደሚልም ተጠቅሷል። (አንዳንድ ቦታዎች ላይ አንድ ሳንድዊች እስከ አስራ አራት ዶላር እንደሚፈጅ/አንድ ብርጭቆ ብርቱካን ጭማቂ እስከ አምስት ዶላር ድረስ እንድሚያወጣ ታውቋል) ሆኖም ከተማው ውስጥ በመጠነኛ ዋጋ ተመሣሣይ ነገሮችን ማግኘትም ይቻላል። መጓጓዣን በሚመለከት ዋነኛው የበዓሉ ትራንስፖርት አቅራቢ የከተማው የባቡርና አውቶቡስ ድርጅት (Metropolitan Atlanta Rapid Transportation Authority - MARTA) ነው። የዚህ ድርጅት የህዝብ ግኑኝነት ኃላፊው አቶ መኮንን ገ/ህይወት የተባሉት ኢትዮጵያዊ ናቸው። አቶ መኮንን በዘንድሮው ኦሎምፒክ በዓል ላይ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ አምባሳደር ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው።

ከMARTA ሌላ የከተማዋን ትራንስፖርቴሽን የሚሸፍኑት የታክሲ ድርጅቶች ናቸው። በከተማዋና በአካባቢዎቿ ውስጥ ከሁለት ሺህ በላይ የሚቆጠሩ ታክሲዎች ግልጋሎት ለመስጠት ተዘጋጅተዋል። በአትላንታ የታክሲ ኢንዱስትሪ ውስጥ ኢትዮጵያውያኖች አንጋፋውን ቦታ ይዘውታል። በአቶ ሠለሞን በቀለ መንገድ ከፋችነት የተመሠረተው የRapid ታክሲና ኢንሹራንስ ድርጅት ለብዙ አገር ልጆች አርአያ/ምሣሌ በመሆኑ የAmerica Cab፣ የUnited Cab፣ የCrown Cab ... ተብለው የሚጠሩ ሌሎች የኢትዮጵ ያውያኖች የታክሲ ድርጅቶች አሉ።

እንደሚባለው ከሆነ ሦስት ታክሲዎች ቢያቆሙ አንዱ ኢትዮጵያዊ እንደሚሆን አይጠራጠሩ! በመሆኑም አብዛኛው ታክሲ የሚንቀሳቀሰው በአገር ልጆች ወይም በሌሎች አፍሪቃውያኖች ነው። በጁላይ19 የሚጀምረው የኦሎምፒክ በዓል ብዙ ድርጅቶችን እንዳቁነጠነጠ ሁሉ በከተማዋ ውስጥ የሚገኙት የአገር ልጅ ድርጅቶችም ተዘጋጅተው ይጠባበቃሉ። በልዩ ልዩ ቦታዎች ላይ የተለያዩ የአበሻ ድርጅቶች መኖራቸው ቢታወቅም እዚህ ላይ ትኩረት የተሰጠው ምግብ ቤቶችና መዝናኛ ቤቶች ላይ ነው። የንግድ ፈቃዳቸውን ለጥፈው በራቸውን ከፍተው የሚጠባበቁ የምግብና የመዝናኛ ድርጅቶች አሉን። እንጀራም፣ ክትፎም ሞልቷል። እንዳውም ለዚህ በዓል ብለው ልዩ ዝግጅት ያደረጉም አሉ።

<u>የአባይ ሬስቶራንት (321-5808)</u> በሻማ የበራ ጠረጴዛ ላይ ጥሩ ራት ለመጋበዝ አመቺ ሲሆን ለአሥራ ሰባቱ የኦሎምፒክ ምሽቶች የሙዚቃና የጭፈራ ዝግጅት እንደሚኖረው ገልጠውልናል። እንዲያውም ድርጅቱ ለጥቂት ሰዓቶች በሩን ከመዝጋቱ በቀር እስከ ሌሊቱ 10 ሰዓት ድረስ (4:00am) ክፍት እንደሚሆን ታውቋል። የአባይ ምግብ ቤት በአንድ ጊዜ እስከ መቶ የሚቆጠሩ ደንበኞችን ማስተናገድ የሚችል ከመሆኑም ሌላ በበዓሉ ምክንያት የደንበኞች ቁጥር እንደሚጨምር በመገንዘብ ግምታቸው ውስጥ ማስገባታቸውን የድርጅቱ አስተዳዳሪዎች አቶ ፋሲልና አቶ ሣሙኤል ገልጠዋል። ለዚህ በዓል ድምፃዊ ጌታቸው ካሣን በማስመጣት የጭፈራውን መድረክ ይከፍታል።

<u>የ"ካሊፎርኒያ ማርት" (320-6747)</u> የተባለው ድርጅት (ብዙዎች የስፖርት ምግብ ቤት ይሉታል) በውስጡ ብዙ መዝናኛዎችን የያዘ ምግብ ቤት/ጌም ሩም ነው። ይህ ድርጅት ከመቶ በላይ የሚሆኑ ደንበኞችን ማስተናገድ የሚችል ሲሆን በውስጡ ምግብ ቤት፣ ቢራ ቤት፣ ቴሌቪዥን ክፍልና የጠረጴዛ ኳስና ከረምቦላን/ፑል ጠረጴዛዎችን የያዙ ክፍሎች ያሉትና በተጨማሪም የስጦታ ዕቃ መደብሩ (Gift shop) በልዩ ልዩ የአገር ቤት ልብሶች/ጌጣጌጦችና ሙዚቃዎች ያሸበረቀ ነው። ድርጅቱ የተዝናና መንፈስ (Mood) የሠፈነበት ከመሆኑም በላይ ከቡናና ከምግብ በስተቀር ሌላ የሚፈልጉትን ነገር የሚያስተናግዱት እርስዎ ራስዎ መሆንዎን ይገንዘቡ። በአጠገብዎ የሚገኙትን ማቀዝቀዣዎች ከፈት አድርገው የሚፈልጉትን ነገር ወስደው መዝናናት ነው። ድርጅቱ Honor System ስለሚጠቀም የሚከፍሉት ሁሉ ራስዎ ቆጥረው የተናገሩትን ነው። የካሊፎርኒያ ማርት ለዚህ በዓል "ፌዲፒዲሥ" የሚል የአስራ አምስት ቀን በዓል እንደሚያዘጋጅና የሙዚቃ ምሽቶችና/ጭፈራዎችም እንደሚኖሩ አስተዳዳሪው አቶ ወንድወሰን ገልጧል።

<u>ሀናና ብንያም ሱቅ (H&B Shop) (296-2766)</u> ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በመታወቅ ላይ የሚገኘው ይህ ድርጅት ከከተማዋ ወጣ ብሎ የሚገኝ ሲሆን ሱቅ፣ ምግብ ቤት፣ ግሮሰሪና የሌሜዚን ሰርቪስ የሚያቀርብ መሆኑን የድርጅቱ አስተዳዳሪዎች ወ/ሮ ወለላና አቶ አስማማው ገልፀዋል።

የከተማችንን መንገዶች፣ የትራንስፖርት ተቋሞችንና የመዝናኛ ድርጅቶችን ያበሰርንዎን ያህል ሌላ እንዲያውቁልን የምንፈልገው በሚዲያ መስክ በኩልም አትላንታ ሁለት ኢትዮጵያዊ መጽሔቶች (ላንዳፍታ እና ኢትዮጵያ ሪቪው) የሚዘጋጁባት ከተማ መሆንዋንም ነው። ሁለቱም አዘጋጆች (አቶ መኮንን እና አቶ ኤልያስ) አትላንታ ውስጥ ከከተሙ ሰንብተዋል። ከእነዚህ አዘጋጆች ጋር ተገናኝቶ ለመነጋገር አመቺው ከተማ ሌላ ሊሆን እንደማይችል እርስዎም ያውቃሉ።

ከእነዚህ ሌላ መጠቀስ ያለባቸው ሁለት ካፌዎች አሉ። ሁለቱም የሚገኙት Little five point (L5P) የተባለው የሒፒ/የራስታ/የኬረዳሽ ሕዝብ ሰፈር ውስጥ ነው። አንዱ ቴት-ሰ-ቴት የተባለው የካፑቺኖና የኬክ ቤት ሲሆን ሁለተኛው Le Creame! የተባለው የቡናና የሳንድዊች ቤት ነው። የሁለቱም ድርጅቶች አስተዳዳሪዎች የአገር ልጆች ሲሆኑ ድርጅቶቹ (አካባቢያቸውም) በጣም የተዝናና መንፈስ (Mood) የሠፈነባቸው ቦታዎች ናቸው።

የኦሎምፒክ በዓል በሚካሄድበት ጊዜ መንፈሳዊ ሰበካ እና የእምነት ተሀድሶ ካስፈለገዎት የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በሯ ክፍት ነው፤ (404) 377-2238

መልካም የኦሎምፒክ በዓል ለሁላችን!

**መልካም የኦሎምፒክ ውጤት**
**ለኢትዮጵያውያን አትሌቶቻችን !!**

# ግልፅ ደብዳቤ

## በቺካጎ ለሚካሄደው የአድዋ መቶኛ ዓመት በዓል ለደጋፊዎች (እርዳታ ሰጪዎች) እና ተሳታፊዎች የተፃፈ

ሰኔ 19, 1996

እኛ ጉዳዩ ያገባናል የምንልና ነገሩም ያሳሰበን በቺካጎ ከተማና አካባቢዋ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ለማክበር ያቀዳችሁትን የአድዋ መቶኛ ዓመት መታሰቢያ በዓል በሚመለከት ስለአስተሳሰባችሁ ለደጋፊዎች ወይም እርዳታ ሰጭዎች ምሥጋናና ልባዊ አክብሮትን ለማቅረብ እንወዳለን። ነገር ግን ፖለቲካዊ ባልሆነ መንገድ እንዲከበር የፀና ፍላጎታችን ነውና አከባበሩ የተደራጀው ያሁኑን የኢትዮጵያን መንግሥት አጀንዳ ለማራመድና ለመንግሥቱም ለራሱ ጥቅም እንዲበጅ ሆኖ የተዋቀረ በመሆኑ ይህንንም በመረዳታችን እጅግ አዝነናል።

ከኦኒባልበኋላ በአውሮፓውያን ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለጥቁር ሀገር ድልን ያቀዳጀው የአድዋ ጦርነት ግቡን ሊመታ የቻለው፣

1) በዳግማዊ ምኒሊክ ትንግርታዊ ወታደራዊ ስልትና በእርሳቸው የጦር መኮንኖች ችሎታ

2) እንደዚሁም አንድነትን በሚያስገርም ሁኔታ ባሳየው ጀግናና ቆራጡ የኢትዮጵያ ወታደር ምክንያት የተነሳ ነው።

ይህ ቋሚና ሕያው የታሪክ ክቡር ቅርስ የአንድ ጎሳ አስተዋጽኦ እንደሆነ ተደርጎ በአሁኑ የኢትዮጵያ መንግሥት እየተውገረገረና እየተጣመመም ነው። በአካባቢውና ዓለም አቀፍ ደጋፊዎቹ ዕርዳታ ይህ የጎሳ መንግሥት በተፋጠነ መንገድ ኢትዮጵያን እያጠፋት ነው። ከጥፍር እስከ ራሱ በዘመናዊ ጦር የታጠቀው የአውሮፓ ወታደር ላይ እንደዚህ ዓይነቱን አዳፍኔ ድል በአንድ ኃይል የተቀዳጀውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደዘረኛው የደቡብ አፍሪቃ የአፓርታይድ ሥርዓት የሕዝባችንን አንድነት ይህ መንግሥት በዘጠኝ የጎሳ ክልሎች ከፋፍሎታል። ይህን የሀገር ማጥፋትና ማፈራረስ ሕጋዊ ለማድረግ ብሎም የኤርትራ መገንጠል የተገቢነት ሽፋን እንዲለብስ በዓለም ላይ ብቸኛና የመጀመሪያውን መገንጠልን የሚያበረታታ ሕገ መንግሥት ደንግጓል።

በቺካጎ አካባቢ ከአድዋ መቶኛ ዓመት መታሰቢያ በዓል በስተጀርባ ፀረ-ኢትዮጵያዊ የሆነ ቡድን ይህን አጋጣሚ በመጠቀም መረቡን እየዘረጋ ነው። ከሁሉም የባሰውና የከፋው ግን በዚህ በዓል በማሳበብ ሽሩን ከማይጠረጠሩ የቺካጎ ነዋሪዎች ይህ ቡድን ገንዘብ ለመሰብሰብ እየጣረ ነው። ይህም ገንዘብ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሚያራምደው ኢሰብአዊ የኅበረተሰብና የኢኮኖሚ ፖሊሲ መደገፊያ ይውላል። ለዚህ በዓል ደጋፊዎችና ተሳታፊዎች ቀላልና ግልፅ ሊሆኑ የሚገባቸው ጥቂት ጥያቄዎች አሉ። ከቶ ለምን ይሆን ቁጥራቸው ከ4,000 በላይ የሚሆኑ የቺካጎ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን፣ የኢትዮጵያውያን የንብረት ድርጅቶችና የኅብረተሰብ ማኅበራት የአድዋ ድል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ቅርስና ኩራት መሆኑ እየታወቀ በእቅዱና በዝግጅቱ ላይ እንዲሳተፉ ያልተነገራቸው? ለምን ይህ ፀረ-ኢትዮጵያ ቡድን ለዴላ(ትግራይ) ገንዘብ ይሰበስባል? ለምንስ ይሆን በኢትዮጵያ ሲሆን የወያኔ ጠባብ ብሔረሰቦች፣ በቺካጎ ግን ዓለም አቀፍ የሆኑት? በተጨማሪም በዓሉ ላይ የሚናገሩት ኢትዮጵያውያን የተመረጡት በጎሳቸው ሐረግና ላለው የዘረኛ መንግሥት ባሳዩት እምነት እንጂ በምሑርነታቸውና ባላቸው የኢትዮጵያ ታሪክ ዕውቀት አይደለም።

የቺካጎ ኅብረትና የሚድዌስት የኢትዮጵያውያን ማኅበር ይህ ሁኔታ ስላስቆጣቸውና ስላሳዘናቸው በሚቻለው መንገድ ሁሉ ተቃውሞአቸውን ለማሰማት እየተዘጋጁ ነው። ኅብረትና የሚድዌስቱ የኢትዮጵያውያን ማኅበር የተደራጁት የኢትዮጵያን አካላዊ ልዕልናና የሕዝቦቿን አንድነት ለማስከበር፣ በኢሕአዴግ የሚካሔዱትን የሰው ልጆች መብት ገፈፋና እንደዚሁም ኢሕአዴግ የሚያራምደውን የዘር ጥላቻ ለማጋለጥ በሚሉ መሠረታዊ መርሖዎች ላይ ነው። ስለሆነም ከዚህ አጭበርባሪ ወይም መሰሪ ዝግጅት ራሳችሁንና ድርጅቶቻችሁን እንድታገሉ በመማፀን ለፍትሐ ዊሕሊናችሁ እንወተውታለን። የአካባቢው ቅጥረኞች የአድዋን በዓል ለኢትዮጵያ መንግሥት አሳፋሪና ኢሰብአዊ የፖለቲካ አጀንዳ ብሎም የአፍሪቃን ትምህርታዊና ዕድገታዊ ድርጅት አጋናኝና ትልቅ ስም በመጠቀም ድርጊታቸውን እንዲፈፅሙ መደገፍ የለብንም።

**የቺካጎ ኅብረትና የሚድዌስት**
**የኢትዮጵያውያን ማኅበር**

# ሻለቃ ግርማ ዳምጤ

1932-1996



*"የመልካም ሰው ሥራ የሚፃፈው በወረቀት ሳይሆን፣ እንዳውም በእግዚአብሔር ልብ ላይ ነው።"*

ሻለቃ ግርማ እንደአውሮፓውያኖች ቀን አቆጣጠር በ1932 ዓ.ም ከአባታቸው ከአቶ ዳምጤ ከበደ ወ/ጊዮርጋስ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ማሚቴ ተበጀ በግንደበረት ተወለዱ። የአርበኛ ልጅ በመሆናቸው የአንደኛ ትምህርታቸውን በገብረማርያም ትምህርት ቤት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትምህርት ቤት ያጠናቅቃሉ። ከዚያም ኢትዮጵያ አየር ኃይል በመግባት የሻለቃነትን ማዕረግ እስካገኙበት ጊዜ ድረስ አገለገሉ። በኋላም በኢትዮጵያ አየር መንገድ ያገለግሉና በ1971 ወደ አሜሪካ በመምጣት ቴኔሲ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ገብተው በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ይመረቃሉ። ሻለቃ ግርማ በድንገት በሞት እስከተለዩን ድረስ የኖሩት ቴነሲ እስቴት በሚገኘው የናሽቪል ከተማ ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ይርጋ ዓለም በላቸውና ከልጆቻቸው ነብዩ፣ መቅደስ፣ ቤተልሔምና በላቸው ጋር ነበር።

ሻለቃ ግርማ አገራቸውንና ህዝባቸውን የሚወዱ ታላቅ ሰው ነበሩ። ብዙ ኢትዮጵያውያን ቤተዘመድን ከሀገር ቤት ኃላፊ በመሆን እያስመጡ በመርዳት ሁሉም ራሳቸውን እንዲችሉ አድርገዋል። ከዚህም በተረፈ በመጀመሪያ የኢትዮጵያውያን ኮሚዩኒቲ ማኅበር በናሽቪል ከተማ እንዲቋቋም ከረዱት መካከል ዋነኛው ነበሩ።

ሻለቃ ግርማ ለአገርና ለወገን ባላቸው ፍቅር የተነሳ ከ25 ዓመት የውጭ አገር ኑሮ በኋላ ወደ ሀገራቸው ሄደው ዘመዶቻቸውንና ጓደኞቻቸውን ጎብኝተዋል። አገራቸው ተመልሰው ከባለቤታቸው ጋር የጡረታ ቤታቸውን ሰርተው ለመኖር አቅደው ነበር። በጣም ደግ ሰው በመሆናቸው ተቸግሬአለሁኝ ብሎ የጠየቃቸውን ሰው በምንም ዓይነት ሳይረዱ አይመልሱም። ሌላው ቀርቶ በፖስታ የሚመጣው እርዳታ ጠያቂ ሁሉ ከግርማ ዳምጤ የገንዘብ እርዳታ ሳይቀበል የቀረ የለም። የተጣላን ለማስታረቅ ሀገሩ ሩቅ ነው ሳይሉ የሚቻላቸውን ያህል ለማድረግ ይሞክራሉ። ሻለቃ ግርማ ለእኔ ብቻ የሚባል ሃሳብ አልነበራቸውም፣ አብረን እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንጫወት፣ እንደሰት የሚሉ ሰው ነበሩ።

የቀ.ኃ.ሥ ት/ቤት 25ኛ ዓመት ኢዮቤልዩ በተከበረበት ጊዜ በታተመው መጽሐፍ ላይ አቶ ነጋሽ ገ/ማርያም ስለሻለቃ (በዚያን ጊዜ ሻምበል) ግርማ የፃፉትን ዛሬ ስናነበው ልዩ ትርጉም አለው፣


"ወልደአምላክ በላቸው "እነ ሻምበል" ግርማ
ተስፋዬ ኪዳኔ ዘውዴና ከተማ (ደስታ)
ያስቁን ነበረ እስኪፈስ እምባችን
የነፍስ ሙዚቃ ነውና ሣቃችን!

*"ደስ ያላት ልብ መልካም መድኃኒት ናት፤ ያዘነች ነፍስ ግን አጥንት ታደርቃለች"* (ምሳሌ 17:22) ተብሎ እንደተፃፈው በሻለቃ ግርማ ፍቅር እና ጨዋታ ልባችን ብዙ ተደስታ ነበር፤ ዛሬ አጥንታችን ደርቃለች።

እንግዲህ የአቶ ነጋሽን ግጥምን እንዲህ እንጨርሰው፣
ሃዘናችን በዛ አበቃ ሣቃችን
ነፍሳትን ለማሳቅ ሄደና ግርማችን!

## የውድ ባለቤታቸው
## የወይዘሮ ይርጋ ዓለም በላቸው
## የኀዘን እንጉርጉሮ

ባለቤቴ ልበልህ አሽከሬ
ወንድሜ ልበልህ ወይንስ አጋሬ፤
ተላላኪዬ ነህ ወይስ ዘበኛዬ
የልቤን አድራሼ ጓደኛዬ
ሁለመናዬ ነህ ግርማዬ።
ብዙ ተወያየን ስለኑሮአችን
ተመካከረንበት እቅዳችንን
ተመልሰን ልንሄድ ወደ አገራችን
መሠረት ልንጥል ለቤታችን
ተስማምተን ነበረ ቃል ተገባብተን
ሞት ቀደመብኝ አንተን።
ሞሽተህ እንኳን አታውቅም ነበረ
የነገርከኝ ሁሉ ምነው ሳይሆን ቀረ።
ማነው ያስተማረህ ይህን ክህደትን
እንደዚህ በአቋራጭ ሳናውቅ መሹለክን።
አገር ቤት ገብተን ከዘመድ ጋራ
የጡረታ ቤታችንን ልንሰራ
ብዙ ልንኖር ነበረ
ምነዋ ቃልህ ተሰበረ።
ትልቁን አዳራሽ ሠርተህ
እኔን ብቻዬን ጎልተህ፤
ለጭንቀት ለጥበት ዳርገኸኝ
ምነዋ የእኔ ግርማ ተለየኸኝ።
ግርማዬ ጌጤ ሁለመናዬ
ወንድም ጓደኛዬ መኩሪያዬ፤
ነበርክ ለእኔ ማር ወተቴ
ስታመም ፈዋሼ መድሃኒቴ፤
ሰው ሲራብ ተርበህ፤ሲጠማ ተጠምተህ፤
ሲስቁ ተጫውተህ ሲያዝኑም እንባ ረጭተህ
ከትንሹ ጋር ስቀህ ተቃልደህ
ከትልቁም ጋር አምሮብህ ኮርተህ
የተጣላ አስታርቀህ
አንተም ተው፣ አንተም ተው ብለህ።
በወገን ተወደህ ተከብረህ የኖርከው
እኔን ብቻ አይደለም ጥለኸኝ የሄድከው።
አገር ነው ጉድ ያለው የሚያውቅህ በሙሉ
ግርማ ዳምጤ የታለ ብሎ ሮሽ ሁሉ።
ምነው ሳትነግረኝ ምስጢርህን ደበቀኸኝ
ምልክት ሳትሰጠኝ መሄዴ ነው ሳትል
በድንገት ከዳኸኝ።
ብቻዬን ቁጭ ብዬ ከዚህ ሰፊ ቤት
ሳቅና ጨዋታህ ይመጣል ድንገት።
እንዳው በፊቴ ላይ ትጎማለላለህ
ስተኛም ስነሳ ሁሌ ትመጣለህ።
ምክርና ጨዋታህ በጎ ሥራህ ሁሉ
በዓይኔ ህሊናዬ ሁሌ ድቅን ሲሉ
የማደርገው ጠፋኝ የምሰራው ሁሉ፤
በያላችሁበት የምታውቁት ሁሉ
ድንገት ይመጣ እንደሁ ግርማ ግርማ በሉ።
ግርማዬ ግርማዬ የእኔ የብቻዬ
እስከምንገናኝ ይፈላል እምባዬ።
ግርማዬ መኩሪያዬ የልጆቼ አባት
እስከምንገናኝ በል በደህና ሰንብት።
ቸር መልካም አድራጊ እንደመሆንህ
አልጠራጠርም ከቅዱሳን ጋር አብረህ እንዳለህ።
ለጊዜው ልበልህ ደህና ክረምልኝ
እስከመጣ ድረስ ለእኔም ቦታ ያዝልኝ።



## የሻለቃ ግርማ
## የመሰናበቻ ቃል

በዚች መሬት ላይ በዚች ምድር
ከቤተሰቤ ጋር ለመኖር ስጥር ስፍጨረጨር
ከላይ ከታች ስወርድ ስወጣና ስጥር
ብዙ የምኖር መስሎኝ በዚህ የኪራይ ምድር።
ትምህርት ቤት ገብቼ እውቀትም ቀስሜ
ሠርቼ በደስታ ለመኖር አልሜ።
ሃሳቤም ተሳክቶ ከባለቤቴ ጋር
በፍቅር በደስታ አብረን ስንኖር፤
እግዚአብሔር ሲፈቅድም አገር እንገባለን፤
ወገናችንንም እንረዳለን።
እያልን ከቤተሰቤ ጋር ስንወያይ
ለእኔ የታቀደውን ሳላይ።
እኖርበታለሁ ያልኩት ቤት
ለካስ ኖሯል እንቅፋት።
በተቻለኝ ወገኖቼን ረድቼ ከጓደኞቼ ጋር ተጫውቼ፣
ካዘነው ጋር አዝኜ ከተደሰተው ተደስቼ።
ከወንድም ከእህቶቼ እስከዛሬ ኖሬአለሁ
መራመዴን ነበር እንጂ መውደቄንማ መች አየሁ።
የሀገርና የወገኔን ናፍቆቴን ሳልወጣ
በአንድ ላይ ተሰብስበን የደስታን ጽዋ ሳንጠጣ፤
ሃሳቤን ሁሉ ሳልጨርሰው ያለምኩትን የወጠንኩትን
መች ጠርጥሬ አውቄ እንዲህ በድንገት መጠራቴን።
በሉ እንግዲህ በደህና ሁኑ በችኮላ ሄድኩኝ እኔ
ሰላምና ፍቅር እመኛለሁ ለሀገሬና ለወገኔ።
የምወድው ጌታዬ በእስቸኳይ ጠርቶኝ ሄጃለሁ
ቤተሰቤና ወገኔ ደኅና ሁኑልኝ እላለሁ።

ለዘመድ አዝማድ፣ ከየሀገሩ ለመጣችሁ፣ በደብዳቤ፣ በካርድና በስልክ የኀዘናችን ተካፋዮች ለሆናችሁን ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

# የውይይት መድረክ

## እነዚህ ልጆች የሚፈልጉት ምንድን ነው?

### "በመስታወት ቤት ውስጥ የሚኖር በሌሎች ላይ የመጀመሪያውን ድንጋይ ወርዋሪ አይሆንም!!

---

### "በኦሮሞ ሕዝብ ደምና እንባ የሚካሄደው ንግድ ማብቃት አለበት!!"

(ከጦቢያ መጽሔት የተወሰደ)

ከመረራ ጉዲና
ረዳት ፕሮፌሰር (አ.አ.ዩ)

ክፍል - 2

የልብወለድ ደራሲያንና ሠዓሊዎች አንዱና ዋነኛው ችሎታ ያዩትንና የሕይወት ገጠመኞቻቸውን ከገሀዱ ዓለም ዕውነታ ጋር በማመሳሰል ዕውነት ሊመስሉ በሚችሉበት መልክ ለተደራሲያኑ ማቅረብ ነው። "ኡርጂ"ና "ሠይፈ ነበልባል" በተባሉ ጋዜጦች በተለያዩ የብዕር ስሞች የሚጽፉት ግለሰቦችም እንደዚያው ይመስሉኛል - አስመስሎ ማቅረብ፣ ግን አልቻሉበትም። እኔ ለሹመትና ለትርፍ ስል ከፍተኛ የመኢሶን ጓዶችንና ከአንድ ሆድ የወጣውን ወንድሜን አሳልፌ ለደርግ ጥይት ሰጥቼ፣ ለአንድ ቀን እንኳን ሹመትና ሽልማቱን ሳላገኝ ለ7 ዓመታት እሥረኛ መሆኔን ይነግሩኛል። የመኢሶን ሚኒስትር የነበሩትን ዶ/ር ተረፈ ወልደፃድቅን ጨምሮ ብዙ የመኢሶን ጓዶችን አስጨርሷል የሚሉኝ ሰው ከ20 ዓመታት በኋላ ለዳግማዊ መኢሶን መምጣት ስታገል ይታያቸዋል። እንደነሱ አባባል አንድም ቀን አቋም ኖሮኝ አያውቅም። ዘላለም ስዋልል የኖርኩኝ ነኝ። "ስደተኛው አማራ" ተመልሶ የኦሮሞን ሕዝብ ባሪያ እንዲያደርግ የሚታገለው መረራ አሁን አራት ኪሎ ለሚገኘው ኢሕአዴግ ለሚሠሩት "ጎበናዎች" መድረክ ማመቻቸት ብቻ ሳይሆን በወያኔ ተራ የተሰለፈ ሆኗል። በአጠቃላይ አንዱ ሀሳባቸው ከሌላው ጋር ጨርሶ ባልተያያዘ ሁኔታ እርቲ ቡርቲ የሚዘበዝቡት እነዚህ የኡርጂና የሰይፈ ነበልባል "ፀሐፊዎች" ከየት መጡ? እነማን እንደሆኑና ዓላማቸውስ ምንድነው? የሚለውን ከሚያቀርቡአቸው እንቶ ፈንቶዎች ጋር እያጣቀስን በዝርዝር እንመልከት።

እንደወጥ ማጣፈጫ ቅመም ከጽሑፎቻቸው የማይጠፉትን ራስ ጎበናን ጨምሮ በእነዚህ ሰዎች ደጋግመው የሚነሱት ስሞች ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ፣ ራስ አበበ አረጋይ፣ ጄኔራል ጃጋማ ኬሎ፣ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ ወ.ዘ.ተ ናቸው። የእነዚህን የኦሮሞ ልጆች ስም የሚያነሱት ትናንት እነሱ በነበሩበት ዘመን ከነበሩት ነባራዊ ሁኔታዎች አንፃር፣ ድርጊታቸውንም በታሪክ ሚዛን ለክተው ከእነሱ የተሻለ ለመሥራት ሳይሆን ከራሳቸው ፀሎት ቤቶችና አካባቢ ውጭ የተወለዱትን የኦሮሞ ልጆች ስም ለማጥፋት አልመውና አቅደው ነው። ሊደርሱበት የሚፈልጉት ግብም ከእነሱ የተሻለ ችሎታና ታሪክ ያላቸውን የኦሮሞ ልጆች ሁሉ ስም በማጥፋት ችሎታውም ሆነ ታሪኩ ለሌላቸው የታሪክ ዝቃጮች ቦታ ለመፍጠርና የደራ የፖለቲካ ንግዳቸውን ለመቀጠል ነው።

ስለሚያቀርቡዋቸው ክሶችም በትክክል የሚያውቁ አይመስለኝም። ለምሳሌ፣ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ክርስትና ተነሱ ይሉናል። እነሱ ክርስትና መነሳታቸውና ስማቸውም ዮሐንስ ለታ፣ አብርሃም ለታ፣ ማርታ ኩምሣ መሆናቸው ግን አይታያቸውም። በመሰረቱ ሁለቱ ልዩነት ቢኖራቸው ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ክርስትና የተነሱት በጥቁሮች ቤተክርስቲያን ሲሆን፣ እነሱ ግን በፈረንጆች ፀሎት ቤት መሆኑ ነው። እኛ የምናውቀው ትናንት የሚሲዮን ኬክ ለመግመጥ ዮሐንስ፣ አብርሃም፣ ማርታ የነበሩት ዛሬም የኦሮሞን ሕዝብ ለማጭበርበር ሌንጮ፣ አባጫላ ለታ፣ ኩዌ ኩምሣ መባላቸውን ነው።

የፈለግነውን ያክል ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን ጠልተናል እንበል። እስኪ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ዓመታት የኖሩትን የፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስንና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ያሉትን የአቶ ዮሐንስ (ሌንጮ) ለታን የማሰብ ችሎታ የሚከተለውን የታሪክ ክንዋኔ በመጥቀስ እናወዳድር።

በአንድ ወቅት እንግሊዞች ኬንያን ከያዙ በኋላ ቦረናንም ለመውሰድ ሰራዊታቸውን ወደ ቦረኖች መሬት አስርገው ያስገባሉ። ቦረናዎች የእንግሊዝን ወታደሮች ከፊሎችን ገድለው ሌሎችንም ወደመጡበት ይመልሳሉ። የሠራዊቱ ደም የፈሰሰበትን መሬት ለመውሰድ የእንግሊዝ መንግስት ዲፕሎማቶቹን ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ይልካል። "ወታደሮቻችን ለግጦሽ ቦረና አካባቢ ገብተው ሞቱብን። የግጦሽ ችግር ስላለብን ቦረና በደም ካሣ መልክ ይሰጠን" ይሉዋቸዋል። ምኒልክም ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን እናናግሩ ይሉዋቸዋል።

ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ አባመላም የእንግሊዝ ዲፕሎማቶችን በፈገግታ ተቀብለው ከአስተናገዱ በኋላ የመጡበትን ጉዳይ ይጠይቋቸዋል። የእንግሊዝ ዲፕሎማቶችም ለምኒልክ የነገሩትን ይደግሙላቸዋል። ፊታውራሪም "ጥያቄያችሁ ተገቢ ነው። እኛም ለወዳጆቻችን የማናደርገው ነገር የለም። ይመዝገብላችሁ" ይላሉ። የፈለጉት የተፈፀመ መስሏቸው የፈነደቁት የእንግሊዝ ዲፕሎማቶችም ጉዳያቸውን አስመዝግበው ሲጨርሱ፣ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ "እኛም ለወዳጆቻችን የምናቀርባት ትንሽ ጥያቄ አለችንና ይመዝገብልን" ይላሉ። አስከትለውም "የእኛ ንጉሥ ልጅ የነበረ ዓለማየሁ የሚባል ለንደን ከተማ ውስጥ ሞቶ ተቀብሮአልና በመቃብሩ አካባቢ ያለውን የለንደንን ከተማ ቆርሳችሁ ስጡን" ይላሉ። ቦረናን ለመውሰድ የመጡ እንግሊዞችም ከለንደን ከተማ መሬት ሲጠየቁ አፋቸውን ዘግተው ተመለሱ። በእንፃሩ የእንግሊዝን፣ የፈረንሳይን፣ የጣሊያንን ዲፕሎማቶች አሳፍረው ሲመልሱ የነበሩትን ሀብተጊዮርጊስን በቅኝ ገዥነት የሚከሱት ማፈሪያዎች ከሻዕቢያና ከወያኔ ጋር ተደራድረው እንዳች ጥቅም ለኦሮሞ ሕዝብ ማስገኘት ተስኗቸው የሰሩትን እንይ።

የሽግግር መንግስቱ ሲመሰረት ከፊል አማራ የሆኑት እነአብዩ ገለታ "አማርኛ አናውቅም" እያሉ በእንግሊዝኛ የመናገር ድራማ ሲሰሩ የሚሰሩትን በትክክል የሚያውቁት እነመለስ ዜናዊ በመንዝ አማርኛ እየተናገሩ የኢህአዴግን ሰራዊት በሀገሪቱ መከላከያ ሠራዊትነት አስመዝግበው እነሌንጮን አስፈረሙ። ሻዕቢያን ከሚያምኑበት አምላክ በላይ የሚያመልኩት እነሌንጮ ለታ በሻዕቢያ አደራዳሪነት ከኢሕአዴግ ጋር ተነጋግረው በሻዕቢያ በሚጠበቅ የኢህአዴግ ማጎሪያ ውስጥ አስገብተው በማጎር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆችን ለስቃይና ለሞት ዳርገዋል።

ይህ ብቻም አይደለም። የኦሮሞ ልጆችን በሥነሥርዓት ሰብስበው ካምፕ አስገብተው ለጥቃት ካመቻቹ በኋላ "እኛ ከሽግግር መንግሥቱ ስለወጣን ካምፖችን ሰብራችሁ ውጡ ብለው" ከአብዶች ወይም የተደበቀ ዓላማ ካላቸው ሰዎች ብቻ የሚጠበቅ ትዕዛዝ ሰጥተው ሺዎችን አስጨርሰዋል።

እነዚህ ሰዎች በሒልተንና በጉለሌ መሐል እየተመላለሱ አራት ኪሎ በሚገኘው መንግሥት ላይ ጦርነት እያካሄድን ነው የሚሉ አስቂኝ ሰዎች ናቸው። የኦሮሞን ልጆች ከሚሠሩባቸው መሥሪያ ቤቶች፣ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎችን ጭምር ወደ ጫካ ሸኝተው ለራሳቸው በቦሌ በኩል በመንግስት አየር መንገድ በመሹለክ ቀደም ብለው በቤተሰቦቻቸው በኩል ወደአዘጋጁት መናኸሪያ ማለትም ወደ አውሮፓ፣ አሜሪካና ካናዳ የበረሩ ትንግርተኛ ሰዎች ናቸው። እንደገናም ተመልሰው በየእስር ቤቱ ለሚማቅቁትና በየጫካው ለሚንከራተቱት የኦሮሞ ልጆች ለትንሽ ቀንም ቢሆን ስንቅ ሊሆን የሚችል ብዙ ሺህ ዶላር አውጥተው፣ ውቅያኖስንና አህጉሮችን አቋርጠው እንወጋዋለን ለሚሉት ጠላት እጅ የሚሰጡ አሳፋሪ ሰዎች ናቸው። እጃቸውን ከሰጡ በኋላ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ፣ በየመንግሥት እሥር ቤቶች የሚማቅቁ የኦሮሞ ልጆች ሳይፈቱ፣ እንፈታም ብለው ማንገራገር እንኳ ቢቀር እነሱን ለማስፈታት በፍርድ ቤት አካባቢ ተገኝተው የታሰሩት እንዲፈቱ ሳይጠይቁ ማመልከቻ ጽፈው "በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን" ብለው በመማጠን እንደተፈቱ ወደ ፈረንጅ ፍርፋሪ ለቀማቸው የሚመለሱ ጉደኞች ናቸው። እንዲህ ዓይነቶቹ የዘመናችን "ጆሉ ሞሮዎች"ና ጆሌዎቻቸው ናቸው እነፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን "አጋሰስ" ብለው የሚከሱት።

እስኪ እነዚህ ሌሎችን "በአጋሰስነት" የሚከሱ ጉዶችን ከእነራስ አበበ አረጋይ፣ ከነደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ ከጄኔራል ጃጋማ ኬሎ ተግባር ጋር ደግሞ እናወዳድራቸው። ራስ አበበ አረጋይ ወጨጫ ተራራ ላይ ሆነው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የመሸጉትን የጣሊያን ፋሽስቶች ዙሪያውን ከበው የገረፉ፣ ሀገሪቷንም ከጣሊያን ፋሺስቶች ነፃ ያወጡ የኢትዮጵያ አርበኞች ቁንጮ ነበሩ። ከሳሾቻቸው እነአብርሃም (አባ ጫላ) ለታ ግን ከመዲናችን በብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች ርቆ በደንቢ ዶሎ አካባቢ በሚገኘው የወለል ተራራ ላይ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆችን አስፈጅተው በሽሽት ወደ ሱዳን የፈረጠጡ ወኔ ቢሶች ናቸው።

ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ በሸዋና በከፋ እየተዘዋወሩ የፋሺስትን የጦር መንጋ ሲነዱ የነበሩ ጀግና ናቸው። በደፋሮች አንደበትና ብዕር "አጋሰስ" እየተባሉ የሚዘለፉት ጄንራል ጃገማ ኬሎ ሃያ ዓመት ሳይሞላቸው የአዲስ ዓለምን የጣሊያን ምሽግ የደመሰሱና ሕዝባችንን ከነጭ እንቁላል ተሸካሚነት ያዳኑ ጀግና ናቸው። እነዚህ ተሳዳቢዎች ለፈረንጆች ያላቸው ፍቅር ለኃይማኖታቸውም ካላቸው ታማኝነት የላቀ ስለሆነ ጣሊያንን መውጋት እንደጀብዱ ያለመቁጠራቸው አያስደንቀኝም። ጥያቄዬ ግን ሌላ ቢቀር እንዴት አያፍሩም? የሚለው ነው። ለመሆኑ በትክክል የአጋሰስ ሥራ ሲሰሩ የኖሩ እነማን ነበሩና ነው? የጎበናን ወደአካባቢያቸው መምጣት በስም ብቻ ሰምተው እንደአጋሰስ ወርቅ ሲሸከሙ የነበሩ የእነዚህ ሰዎች አባቶች አልነበሩም? የእነሱ ጉድ ሲሆን እንዲነገርም፣

እንዲነሳም አይፈልጉም እንጂ የአፍሪካ ሕዝብ የነፃነት ትግል በጀመረበት ታሪካዊ ወቅት መጀመሪያ እንግሊዝን "ነይና ግዥን" ብለው ማመልከቻ የፃፉ፣ እንግሊዝ እምቢ ስትል ለጣሊያን ፋሺስት አጋሰስ ሆነው እንቁላል ሲሸከሙ የነበሩ የእነሱ አባቶች አልነበሩም? በጥቁር አንበሳ ሥር ተሰባስበው የነበሩትን አርበኞች ያስፈጀስ ማነው?

ከ1950ዎቹ ጀምሮ ወደ ጉደኞቹ አካባቢ ለጎረፉት ሚስዮናውያን የ"መጽሐፈ ቁልቁሉ" ተሸካሚ አጋሰስ የሆነው ማነው? ሶሻሊዝም ትርፍ ያስገኛል ሲባል ደግሞ ከወንጌል ሰበካ ወደ ካድሬነት እጅግ አስገራሚ በሆነ ፍጥነት ተሸጋግረው የቀዩ መጽሐፍ ተሸካሚ አጋሰስ አልሆኑም? ለዚህ ነው ይህን ጽሁፌን "በመስታወት ቤት የሚኖር በሌሎች ላይ ድንጋይ ለመወርወር የመጀመሪያው አይሆንም" ያልኩት። እኔን በሚመለከት የ"ኡርጂ" እና የ"ሰይፈ ነበልባል" "ደራሲዎች" ወደሚቀባጥሩት ትርኪ ምርኪ እንመለስ። እኒህ የተውኔት ደራሲያን መረራ "የመኢሶን ካድሬ ነበር። የጅባትና ሜጫ አውራጃ የቀይ ሽብር ኮሚቴ እንዴት ዝም አለው?" በማለት የእሰሩልን ማመልከቻ ያቀርባሉ። እዚህ ላይ አንዳንድ ነገሮች ግልፅ መሆን ያለባቸው ይመስለኛል።

የመኢሶን አባል እንደነበርኩና በዚህም ምክንያት ለ7 ዓመታት እንደታሰርኩ የአደባባይ ምስጢር ነው። ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ወደ አምቦ ሜካ፣ ከዛም ወደ ልዩ ልዩ የደርግ እሥር ቤቶች ከመንከራተት በስተቀር ለአንድ ወር እንኳ ደመወዝ ያልበላሁበትን መረራን "ትርፍ ይኖራል" ብለው በገመቱበት አካባቢ ሁሉ እያፈነፈኑ አንዴ የመኢሶን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የኢጭአት ካድሬ የነበሩ፣ ዛሬ ኦነግ ሆነው ሲከሱኝ አስቂኝም፣ አሳዛኝም ነው።

ዛሬ በኦነግ ቁንጮ ላይ ሆነው ያለኛ ታጋይ የለም የሚሉት እነአብዩ ገለታ፣ እነ መኮንን ገላን የደርግ ዋና አስተዳዳሪዎች አልነበሩም? በሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆችን ለደርግ ሚሊሽያነት መልምለው፣ በጊዜው ኦነግ የነበሩትን እነጃራ አባ ገዳን ጭምር ሲያስወጉ የነበሩ ከፍተኛ የደርግ ካድሬዎች እኔን በቀይ ሽብር ተዋናይነት እንዴት ይከሱኛል? የኢትዮጵያ ወጣቶች በቀይ ሽብር በሚረገፉበት ጊዜ፣ እኔ ከአምቦ ተይዤ አዲስ አበባ ስመጣ እኔን በደረሰኝ ተቀብለው ለሞት ወደ ደርግ ጽ/ቤት የላኩኝ ዘመዳሞቹ የነቀምቴ ልጆች ሻምበል ሳሙኤል ኃይሉና የዛሬው የኦነግ ዋና ፀሐፊ ዮሐንስ በንቲ (ገላሣ ዲልቦ) በጊዜው የሸዋ ክፍለ ሀገር ካድሬዎች አልነበሩም? ዛሬ የአምቦ ሕዝብ የሚኮራበትና እኔም በግሌ አስተዋጽኦ ያደረግሁበት ጉዳይ ጅባትና ሜጫ አውራጃ ውስጥ ታላቅ ወንድሜን ጨምሮ እነ ዶ/ር ተረፈ ወልደፃድቅና ከበደ ድሪባ አልቀውበት እኔ ከሞት የተረፍኩብት ከመሆኑ በስተቀር ቀይ ሽብር ካልተካሄደባቸው በጣም ጥቂት ስፍራዎች ውስጥ አንዱ መሆኑ ሊካድ የሚችል አይደለም።

"ታሪክን አታንሱ አለን። ጎበና ለምን ተነካ አለ?" ይሉኛል። በመጀመሪያ ደረጃ ራስ ጎበናን በጥቅም የሚከሱ ከሆነ በየትኛውም ሚዛን ከጎበና ጋር ሊመዘኑ አይችሉም። እነሱም የማይክዱት ትልቁ ልዩነታቸው ግን ራስ ጎበና ጀግና መሆናቸውን ነው። የወንጃዮቼ ችሎታ ደግሞ በሚሊዮን ፀሎት ቤቶች መዝሙር ማቅለጥ ነው። እኔ "ከጎበና ሙት መንፈስ ጋር አትታገሉለ ያልኩበት" ላለፉት ሩብ ምዕተ ዓመት አካባቢ ሐቀኛ የኦሮሞ ልጆች ትግል አንድ እርምጃ ወደፊት በተራመደና የአወናባጆቹ ጥቅም በተነካ ቁጥር፣ በተለይም በእነሱ ውሃ ያላደጉና ያልተጠመቁ የኦሮሞ ልጆች አንዳንድ የአቋም ልዩነቶችን ሲያሳዩ፣ የተሻለ የፖለቲካ ችሎታም ብቃትም ስለሌላቸው ዘለው የሚጠቀሙበት የፈሪ በትር ስም ማጥፋት ስለሆነ ነው። "ከሙት መንፈስ ጋር አትታገሉ" የምለው የተሰበረ ሸክላ ሙዚቃ ስለሰለቸኝ ብቻ ሳይሆን ወደ ኋላ እንጅ ወደፊት ማየት የማይችሉ፣ ራዕይ(vision) የሌላቸው የፖለቲካ ዕውራን መሆናቸውን ስለማውቅም ነው። በዚህም ምክንያት የሕዝባችንን ብሔራዊ ጥቅምና መብት የበለጠ እያስደፈሩ ነው።

ሌላው ክሳቸው "የኦሮሞ ሕዝብ አልተጨቆነም፣ ከጠላቶቻችን ጋር እንኑር ትለናለህ" የሚል ነው። መረራ የኦሮሞ ሕዝብ አልተጨቆነም ይላል የሚለውን ተረት ከየት እንዳመጡት አይገባኝም። ክርስቲያን ነን እያሉ ለምን ሰውን በሐሰት እንደሚከስሱ አይገባኝም። የሕዝባችንን ጥያቄ በሚመለከት የእኔ ግልጽ አቋም፣

"1. ኢትዮጵያ ውስጥ ብሔራዊ ጭቆና ትናንት ነበር፣ ዛሬም አለ፣

2. የኦሮሞ ሕዝብ የተጣላው ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጋር ሳይሆን ትናንት ኢትዮጵያን ሲገዙ ከነበሩና አሁንም እየገዙ ካሉ ጨቋኝ ገዥዎች ጋር ነው።

3. የችግራችን መፍትሔም "ትናንት ከመንዝ ከተንቀሳቀሱና ዛሬም ከአድዋ ከመጡት ይልቅ አራት ኪሎ ለሚገኘው የምንልክ ቤተ መንግስት ለእኔ ይቀርባል ብሎ መከራከርና በኢትዮጵያችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት በሚደረገው ትግል መሳተፍ፣ ትናንት የኀደፈውንም ሆነ የወደፊቱን ታሪክ ለማስተካከል የተሻለ መንገድ ነው።" የሚል ነው።

እስቲ በእነዚህ ሀሳቦች ውስጥ ምን የኦሮሞ ሕዝብን ታሪካዊም ሆነ ፖለቲካዊ ጥቅሞች የሚፃረር ነጥብ አለ? ዴሞክራሲ የኦሮሞ ሕዝብን ያጠፋል ነው የሚሉት? ወይስ ከዚህ ቀደም እንዳነሳሁት "የደንቆሮዎች ውይይት" በመሰለ የሀሳብ ውዥንብር ውስጥ እየዳከሩ የራሳቸውን ሕልም ጽፈው፣ ራሳቸው እያነበቡ፣ በዚሁ በሚፈጥሩት መልካም ሕልም ሲፈነድቁ ለመኖር ይፈልጋሉ?

አንድ ሌላ የሚደጋግሙት ተረት አለ። "ከሐበሾች ጋር አብረን እንኑር እንዴት ትለናለህ?" ይላሉ። ከአባቶቻቸው፣ ከእናቶቻቸው ወይም ከሚስቶቻቸው ጋር እንዲኖሩ መጠየቅ ምን ችግር አለበት? እነ አብዩ ገለታን ከአማራ እምቻዎቻቸውና ዘመዶቻቸው እንዲሁም ሚስታቸው ጋር በአንድ ሀገር መኖራችሁ ይመረጣል ማለቴ እንዴት አስከፋቸው? የሚሉት እውነት ከሆነ እኔ የምለው "የምትሉትና የምትሰሩት አንድ ይሁን" ነው። ያለምክንያት አይደለም። ጉለሌ ላይ የኦሮሞ ሕዝብ ያለ ገዳ ሥርዓት አዳኝ የለውም ይሉናል። ትንሽ ፈቀቅ ሲሉ "ያለ ኢየሱስ አዳኝ" የለውም ብለው ይሰብካሉ። በከተማ ከሐበሾች ጋር በአንድ ሀገር እንኖርም እያሉ በቤተክርስቲያን "የእግዚያብሔር በጎች ሁሉ አንድ ናቸው" የሚል ስብከት አላቸው። አበሾች የእግዚአብሔር በጎች አይደሉም ልትሉን ይሆን?

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ ለመኖር የደቡብ አፍሪካ ዓይነት መፍትሔ ማግኘት ይቻላል ስባልኩ ብዙ ብዙ ተባለ። ራሳቸውን ማንዴላ፣ እኔን ቡቴሌዚ አድርገው ለማቅረብ ሙከራ እያደረጉ ነው። እስቲ የማን አቋም የቡቴሌዚን፣ የማን አቋም ደግሞ የማንዴላን እንደሚመስል እንመልከት። ቡቴሌዚ በነጮች ፍርፋሪ ያደገ፣ ነፃነት ሲመጣ የነጮቹ ፍርፋሪ እንዳይቀርበት አርበኛ መስሎ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር እያጋጨ፣ በጥቁር ሕዝብ ደም እየነገደ ለመኖር የሚፈልግ ተራ የፖለቲካ ነጋዴ ነው። ልክ እንደቡቴሌዚ እነዚህም በፈረንጅ ፍርፋሪ ያደጉና ወደፊትም እንዳይቀርባቸው የሚታገሉ ሆነው ነው የሚታዩኝ። ልክ እንደቡቴሌዚ እነዚህም ኦሮሞን ከኦሮሞ ጋር፣ ኦሮሞን ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እያጋጩ፣ በዚህም ምክንያት በሚፈሰው የኦሮሞ ሰፊ ሕዝብ ደምና እንባ እየነገዱ ለመኖር ይፈልጋሉ።

ማንዴላ ለ27 ዓመታት በእስር በመማቀቃቸው ቂም ሳይዙ "ከአውሮፓውያን ጋር ሳይቀር ብሔራዊ እርቅ ፈጥረን ለዛሬና ለነገው የደቡብ አፍሪካ ትውልድ የምትሆን ዲሞክራሲያዊት ደቡብ አፍሪካን መገንባት እንችላለን" የሚሉና የዓለምን የታሪክ ጉዞ የተረዱ፣ የደቡብ አፍሪካ ብቻ ሳይሆን የመላው ጥቁር ሕዝብ ጀግና ናቸው። እስቲ እኔን በቡቴሌዚ ሲመስሉኝ፣ ራሳቸውን በማንዴላ ለመመሰል ሲንጠራሩ እላይ ካስቀመጥኩት የሁለት ዓለም ሰዎች ሥራ የትኛው የእነሱን ይመስላል?

ማንዴላ ሆኖ ታሪክ ለመሥራት ወደ አገር ቤት የገባው ሌንጮ አይደለም እንዴ ወር የሞላ ጊዜ እንኳን ሳይታሠር "በሰላማዊ መንገድ እታገላለሁ" ብሎ ማመልከቻ ጽፎ ወደ መጣበት የፈረንጅ ሀገር የፈረጠጠው? ያልሆንኩትን ለመሆን የምፈልግ ግብዝ ባልሆንም "ብሔራዊ እርቅ ይፈጠር፣ ለዲሞክራሲዊ ሥርዓት መምጣት በጋራ እንታገል፣ የሁሉም ሕዝቦችዋ እኩልነት በተከበረባት ኢትዮጵያ አብረን መኖር እንችላለን" የሚለው የእኔ አቋም ለማንዴላ የሚቀርብ ይመስለኛል። በእርግጥ ማንዴላን ለመሆን በምኞት ሳይሆን የማንዴላን ሥራ በተግባር መሥራትና ለዛም ተገቢውን መስዋዕትነት መክፈል ያስፈልጋል። ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ችግርና አፈታቱ የሚሰማኝን ስለተናገርኩ በጋዜጦቻቸው ይሰድቡኛል። ሌንጮዎች እውነትም አንበሳ እንዲሆኑ የግድ መረራ የኦሮሞ ሕዝብ ጠላት መሆን አለበት? እኔ እንደማምንበት ግን ሌንጮ (አንበሳ) ለመሆን ከአውሮፓና ከአሜሪካ ይልቅ የሌንጮ ታናሽ ወንድም አብርሃም (አባጫላ) ለታ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆችን አሰፈጅቶና በትኖ የፈረጠጠበት ቱሉ ወለልን ጨምሮ የኦሮሞ መሬት ብዙ ተገቢና ተስማሚ ቦታዎች ያሉት ይመስለኛል። ኦሮሞ የሚፈልገው አንበሳ (ሌንጮ) እንደማሞ መዘምር ሞት አይፈሬ የሆነውን ጀግና ነው። ማሞ መዘምር ሞት ተፈርዶበት ለጃንሆይ ይግባኝ ጠይቅ ሲባል "አሽከር ፈርዶብኝ ወደ ጌታው ይግባኝ አልጠይቅም። ልነግራቸው የምፈልገው ግን ዛሬ እናንተ የፈረዳችሁብኝን ፍርድ ነገ የኦሮሞ ልጆች በመብራት ያነቡታል" ብሎ ሞትን ተጋፍጧል። ጧትና ማታ ልብወለድ ተረቶች ከመቸክቸክ፣ ስላለፈው የኦሮሞ ሕዝብ የትግል ታሪክ ለማወቅም ሆነ አዲስ ታሪክ በመሥራት ለሚታገለው አዲስ ትውልድ የማሞ መዘምርን ዓይነት የጀግንነት ታሪክ ብታቀርቡለት የሚሻል ይመስለኛል። የ"ሰይፈ ነበልባሉ" ሞቲ "የኦሮሞ ምሁራን የሀበሻ ገዥዎችን ተከትለውና የሚረግጡትን ረግጠው በመጓዝ የሕዝቦቻቸውን ጥቅሞች መሸጥ የለባቸውም። የታሪክም ሆነ የወቅታዊ ፖለቲካ ዕይታችን መሰረት ማድረግ ያለቢት የሕዝባችንን ዘላቂ ፍላጎትና ጥቅሞች እንጅ እገሌ ምን አለ? የሚል የአመለካከትና የአስተሳሰብ አሮጌ ፋሽኖች መሆን የለበትም" ይላል። እነዚህ እኔም የማምንባቸው ድንቅ ምክሮች ናቸው። ምክሩ ግን የሚመለከተው እኔን ሳይሆን የሚሻል ይመስለኛል። የ"ሰይፈ ነበልባሉ" ሞቲ "የኦሮሞ ምሁራን የሀበሻ ገዥዎችን ተከትለውና የሚረግጡትን ረግጠው በመጓዝ የሕዝቦቻቸውን ጥቅሞች መሸጥ የለባቸውም። የታሪክም ዕይታችን መሰረት ማድረግ ያለበት የሕዝባችንን ዘላቂ ፍላጎትና ጥቅሞች እንጅ እገሌ ምን አለ? የሚል የአመለካከትና የአስተሳሰብ አሮጌ ፋሽኖች መሆን የለበትም" ይላል። እነዚህ እኔም የማምንባቸው ድንቅ ምክሮች ናቸው። ምክሩ ግን የሚመለከተው እኔን ሳይሆን የኦሮሞ አርበኞች ነን የሚሉትን "የሞቲ ቢያ" አለቆችን ነው። እኔ አምቦ ውስጥ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን የዛሬ 33 ዓመት ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ የአካዳሚክ ሬኮርዴንም ሆነ ሌሎቹ ተሳትፎዎቼን በተመለከተ ቁልጭ ያለ የሕይወት ታሪክ ስላለኝ የምጨነቅበት ጉዳይ የለም።

የሻዕቢያ መሪዎች ሐበሾች አይደሉም ካልተባልን በቀር የሻዕቢያን መሪዎች ተከትለው፣ እነሱ የሚረግጡበትን የሚረግጡ፣ እነሱ የሚሉትን እንደገደል ማሚቶ መልሰው የሚያስተጋቡ፣ እነሱ በእንግሊዝኛ የሚናገሩ፣ ሌላው ቀርቶ የሻዕቢያን ቀጭን ትዕዛዝ በመቀበል በሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆችን ሰብስበው ካምፕ በማስገባት ያስጨረሱ የ"ሞቲ ቢያ" አለቆች ናቸው።

እስቲ የእነዚህን ሰዎች አንዳንድ ሥራዎች ዘርዘር አድርገን እንይ፣

1. 1972 ዓ.ም መጀመሪያ የኦሮሞ አርበኞች ነን ብለው የሚደነፉበት ጊዜ ነበር። ያኔ ዳንኤል ዳፋና ፍቅሩ ከበደ የሚባሉ የነዮሐንስ (ሌንጮ) ለታ አካባቢ ልጆች በኢጭአትነት ይያዛሉ። እነዚህ ሰዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆችን በጥቂት ቀኖች ውስጥ አሳፈሱ። የደርግ መርማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቶስም "ልባችን የደበቀውን ያያል" የሚሉ ስለነበሩ የሚያውቁትን ድርጅታዊ ምስጢሮች በሙሉ ዘከዘኩ። በተለይ የኦሮሞ ልጆች ልብ እንዲሉልኝ የምፈልገው፣ አብዛኛው ጥቆማዎች ይደረጉ የነበሩትና "ወንጀሎች" ሁሉ የተደፈደፉት ድርጅታዊ ምስጢርን ለመደበቅ በሞከሩ፣ ከአቋማቸውም ጋር ለመሞት በተዘጋጁ፣ ከሌሎች አካባቢ በመጡ የኦሮሞ ልጆች ላይ እንደነበር ነው። በውጤቱም ከእነሱ አካባቢ አንድ ሰው እንኳ ሳይገደል ከበደ ደምሴና መቶ አለቃ ይገዙ የሚባሉ የሸዋ ልጆች፣ የመላው ኢትዮጵያ ሰራተኞች ማኅበር ሁለተኛ ሰው የነበረውና ገዛኸኝ ካሣሁን የሚባለው የጅማ ልጅና በእኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የነበረው ሞሔ አብዶ የሚባል የአርሲ ልጅ ተመርጠው መገደል ምክንያት የደርግ መርማሪዎች ብቻ እንዳልነበሩም አያጠያይቅም።

በጫካ የነበረው ሁኔታም ቢሆን ከዚህ የተለየ አልነበረም። በአንድ ወቅት የኦነግ ሊቀመንበር የነበረው መገርሣ በሪ(የባሌ/ሸዋ? ልጅ)፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ተሳታፊ የነበረው ደምሴ ተጫኔ (የአርሲ ልጅ)፣ ወዘተ በዚሁ ሁኔታ ለሞት ተዳርገዋል። ከሱማሊያ ጋር በተደረገው ግጭት ከሞተ አንድ ሰው በስተቀር ከመቶ አለቃ ማሞ መዘምር ሞት ጀምሮ በኦሮሞ ጉዳይ የሞተና በስም የሚታወቅ የእነሱ ሰው ማነው? ሞት ወደእነሱ የማይጠጋው የሚሲዮናውያን ፀሎት እያዳናቸው ወይስ እነሱ ወደ ሞት ስለማይጠጉ? መልሱን እነሱን ለሚያውቁ የኦሮሞ ልጆች መተውን እመርጣለሁ።

2. እነ አብዩ ገለታና መኮንን ገላን በዋና አስተዳዳሪነት ደርግን ያገለገሉበት በኢጭአትነት ነበር። ያኔ ደርግ ወንጀላቸውን ከፍ ለማድረግ የኦነግ አባሎች ናችሁ ይላቸዋል። እነሱም ደርግ የሰጣቸውን ስም እንደ እውነት ይወስዱትና ክብራቸውን ከፍ ለማድረግ፣ ያውም በእነአቶ ጃራ ይመራ የነበረውን ኦነግን ሚሊሽያ መልምለው ሲያስወጉ የነበሩ ሰዎች ዘወር ብለው ኦነግ ነን ማለት ጀመሩ። በኢጭአትነት አለቃቸው ሆኖ ታስሮ በነበረው አቶ አሰፋ ጫቦ ላይ አሴሩ። "ለምን ኢጭአት ናቸው ትለናለህ" ብለት ተጣሉ። አቶ አሰፋ ጫቦም የአንድ ድርጅት ብቸኛ እሥረኛ ሆኖ ለአሥር ዓመታት ወህኒ ቆየ።

3. ከኢትዮጵያ አብዮት መፈንዳት በኋላ በአንዳንድ የኦሮሞ ልጆች የተፈጠረ "ኦሮሚያ" የሚባል ቡድን ነበር። እኔ እስከማውቀው ድረስ ለመጀመሪያ ጊዜ "ኦሮሚያ" የሚለውን ስያሜ የተጠቀመውን የዚህን ቡድን መሪ "ከደርግ ጋር አብረን በመሥራታችን በኅበናንት እየከሰሰን አላሰራ አለን" ብለው ያሳስሩታል። ከፍተኛ የስም መጥፋት ዘመቻም ያካሂዱበታል። ዛሬ ሰውዬው እዚሁ አዲስ አበባ ስላለ ለሚፈልጉ ሁሉ ዝርዝር ሁኔታውን ሊያስረዳ ይችላል ብዬ እገምታለሁ። ይህ ሰው ከብዙ ዓመታት በኋላ ከእስር ቤት ሲወጣ፣ አሳሳሪዎቹ "ኦሮሚያ" ብለው የሚዘፍኑና የሚያዘፍኑ ሆነው ብቅ አሉ።

4. ከሁለት ዓመት በፊት የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት፣ ካርተር አትላንታ ላይ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ልዩነቶቻቸውን አቻችለው እንዲደራደሩ በጋበዙዋቸው ጊዜ እነዚሁ ሰዎች አንድ አስቂኝ ድራማ ሰሩ። ካርተር ተቃዋሚዎች ሁሉ የመነጋገሪያ አጀንዳችሁን አቅርቡ ይላሉ። ኦነግን ወክለው የሄዱት እነአብዩ ገለታ "ከነፍጠኛ ተቃዋሚዎች የተለየ ጉዳይ ስላለን ለብቻ ካልሆነ በስተቀር ጥያቄአችንን አናቀርብም" ይላሉ። በጣም ግራ የገባቸው የፈረንጅ ሽማግሌ "እሺ ለብቻችሁም ቢሆን አቅርቡ" ይላሉ። እነሱም ያቀርባሉ። ተስፋ ያልቆረጡት ካርተር ተቃዋሚዎችን ለማቀራረብ ምሣ አብረው እንዲበሉ ይጋብዙአቸዋል። አሁንም እነአብዩ ገለታ "ከነፍጠኞች ጋር ደመኞች ስለሆን፣ ከእነሱ ጋር አንበላም" ይላሉ። ይህን ዓይነቱን የማስመሰል ድራማ የሚሰሩት ሌሎች ሳይሆኑ ከአማራ የተዛመዱና ከአማራ ሴት ልጆች የተወለዱ እነአብዩ ገለታ ናቸው።

5. በ1984 ዓ.ም የኢህአዴግና የኦነግ ጊዜያዊ ፍቅር አልቆ፣ በአንዳንድ ቦታዎች ግጭቶች እየተካሄዱ እነዮሐንስ(ሌንጮ) ለታ ያስወሩ የነበረው "በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኮማንዶዎችን አዲስ አበባ ውስጥ አሰማርተናል። የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ እንዳይጎዳ ፈርተን ነው እንጂ በአራት ኪሎ ላይ ያነጣጠረ ከባድ መሣሪያ አለን። ወደ መቶ ሺ የሚገመት ሠራዊት አዲስ አበባ አካባቢ አለን፣ ወ.ዘ.ተ." የሚል ነበር። በመጨረሻ ያየነው ግን "አዲስ አበባ ከተማ የነበረው ኮማንዶ" እርምጃ ሲወስድ ወይም "መቶ ሺው ጦር ወደ አዲስ አበባ ከተማ ሲንቀሳቀስ ሳይሆን እነአቶ ሌንጮ በሥነ ሥርዓት ቢሮ በደረሰኝ ሲያስረክቡ፣ ጀግኖች ወደሚሄዱበት ባሌ ሳይሆን ወደ ቦሌ ሲከንፉ ነበር። የኦነግ አመራር አባላት በአደባባይ ጥያቄ ሲቀርብላቸው የሚጨንቃቸው ቢሆንም እኔ አንድ ነገር ልጠይቃቸው። ከእነሱ ጋር ለመሞት ለተዘጋጁት የኦሮሞ ልጆች እንዲህ ዓይነቱን አሳፋሪ የውሸት ወሬ ማስወራት ለምን አስፈለገ?

6. ከሁሉም በላይ የሚገርመው ደግሞ እነዮሐንስ(ሌንጮ) ለታ በአንድ ወገን ኢህአዴግን እንወጋለን እያሉ በሌላ ወገን ደግሞ ፓስፖርትና ቪዛ ለማስወጣትና የአይሮፕላን ትኬቶችን ለመግዛት ሲያደርጉት የነበረው መሯሯጥ ነው። ኢህአዴግ እንደገባ የወጡትን የአቶ ሌንጮ ለታ ቤተሰቦችና ኦነግ ከሽግግር መንግሥቱ ከመውጣቱ በፊት የወጡትን የታደሰ ኤባ ቤተሰቦችን ጨምሮ ከ250 ያላነሱ ዘመድ አዝማዶቻቸውን ከኦሮሞ ሕዝብ ጉሮሮ ተነጥቆ በተሰበሰበ ገንዘብ ትኬቶች እየተገዙ፣ የቤት ጓደኞቻቸውን ሳይቀር ካሸጋገሩ በኋላ ራሳቸውም ወደ አውሮፓና አሜሪካ ለመሄድ እየተዘጋጁ እያሉ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆችን ከሥራ ገበታቸውና ከትምህርት ላይ ያለ ዝግጅት፣ ያለስንቅ፣ ያለትጥቅ፣ ወደ ጫካ ሸኝተው ወደ ለሰለሰው የፈረንጅ ኑሮ የበረሩበት ትያትር ከሁሉም በላይ አስገራሚ ነበር። እንዲህ ዓይነቶቹ ተራ ሰዎች ናቸው "ያለእኛ የነፃነት ታጋይ የለም" ብለው ሊያሳምኑ የሚባዝኑት።

በእኔ ላይ ወደሚሰነዘሩት ክስ ልመለስ። "ተለዋዋጭ አቋም አለህ" ይሉኛል። "አንድም ቀን የተስተካከለ አቋም ያልነበራቸው፣ እንደገበቴ ውኃ ሲዋልሉ የኖሩ ናቸው" ተብሎ ስለእኔ ተጽፏል። እኔ ላለፉት ሩብ ምዕተ ዓመታት በብዙ ሺ በሚቆጠሩ ሰዎች ዘንድ የሚታወቅ የፖለቲካ ሕይወት አለኝ። በራሳቸው ብዕርም የዛሬ 20 ዓመት የመኢሶን አባል እንደነበርኩ፣ ዛሬም "የመኢሶን መርዝ አልለቀቀውም" የተባልኩ ስለሆነ ቢያንስ፣ ቢያንስ "ተለዋዋጭ አቋም አለው" ተብዬ የምከሰስ አይመስለኝም። እኔንም እነሱንም የሚያውቁ የኦሮሞ ልጆች ሊመሰክሩ እንደሚችሉትም መኢሶን ሲዳከም ወደ ኢጭአት፣ ኢጭአት ሲመታ ወደ ኢሠፓና ኦነግ፣ ኦነግ መመታት ሲጀመር ወደ ኦነግ/ኦህዴድ፣ የሁለት ዓለም መሥራት ሳይቻል ሲቀር ወደ ሙሉ ኦህዴድነትም በመለዋወጥ ትርፍ በተገኘበት ቦታ ተጠራርተው የሚሰፍሩ የኦሮሞ የእንግዴ ልጆች ናቸው።

ይህም ብቻ አይደለም ሃይማኖት ትርፍ ሲያመጣ ወደ ሚሲዮን ፀሎት ቤቶች፣ ሶሻሊዝም ትርፍ የሚያመጣ መስሎ ሲታይ ወደ ካድሬነት፣ ሳሻሊዝም አላተርፍም ሲል ተመልሶ ወደ ሚሲዮን ፀሎት ቤቶች፣ ትንሽ ቆይቶ በብሔረሰብ መደራጀት ጥቅም ማስገኘት ሲጀምር ወደ ኦነግና ኦህዴድ የጎረፉት እነሱ ናቸው። ከዚህ በላይ ምን ተለዋጭነት አለ?

"መረራ የሚታገለው ለጥቅም ነው" ብለው አንድ መቶ አንድ ቦታዎች ደጋግመው ጽፈዋል። አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ማስተማርና በሙያዬና በችሎታዬ ተጠርቼ በምካፈልባቸው አለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ መገኘት እንደወንጀል ካልተቆጠረብኝ በቀር ምን ሌላ ጥቅም እንዳገኘሁ አይገባኝም። ነገሩ "ሌባ እናት ልጅዋን አታምንም" ዓይነት ስለሆነ የችግሩ ምንጭ ግልፅ ነው።

ማን በኦሮሞ ሰፊ ሕዝብ ደምና እንባ እንደሚነግድ ብዙ ማለት ይቻላል። በኬንያ የኦነግ መሪዎች የሚንደላቀቁባቸው ምርጥ ሆቴል ቤቶችና በናይሮቢ ከተማ የሚርመሰመሱ ማታቱዎች (Minibuses)፣ በነባሮ ቱምሣ ቤተሰብ የሚንቀሳቀሰው የጀርመኑ የገበያ አዳራሽ (supermarket) የነአቶ ዮሐንስ(ሌንጮ) ለታ የካናዳ የተደላደለ ኑሮ፣ የነታደሰ ኤቦ ቤተሰቦችን ጨምሮ ብዙ የአካባቢያቸው ልጆች የሚንፈላሰሱባቸው የሚኒስታ ቪላዎች፣ የእነአብዩ ገለታ የተቀማጠለ ኑሮ የሚቀጩበት የዋሽንግተን ዲሲው የ"ኦሮሞ ማዕከል" እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ከሕዝብ በተዘረፈ ገንዘብ የሚነገድባቸው ሆቴል ቤቶች፣ ዳቦ ቤቶች፣ የጭነት መኪናዎች፣ በተለይም የነባቶ ቱምሣ ቤተሰቦች ከባለጊዜዎች ጋር የሚምነሸነሹባቸው አዳዲስ ሞዴል ኮብራዎችና ማርቼዲስ መኪኖች ምስክሮቼ ናቸው። በዚህ ምክንያት ነው ከእንግዲህ በኦሮሞ ሕዝብ ደምና እንባ የሚካሄደው የደራ ንግድ ማብቃት አለበት የምለው።

"እነ መረራ ቫይረሶች ናቸው" ይላሉ። ይህ እጅግ በጣም አስቂኝ ክስ ነው። በኢትዮጵያ ምድር ብቻ ሳይሆን በኬንያ፣ በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በካናዳ ከተሞች ሁለት የኦሮሞ ልጆች ተገናኝተው ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ችግር ሲጠያየቁ፣ "የኦሮሞ ሕዝብ ቫይረስ ማነው?" ለሚለው ጥያቄ ከሚሲዮን ፀሎት ቤቶች አካባቢ ከተወለዱት በስተቀር በአነስተኛ ግምት ከ90% በላይ የሚሆኑት የሚሰጡት መልስ "እነዚያው የሚሲዮን ዲያቆኖች ናቸው" የሚል ነው። እጅግ በጣም አስቀያሚ መሆንዋን የማታውቀው ዝንጀሮ አንድ ቀን መስታወት ውስጥ ምስሉዋን ታይና "እንዲህ አስቀያሚ ብሆን ኖሮ ራሴን ሰቅዬ እገድል ነበር" አለች ይባላል። እስኪ እነሱም አቋምና ተግባሮቻቸውን ይመርምሩ፣ ለማንኛውም ለማያውቋቸው የኦሮሞ ልጆች የነፃነት ታጋይ ይምሰሉ እንጂ ከእኔ ጋር በሚገባ እንተዋወቃለን።

"መረራ ፖለቲካ የማይገባው ፕሮፌሰር ነው" አሉ። ፕሮፌሰርነቱንም የሰጡኝ "የጠቢያ ነፍጠኞች" እንደሆኑ አድርገው ደሰኮሩ። እሱን ለታዛቢ እንተወውና አንድ ጥያቄ ልጠይቃቸው። ለመሆኑ የእኔን ትምህርት ስታናንቁ "በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠረውን የኦሮሞ ሕዝብ ወደ ድል እየመራ ነው" የምትሉት ዮሐንስ በንቲ (ገላሣ ዲልቦ) አንደኛ ዓመት (Freshman) እንኳን እንዳልጨረሰ ልብ ብላችኋል? ወይስ አንደኛ ዓመት ባይጨርስም የወንዛችን ልጅ የግድ መብለጥ አለበት ነው የምትሉት?

"በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በሚያስተምሩ ምሁራን ዘንድ አንተ ክብርና ሞገስ አግኝተህ የኛዎቹ "ሐቀኛ" የኦሮሞ ልጆች ብዙ ጥናትና ምርምር እያደረጉ ጥላሸት ይቀባሉ" ተባልኩ። በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ያለነው በደንብ ስለምንተዋወቅ ችግር ያለ አይመስለኝም። እዚህ ላይ ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የምናውቃቸው ለነኡርጂ የቦርድ አባሎችም ሆነ ርካሽ ዝናን ፍለጋ ለነኡርጂ አቤቱታ ለሚያቀርቡት አንድ መልዕክት አለኝ። ዛሬ በሞቀበት ለመዝፈን ሙዚቃችሁን ብትቀይሩም ትናንት

"መኢሶን በአካባቢያችን ይንቀሳቀስ በነበረበት ጊዜ አብዛኞዎቻችሁ ቢያንስ የመኢሶን ወረቀት በታኞች እንደነበራችሁና አንዳንዶቻችሁም ሳንቃችሁ እስኪሰነጠቅ "መኢሶን ያሸንፋል!" ያላችሁ የመኢሶን ካድሬዎች እንደነበራችሁ፣ እንዲሁም ከአራት ዓመት ተኩል በፊት ማናችሁም የኦነግ አባል ያልነበራችሁ መሆኑ ብቻም ሳይሆን ጠላትም እንደነበራችሁ መረሳት የለበትም።

መቼም እነዚህ ሰዎች ዋና ትግላቸው ወደ እኔ ዞሯል። ከጥቁሮች አልፈው ፈረንጆችም እንዲያውቁላቸው ነው ይመስለኛል ለመጀመሪያ ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባወጡት የኡርጂ ጋዜጣ ላይ እኔ ያቀረብኩትን "የአንድ ሰው፣ አንድ ድምፅ" ዴሞክራሲያዊ መፍትሔ ተቃውመዋል። በሀገር ውስጥም ሆነ በደቡብ አፍሪካ፣ በፈረንሳይ፣ በኔዘርላንድ፣ በእንግሊዝ፣ በናይጄሪያና በአሜሪካ፣ ወዘተ በተሳተፍኩባቸው አለም አቀፍ የጥናት ስብሰባዎች ላይ ብቻም ሳይሆን ምናልባትም ከኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ የተሻለ አድማጭ ባለው የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ "እስካሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አልተመሠረተም። የአሁኑ መሪዎቻችን ከዚህ በፊት የነበሩ መሪዎች የሰሩአቸውን ስህተቶች በቪዲዮ እያዩ እንደሚደግሙ በሚመስል ሁኔታ እየሠሩ ይመስለኛል" ብያለሁ።

እነሱ ግን እ.ኤ.አ. በ1992 ሲካሄድ የነበረው ምርጫ በሻዕቢያና በወያኔ ሲጨናገፍ ለሥራ ጉብኝት ወደ ክልል አንድ ሄደህ ነበር ወይ የሚል ጥያቄ ይጠይቁኛል? አንባቢ ልብ እንዲያደርግልኝ የምፈልገው ከሚያመልኩበት "መጽሐፈ ቁልቁሉ" ቀጥሎ በሻዕቢያ የሚያምኑት እነዮሐንስ ለታ ምርጫው በሰላማዊ መንገድ እንዳያልቅ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆችን ከመሸጉባቸው ጫካዎች በሥነሥርዓት ሰብስበው ወደ ኢህአዴግ ማጎሪያዎች ያስገቡ፣ በዚህም የተነሳ በሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆች እንዲያልቁ^ ይቅሩትም ብምንግሥት እሥር ቤቶች እንዲማቅቁ ያድረጉ ሰዎች መልሰው እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ሲጠይቁኝ እንዴት አያፍሩም? የኦሮሞን ሕዝብ ክብር በሚነካ መንገድ እስካሁን የሻዕቢያን ደጅ መጥናት ያላቋረጡ ሆነው ሳለ የተገላቢጦሽ እንዴት እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ይጠይቁኛል? ሻዕቢያን ለማስደሰት ሲሉ በፈረንጅ ቋንቋ የሚናገሩ፣ ከሙያቸው ውጭ በኤርትራ የተቀበሩትን የኢትዮጵያ ልጆች አፅም ለይተው እንደሚያውቁ ሁሉ የኦሮሞንና የአማራን አጥንት ለይተው ሲቆጥሩ የነበሩ የሻዕቢያ ታማኝ አገልጋዮች ዛሬ እንዴት የሻዕቢያ ጠላትነት ታያቸው? በምርጫው ጊዜ እነሻዕቢያ ምን ይሰሩ እንደነበር ዮሐንስ (ሌንጮ) ለታ ለምን አይጠይቁትም? "የሚሰሩትን ስለማያውቁ ይቅር በላቸው" ከማለት በስተቀር ምን ለማለት እችላለሁ?

እኔን ለመቃወም ብለው ስለሻዕቢያና ወያኔ የፃፉትን ሳነብ በጣም አዘንኩላቸው። "ነፃነቱን የተገፈፈ ሕዝብ በጠላቱ ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት ቀላል እንዳልሆነ የሕዝቦች ትግል ታሪክ ያስረዳል።

የኤርትራ ሕዝብ ግዙፍ ሠራዊቴ የነበረውን የኢትዮጵያን መንግሥት የጣለው ከ30 ዓመታት በላይ ተዋግቶ ነው። የትግራይ አማፅያን ወገናቸውን የአቢሲኒያን ገዥ መደብ በመጣል ከሃያ ዓመት በላይ የትጥቅ ትግል አካሂደዋል።" የሚል ውዳሴ አንብቤአለሁ። ከማን ጋር እንደሚታገሉ ከገባቸው ጥሩ ነው። እንደዚህ ዓይነቱን መያዣና መጨበጫ የሌለው ጽሁፍ የሚሞነጫጭሩት በእንሱ ቤት "ለኦሮሞ ልጆች መብትና ነፃነት እየታገልን ነው" ለማለት ነው።

ልጅ ሆኜ በጣም አስቸጋሪ ውሻ የነበራቸው አያቴ ሁልጊዜ ሲያስጠነቅቁኝ "ያበደች ውሻ የቤትና የውጭውን ሰው ለይታ ስለማታውቅ ተጠንቀቅ" ይሉኝ ነበር። እነዚህም አስቸጋሪ ወንድሞቻችን ከእነሱ የተለየ አቋም ያላቸውን የኦሮሞ ልጆች ጨምሮ በኢትዮጵያ ምድር የማይነክሱት የለም። አውሮፓና አሜሪካ ተቀምጠው ጀኔራል ዋቆ ጉቱን፣ ጃራ አባ ገዳን፣ የአቋም ልዩነት ያሳዩትን የእብሰአ ልጆች፣ ያለነሱ ፈቃድ መዝገበ ቃላት ያዘጋጁትን አንድ የሐረር ኦሮሞ ምሁር፣ በአጠቃላይ ከእነሱ አካባቢ ያልተወለደውንና ለእነሱ ፍላጎት ያልተገዛውን ሁሉ ይኮንናሉ። ሌላው ቀርቶ እነሱ ሳይወለዱ የሜጫና ቱለማ መሥራች የነበሩት አዛውንት ኮሎኔል ዓለሙ ቂጤሳ ለአሜሪካ ድምፅ በሰጡት ቃለ ምልልስ "በእኩልነት ተከባብሮ አብሮ መኖር ይቻላል" በማለታቸው ኤች ኪው ሎክቱ የተባለ የኡርጂ "ፀሐፊ" የሚከተለውን ሽሙጥ ጽፎ ነበር።

"ከዚህ ቀደም ከተለያዩ የኢትዮጵያ የአገዛዝ ሥርዓቶች ጋር በተለያየ መልኩ የሰሩና ያገለገሉ፣ በዕድሜ የገፉ የኦሮሞ ፖለቲከኞችና ምሁራን በዛሬዎቹ የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ወይም እርምጃ ለመውሰድ ያ የቀድሞው ሕይወታቸው፣ ልምዳቸውና በአእምሮዋቸው ውስጥ ተቀርጾ የቀረበው አስተሳሰባቸው ተፅዕኖ ስለሚያደርግባቸው የኦሮሞ ሕዝብ የፖለቲካ ትግል አመራር በዕድሜ ከገፉት እጅ ወጥቶ በወጣት ምሁራን እጅ መግባት አለበት።" (ኡርጂ፣ መስከረም 29/1988 ዓ.ም እትም)

ለማያውቃቸው "ምንም ንክኪ የሌለብን የኦሮሞ ብርቅዬ ልጆች እኛ ብቻ ስለሆን፣ እኛን ብቻ ስሙ" ባዮች ናቸው። ከሁሉም የሚያሳዝነው ግን ያለችሎታቸው የኦሮሞ ሕዝብ መሪ ለመሆን፣ ሃይማኖታቸውንም የኦሮሞ ሕዝብ ሃይማኖት ለማድረግ የሌሎችን የኦሮሞ ልጆች ታሪክ አጥፍተው ለራሳቸው አዲስ ታሪክ ለመፃፍ የሚያደርጉት መባዘን ነው። እዚህ ላይ በተለይ የኦሮሞ ልጆች ከሰይፈ ነበልባል የታህሣሥ 5 ቀን 1988 እትም የወሰድኩትንና ከዚህ በታች የሰፈረውን ሀሳብ ልብ እንዲያደርጉልኝ እፈልጋለሁ። "ዛሬ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላቸውን እውቅ ምሁራን ያፈራው ይህ ት/ቤት (የደንቢዶሎ ሚ^ዋን ት/ቤት ነው) ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ምርጥ ፖለቲከኞችን፣ ተዋጊ ጀኔራሎችን፣ ሐኪሞችን፣ ፓይለቶችንና በበርካታ ሙያ ላይ የተሰማሩ ታዋቂ ግለሰቦችን

ማፍራቱን በቀደሙት ጊዜያት ከተለያዩ የአውሮፓ ሀገሮች ወደ አካባቢው ተጉዘው ወጣቱን በትምህርት ሲኮተኩቱ የነበሩት የውጭ ሀገር ዜጎች ሳይቀሩ በኩራት ይናገራሉ።"

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ት/ቤቱን ያሰሩት አባት ቄሶች ስም ከታዋቂ ልጆቻቸው ጋር ተዘርዝሯል። ጋዜጣውን የጠቀስኩት የአንድ ሚሲዮን ት/ቤት ታሪክ ቁም ነገር ስላለው ሳይሆን በተባሉበት ሀሳቦች ውስጥ ብዙ የሚያጠያይቁ ነገሮች ስላሉ ነው። እስኪ ጥቂት ጥያቄዎችን አብረን እንጠይቅ።

1. የነፃነት ታጋዮቻችን የነማን ልጆች ናቸው?
2. የነፃነት አርበኞቻችን የየትኛው ት/ቤት ምሩቃን ናቸው?
3. ዛሬ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላቸው እውቅ ምሁራን የሚሉን እነማንን ነው?
4. ት/ቤቱ ያፈራቸው "ምርጥ ፖለቲከኞች" እነማን ናቸው?
5. ት/ቤቱ ያፈራቸው ተዋጊ ጄኔራሎችስ?

እነዚህ ጥያቄዎች በለሆሳስ የሚታለፉ አይደሉም። በተለይ እነፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን፣ ራስ አበበ አረጋይን፣ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪን፣ ጄኔራል ጃጋማ ኪሎን፣ ፈረንጅም ጥቁርም የሚያውቃቸውን የኦሮሞ ጄኔራሎች "ለሐበሻ መንግሥታት ያገለገሉ አጋሰሶች ናቸው" ብለው የሚጽፉ ሰዎች ዛሬ ሰምተን ስለማናውቃቸው ጄኔራሎች ልብወለድ ታሪክ ሲተርኩልን የሚሉንን ማመን በጣም ያስቸግራል። የተባሉት ጄኔራሎች ካሉም መቼም እስከ ጄኔራልነት ማዕረግ የደረሱት ለእነዚሁ "ለሐበሻ መንግሥታት" በሰጡት አገልግሎት ነው። የተባሉት ጄኔራሎች ካሉ ጸሐፊዎቹ እንደሌሎቹ ሁሉ "አጋሰሶች" የማይሏቸው ሚዛናቸው ወንዝ አለዚያም ሃይማኖት ስለሆነ ብቻ መሆን አለበት።

እነዚህ በኦሮም ስም የሆነ ያልሆነውን የሚሞነጫጭሩ ሰዎች የወንዝ ልጅነትና የሃይማኖት ጨዋታ መላው ጥቁር ሕዝብ ልቡ ተሰልቦ የነጭ ባሪያ የሆነበት መሠረታዊ ምክንያት እንደሆነ ያውቁ ይሆን? ለመላው ጥቁር ሕዝብ የማይረሳ ትምህርት አስተምረው ያለፉት ስመጥር የአፍሪካ ልጆች ከዋሜ ንክሩማህ፣ አሚልካል ከብራል፣ ሰሞራ ማሼል፣ ፍራንስ ፋኖን፣ ወዘተ፣ ስለጭ ሚሲዮናውያን የፃፉትን እነሱ ረስተው ሊያስረሱን ይሞክራሉ። የኬንያው የነፃነት አርበኛ ጆሞ ኬንያታ በአንድ ወቅት፣

"ነጭ ቅኝ ገዥዎች ሲመጡ፣ እነሱ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እኛ መሬት ነበረን። ዓይናችንን ጨፍነን እንድንፀልይበት መጽሐፍ ቅዱስ ሰጡን። ፀሎቱን ጨርሰን ዓይናችንን ስንከፍት እኛ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ተሸክመን ቀረን፣ እነሱ መሬታችንን ወሰዱ። ብለው ስለሚሲዮናውያን ሚና ለጥቁር ሕዝብ የሰጡት ምስክርነት ዛሬም ሕያው አይደለምን? የእኛ ጉዶች ሊያስረሱን የሚፈልጉት ይህንን ነው።

የኤርትራ ሕዝብ ግዙፍ ሠራዊቴ የነበረውን የኢትዮጵያን መንግሥት የጣለው ከ30 ዓመታት በላይ ተዋግቶ ነው። የትግራይ አማፅያን ወገናቸውን የአቢሲኒያን ገዥ መደብ በመጣል ከሃያ ዓመት በላይ የትጥቅ ትግል አካሂደዋል።" የሚል ውዳሴ አንብቤአለሁ። ከማን ጋር እንደሚታገሉ ከገባቸው ጥሩ ነው። እንደዚህ ዓይነቱን መያዣና መጨበጫ የሌለው ጽሁፍ የሚሞነጫጭሩት በእንሱ ቤት "ለኦሮሞ ልጆች መብትና ነፃነት እየታገልን ነው" ለማለት ነው።

ልጅ ሆኜ በጣም አስቸጋሪ ውሻ የነበራቸው አያቴ ሁልጊዜ ሲያስጠነቅቁኝ "ያበደች ውሻ የቤትና የውጭውን ሰው ለይታ ስለማታውቅ ተጠንቀቅ" ይሉኝ ነበር። እነዚህም አስቸጋሪ ወንድሞቻችን ከእነሱ የተለየ አቋም ያላቸውን የኦሮሞ ልጆች ጨምሮ በኢትዮጵያ ምድር የማይነክሱት የለም። አውሮፓና አሜሪካ ተቀምጠው ጄኔራል ዋቆ ጉቱን፣ ጃራ አባ ገዳን፣ የአቋም ልዩነት ያሳዩትን የእብሰአ ልጆች፣ ያለነሱ ፈቃድ መዝገበ ቃላት ያዘጋጁትን አንድ የሐረር ኦሮሞ ምሁር፣ በአጠቃላይ ከእነሱ አካባቢ ያልተወለደውንና ለእነሱ ፍላጎት ያልተገዛውን ሁሉ ይኮንናሉ። ሌላው ቀርቶ እነሱ ሳይወለዱ የሚጫና ቱለማ መሥራች የነበሩት አዛውንት ኮሎኔል ዓለሙ ቂጤሳ ለአሜሪካ ድምፅ በሰጡት ቃለ ምልልስ "በእኩልነት ተከባብሮ አብሮ መኖር ይቻላል" በማለታቸው ኤች ኪው ሎክቱ የተባለ የኡርጂ "ፀሐፊ" የሚከተለውን ሽሙጥ ጽፎ ነበር።

"ከዚህ ቀደም ከተለያዩ የኢትዮጵያ የአገዛዝ ሥርዓቶች ጋር በተለያየ መልኩ የሰሩና ያገለገሉ፣ በዕድሜ የገፉ የኦሮሞ ፖለቲከኞችና ምሁራን በዛሬዎቹ የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ወይም እርምጃ ለመውሰድ ያ የቀድሞው ሕይወታቸው፣ ልምዳቸውና በአእምሮዋቸው ውስጥ ተቀርጾ የቀረበው አስተሳሰባቸው ተፅዕኖ ስለሚያደርግባቸው የኦሮሞ ሕዝብ የፖለቲካ ትግል አመራር በዕድሜ ከገፉት እጅ ወጥቶ በወጣት ምሁራን እጅ መግባት አለበት።" (ኡርጂ፣ መስከረም 29/1988 ዓ.ም እትም)

ለማያውቃቸው "ምንም ንክኪ የሌለብን የኦሮሞ ብርቅዬ ልጆች እኛ ብቻ ስለሆን፣ እኛን ብቻ ስሙ" ባዮች ናቸው። ከሁሉም የሚያሳዝነው ግን ያለችሎታቸው የኦሮሞ ሕዝብ መሪ ለመሆን፣ ሃይማኖታቸውንም የኦሮሞ ሕዝብ ሃይማኖት ለማድረግ የሌሎችን የኦሮሞ ልጆች ታሪክ አጥፍተው ለራሳቸው አዲስ ታሪክ ለመፃፍ የሚያደርጉት መባዘን ነው። እዚህ ላይ በተለይ የኦሮሞ ልጆች ከሰይፈ ነበልባል የታህሣሥ 5 ቀን 1988 እትም የወሰድኩትንና ከዚህ በታች የሰፈረውን ሀሳብ ልብ እንዲያደርጉልኝ እፈልጋለሁ። "ዛሬ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላቸውን እውቅ ምሁራን ያፈራው ይህ ት/ቤት (የደንቢዶሎ ሚስዎን ት/ቤት ነው) ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ምርጥ ፖለቲከኞችን፣ ተዋጊ ጄኔራሎችን፣ ሐኪሞችን፣ ፓይለቶችንና በበርካታ ሙያ ላይ የተሰማሩ ታዋቂ ግለሰቦችን

ድርጅት የሚያንቀሳቅሱት የባሮ ቱምሣ ቤተሰቦች፣ እኔ ባየሁበት ጊዜ ከአሥራ ሁለት ማቱታዎች (minibuses) በላይ ያሉት የኬንያው የንግድ ተቋም ኃላፊ፣ መኮንን ገላን፣ እዚሁ የምናያቸው የ"ኡርጂ"ና የ"ሰይፌ ነበልባል" አዘጋጆችና የቦርድ አባላት አሁን የተዘጋው የኦራ (ORA) ኃላፊዎች፣ ወዘተ፣ የአንድ አካባቢና የአንድ ፀሎት ቤት ልጆች ናቸው። በነገራችን ላይ እነሱ ይህን ሁሉ እያንቀሳቀሱ ነው የሸዋ ልጆች የልማት ማኅበር ሲያቋቁሙ "ኀበናዎች ተደረጁ" ብለው ሲንጫጩ የነበረው። በአጭሩ ጥቂትና የአንድ አካባቢ ልጆች የኦሮሞን ሕዝብ ንቅናቄ ወደ ሃይማኖት ማዕከልነትና ወደየግል ንግድ ካባንያነት ለውጠዋል ማለት ይቻላል። እንግዲህ በእነዚህ ሰዎች ዘንድ የእኔ ዋና ወንጀል ገበናቸውን ማወቄና የሚያካሂዱትን አፍራሽ ተግባር ከማይቀበሉና ከሚቃወሙ የኦሮሞ ልጆች ውስጥ አንዱ መሆኔ ነው።

የማጠቃለያ ሃሳብ ከመስጠቴ በፊት ብዙ የኦሮሞ ልጆች ብቻም ሳይሆን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እንቆቅልሽ ስለሆነው ጉዳይ አስተያየቴን ልስጥ። የአንዳንድ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ጦር ሳይኖራቸው ጦርነት አውጃችኋል ተብለው በሚወነጀሉበት፣ ጋዜጠኞች ስለሌለው ጦርነት ፃፋችሁ፣ ሕዝቡን ለጦርነት ቀሰቀሳችሁ እየተባሉ በሚታሰሩበት ሀገር፣ ምንም ጠመንጃ የሌላቸው የኢትዮጵያ ሠራተኞች መሪ አቶ ዳዊ ኢብራሒም ወደ ውጭ እንዳይወጡ ከቦሌ በሚመለሱበት ሀገር፣ ኡርጂና ሰይፌ ነበልባል እንዳቀረቡት እነሻለቃ ጃተኔ ዓሊ ኬንያ በስደት በሚኖሩበት በመንግሥት ፀጥታ ኃይሎች ተገደሉ በተባለበት አገር ጦርነት አውጆ፣ አንድ መቶ አንድ ጊዜ የጦርነት መግለጫዎችን የሚሰጥ ድርጅት መሪዎች የሆኑት እነሌንጮ ለታ የቦሌ መንገድ እንዴት የጨርቅ መንገድ ሆነላቸው?

አቶ ሌንጮ ሒልተንና ጉለሌን ለቀው የሄዱት አብዛኛው የኦነግ ሠራዊት ከተመታና፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ኦሮሞዎች ከታሰሩ በኋላ መሆኑ ጥርጣሬአችንን ያጎላዋል። ተራ ተዋጊ ሲታሰርና ሲገደል መሪዎች ወደ ፈረንጅ ሀገሮች የመሄድ የሽርሽር ፈቃድ እንዴት ሊሰጥ እንደሚችል አይገባንም። ከጉለሌው ቢሮዋቸውና መዝናኛቸው ከሆነው ሒልተን 4 ኪሎ በሚገኘው መንግሥት ላይ የጦርነት ከበሮ ሲደልቁ ሰንብተው በመንግሥት አይሮፕላን ወደ ፈረንጅ አገር ምሽጋቸው እንዴት ሊጓዙ ቻሉ? እውን ኢህአዴግ እነ አቶ ዮሐንስ (ሌንጮ) ለታ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኦሮሞዎችን መርተው በባሌ ይመጡብኛል ብሎ ሲገምት በቦሌ ይሸኛቸው ነበር? ምንም ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ አለመሆናቸውን ተገንዝቧል ማለት ነው። እነዚህ ምናልባትም በዘመናችን ያልታዩ፣ በተለይ በኢትዮጵያችን እጅግ በጣም እንግዳ የሆኑ ነገሮችን ምንነትና ምክንያት ለመመለስ የፖለቲካ ሳይንስ ችሎታ የሚያስፈልግ አይመስለኝም።እስካሁን ካቀረብኩት ሀሳብ በመነሳት አንባቢ ዛሬ የኦሮሞ ሕዝብ ውስጥ ያሉ ችግሮችን የሚረዳ ይመስለኛል።

አንዳንዶችን ይበልጥ ግልፅ ላድርግ፣

1. ለብዙ ዓመታት ከሚሲዮናውያን ጋር ተለጥፈው በኖሩበት ዘመን የነሌንጮ ጭንቅላትና ልብ በ"መጽሐፈ ቁልቁሉ" በሥነሥርዓት መታጠቡንና የትም መድረስ እንደማይችል ሻዕቢያ ያውቃል።

2. የእስራኤል ደህንነት ያሲር አራፋትን ከፍልስጤም ታጋዮች ተደጋጋሚ የጥቃት ሙከራ አድኖ የተሽመደመደ የፍልስጥኤም ነፃ አወጭ ድርጅት (P.L.O) እንዲኖር ለማድረግ መቻሉ ይታወቃል። ኢህአዴግም የተሽመደመደ ኦነግ እንዲኖርና ጠንካራ የኦሮሞ ልጆች ወደ ትግሉ መድረክ እንዳይወጡ ይሠራል።

3. ሌሎች የኦሮሞ ድርጅቶች ማለትም የነጃራ አባገዳ፣ የጄኔራል ዋቆ ጉቱ፣ የእብስኦ ልጆችና በየቦታው ተበታትነው ያሉት ቡድኖች ልዩነቶቻቸውን አቻችለው ጠንካራ ኦሮሞ አቀፍ ግንባር እንዳይፈጥሩ እነሌንጮ የበታችነት ስሜት ይጫወታሉ።

4. የኦሮሞ ሕዝብ ሰፊ ድጋፍ ያለው ኦነግ ከሌሎች የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመስረትና መገንባት እንዳይሰለፍ፣ የኃይል ሚዛንም የወቅቱን ገዥዎች በሚጎዳ መልክ እንዳይለወጥ ኢህአዴግ የነዮሐንስ (ሌንጮ) ለታ ቡድን በኦነግ አመራር ላይ እንዲቆይ ይፈልጋል።

እንግዲህ ለችሎታቸው የኦሮሞ ሕዝብ መሪዎች ለመሆን ሲሉ እኛን በወንዝና በሃይማኖት በአደገኛ ሁኔታ ራሳቸው እየከፋፈሉን ባለ (ኀበናዎች ከፋፈሉን) ብለው የሚጮሁ፣ ከኢትዮጵያ ምድር እስከአውሮፓና አሜሪካ ድረስ የደራ የንግድ መሥመር ዘርግተው በሕዝባችን ደምና እንባ እየነገዱ ድርጊታቸውን ለመሸፋፈን ሐቀኛ የኦሮሞ ልጆችን "በጥቅም ተገዙ እያሉ" ስም የማጥፋት ዘመቻውን ተያይዘውታል።

በእርግጥ "የሕዝባችን ትግል ስለሚጎዳ መልስ አትጻፍ" ብለው የለመኑኝ የኦሮሞ ልጆች ብዙ ናቸው። ምናልባት መልሴን እንብበው ቅር የሚሰኙም ሊኖሩ ይችላሉ። ይሁንና ሀቀኛ የኦሮሞ ልጆች ከሩብ ምዕተ ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትዕግሥት በኋላ ለመፃፍ መገደዴን ሊያቁልኝ የሚችሉ ይመስለኛል። "የኦሮሞን ገመና አወጣህ፣ የኦሮሞን ዕድፍ በአደባባይ አጠብክ" የሚሉኝም አልታጡም። በእኔ እምነት ታላቁ የኦሮሞ ሕዝብ የሚሸሽግ ገመናም፣ እድፍም የለውም። እድፍ ካለው ይህ የምንነጋገርበት ጉዳይ ነው። ለሁሉም ስለነዚሁ የኦሮሞ ሕዝብ እድፎች የሚከተለውን ለማስቀመጥ እፈልጋለሁ።

1. በመጀመሪያ ደረጃ ድንጋይ መወርወር የጀመሩ እነሱ ናቸው። ስሞችንና ድርጊቶችን በግልጽ ማስቀመጥ የፈለግኩትም የምለውም ሁሉ በተራ ሐሜት እንዳይተረጎምና እድፉም ማን እንደሆነ ለማሳየት ፈልጌ ነው። በጥቂት ሰዎች ድብቅ ዓላማ ሕዝብ አስፈላጊ ያልሆነ መስዋዕትነት እንዳይከፍልም ነው።

2. የፃፍኩዋቸው ነገሮች ሁሉ ምስጢርነታቸው ለአብዛኛው ኦሮሞ ሕዝብና ሐቀኛ

ልጆቹ ምስጢር ሊሆኑ ይችላሉ። ከእኔ የተሻለ ስለእነሱ የሚያውቁ የራሳቸው ሰዎች አሉና ከመንግሥት ግን የተደበቁ አይደሉም።

3. የዛሬ 23 ዓመት አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ከገባንበት ጊዜ ጀምሮ ከእነዚህ ሰዎች ጋር በተለያየ ደረጃ፣ በፖለቲካ ዓለም ጭምር ቆይቻለሁ። ከዚሁ የረጅም ዘመናት ትውውቅ የሚመነጩ ምሬቶችም አሉኝ። ዋናው ችግሬም እነዚህ ሰዎች ግልጽ አቋም የሌላቸውና ዓላማችን ነው የሚሉትም እንደየጊዜው ሁኔታ የሚለዋወጥ መሆኑ ነው። እስኪ ጥቂቶቹን እንመልከት፣

ሀ. በተማሪው እንቅስቃሴ ወቅት ከነፍጠኛ ልጆች ጋር በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ አንሳተፍም ሲሉ ይቆዩና የተማሪ መሪዎች ምርጫ ሲመጣ ተሽቀዳድመው ይገቡ ነበር።

ለ. "መሬት ለተወላጁ (Land to the indegeneous እንጂ መሬት ለአራሹ (Land to the tiller) ትክክለኛ መፈክር አይደለም። ምኒልክ የኦሮሞን መሬት ለነፍጠኞች አከፋፍለዋል። እንዴት የምኒልክ ልጆች ዳግመኛ በኦሮሞ ሕዝብ መሬት ላይ ቆመው ያከፋፍላሉ" ሲሉ ቆይተው ትርፍ እንደሚያገኙ ሲያስሉት ለእድገት በኅብረት ዘመቻ መዝመት ብቻ ሳይሆን የመሬት ይዞታ ባለሥልጣናት ሆነው አዋጁን ለማስፈጸም ሲሽቀዳደሙ ነበር።

ሐ. ለምን ወደ ቤተክርስቲያን አትሄድም እያሉ ሰውን ሲጨቀጭቁ የኖሩ ሰዎች ዘለው የሶሻሊስት ካድሬዎች ሆነው ሲያገለግሉ ነበር።

መ. ከነፍጠኞች ልጆች ጋር እንደራጅም ሲሉ ከርመው ትርፍ እናገኝበታለን ብለው ሲገምቱ ብዙ የአማራ ምሁራን የነበሩበት የመኢሶን ካድሬ ሆነው ሊያስተምሩኝ እምቦ ድረስ መጥተዋል። እነሱ የደርግ ከፍተኛ ባለሥልጣንና ካድሬ ሆነው እየተሾሙና እየተሸለሙ አንድ ወር እንኳ ደመወዝ አግኝቼ የማላውቀውን መረራን "ቀይ ኅበና" ብለውኛል።

ሠ. መረራ ለኦሮሞ ባሕል መከበር አይታገልም እያሉ ይከሱኛል። እነሱ ግን ወቅቱ የማይደግፈው በመሰላቸው ጊዜ የኦሮሞ ባህላዊ እምነት መግለጫዎችን "የጣኦት አምልኮ ዕቃዎች ናቸው" እያሉ ወንዝ ሲጨምሩ ነበር። ዛሬ ደግሞ ራሳቸው ጨሌ ሰብሳቢዎች ሆነዋል።

ረ. በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት በነበርኩበት ጊዜ እነሱ ሐቀኛ መኢሶኖች ሆነው "መረራ ኦነግ ሆነ" ብለው ሲወሽክቱ የነበሩ አሁን ደግሞ የኦነግ አባል ሆነው እኔን በኅበናነት ይከሱኛል። እኔን "ከነፍጠኛ ልጆች ጋር ለምን ትገጥማለህ?" ይሉኛል። እነሱ ከመንዝና ከቡልጋ ያገባሉ። ለነገሩ የእነሱን አቋም የለሽነትና መሰሪነት ለማሳየት እንጂ ይህ ለምን ሆነ ማለቴ አይደለም።

በአጠቃላይ እነሱ እንደየጊዜው ትርፍና ሁኔታ ወደሚነጉዱባቸው ድርጅቶች አብሬ እስካልተጓዝኩና ወጥመዳቸው ውስጥ ገብቼ እስካልዋኘሁ ድረስ ክሳቸው ሊቀጥል ይችላል። ራሳቸው በሚሰሩዋቸው ወንጀሎች እኔንም ሆነ ሌሎችን የኦሮሞ ልጆች መክሰስ ቢያቆሙ ለእነሱም፣ ለመላው ኦሮሞ ሕዝብም ይጠቅማል እላለሁ። ቀደም ብዬ እንዳነሳኋት ዝንጀሮ በጣም አስቀያሚ ጠባይና አቋም እንዳላቸው እያውቁም ወይም ማወቅ አይፈልጉም። እንዲያው ቁንጅናቸውን እያደነቁ፣ ራሳቸውንም ሆነ መላውን የኦሮሞ ሕዝብን አጥፍተው እንዳይጠፉ ባለኝ ጭንቀት ጭምር የችግራችንን መንስዔና ምክንያት ይፋ መውጣቱን መርጫለሁ።

አንድ ተጨማሪ ነጥብ ልጨምር። የሐሰት ዝባዝንኬ የሚጽፉ ሰዎች ጭምር በደንብ የሚያውቁት አብዲ አህመድ የሚባል የሐረር ልጅ ነበር። ከሚከሱኝ ሰዎች ጋር የሠራና በጣም የማከብረው ሰው ነው። ከ13 ዓመታት በፊት ከእሥር ቤት ሊጠፋ ሲዘጋጅ የስንብት ሻይ ጋብዞኝ "አንተም በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ መኖር ይቻላል ብለህ፣ እኔም ይህ ሀገር ካልፈረሰ የኦሮሞ ሕዝብ ነፃ አይወጣም ብዬ በተለያየ የጦር ሜዳ ተሰልፈን እንገናኝ ይሆናል። ሁለታችንም ግልጽ አቋም ያለን ጠላቶች ስለሆን ችግር ያለብን አይመስለኝም። አንድ ቀን ወይ እኔ የአንተን መንገድ፣ ወይ አንተ የእኔን መንገድ እንመርጥ ይሆናል። ነገር ግን አንድ ነገር እንዳትረሳ! በየትኛውም መንገድ ከሚሲዮን ፀሎት ቤቶች የተፈለፈሉ ቅጥረኞች (Merceneries) እኛ ጋር እስካሉ ድረስ ሕዝባችን በምንም መንገድ ነፃ ይወጣል ማለት ሕልም ነው" አለኝ።

እኔንና አብዲ አህመድን ጨምሮ ብዙ የኦሮሞ ልጆች በሽታችንን ከአወቅን ቆይተናል። እኔም ለአብዲ በጊዜው የመለስኩለት "ሰው ጣቱን ገማኝ ብሎ አይቆርጥም" በማለት ነበር። ዛሬ ከ13 ዓመታት በኋላ ግን ሁሉንም ሰውነት የሚመርዝ ከሆነ መቁረጡ አስፈላጊ መሆኑን አምኜበታለሁ። እነሱ በሕዝባችን ደምና እንባ መነገዱን ምንጊዜም ስለማይተዉ የግድ እኛም ሆዳችን የሚቆርጥበት ጊዜ መድረስ አለበት ከሚል አቋም ላይ ደርሻለሁ።

ከዚህም በላይ ዛሬ "ለኢትዮጵያ አንድነት ቆምክ" ብለው የሚከሱኝ ሰዎች አንድነቱ አሁን ከሚያገኙት በላይ ትርፍ የሚያመጣ ከሆነ ወይም ኢህአዴግም ጨክኖ ለብሔራዊ እርቅ እነመኢሶንን፣ ኢህአፓን ኢዲሃቅን፣ ወዘተ፣ ቢጠራ በዛሬው ክሳቸው ምንም ሳያፍሩበት በቀድሞ ደራሽነት ጠባያቸው "ሰላም ፈላጊ ኦነግን" ፈጥረው ወደ አዲስ አበባ እንደሚበሩ፣ ኢህአዴግ እንኳ እምቢ ቢል ዛሬ የከዱትን መኢሶንን የኛው ነበር ብለው በአደራጅነት እንደሚሰለፉ በእርግጠኝነት ለመናገር እችላለሁ።

ጽሑፌን ከማጠቃለሌ በፊት በታሪክና በኦሮሞ ሕዝብ ፊት ተወቃሽ ላለመሆን፣ የሕዝባችን ትግልም ወደፊት እንዲገፋ፣ ዴሞክራሲያዊት የጋራ አገር በጋራ እንድንገነባ፣ ለሕዝባችን ብሔራዊ ክብርና መብት በሐቅ ለቆሙ የኦሮሞ ልጆች የሚከተለውን ጥሪ ለማስተላለፍ እወዳለሁ። ፖለቲካ ሂሳብ ብቻ አይደለም። አንድ ሕዝብ ለድል የሚበቃው በቅጡ ሲደራጅና ብቃት፣ ችሎታና ቆራጥ አቋም ባላቸው

የፖለቲካ መሪዎች ሲመራ ነው። ዛሬ ኦነግን አፍነው የያዙት፣ ከአንድ ፀሎት ቤት የተመረቁ የአንድ አካባቢ ልጆች መሆናቸውንና ከተራ የፖለቲካ ንግድ ባሻገር የፖለቲካም ሆነ ወታደራዊ ዕውቀት የሌላቸው መሆኑን ላለፉት 20 ዓመታት የምናውቃቸው የኦሮሞ ልጆች በእርግጠኝነት ለመናገር እንችላለን። የኦሮሞ ሕዝብ ትግል በየትኛውም መንገድ ቢሆን ወደፊት የሚገፋው ዛሬ በየፈረንጁ ፀሎት ቤቶች ሆነው የጦር ስልትና ትዕዛዝ የሚሰጡት ወደ ተገቢው ቦታቸው ወርደው ትግሉ ብቃትም ቆራጥነትም ባላቸው የኦሮሞ ልጆች ሲመራ ብቻ ነው። ይህም ይላካ ዘንድ በ"ሜጫና ቱለማ" እንዲሁም ከዚህ ድርጅት ውጭ ያሉ የኦሮሞ ሽማግሌዎች የሚጫወቱት ሚና አለ።

ትናንት የአንድ ወጣት ትውልድ ብርቅ ልጆችን ጨርሶ ላለፈው ቀይ ሽብር ኃላፊነቱ የማን ነበር ብለን የምንጠያየቀው ጥፋቱ ከተሠራ በኋላ ዛሬ ነው። ዛሬ ከሁሉም አካባቢዎች የበለጠ ተመሳሳይ አደጋ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ እያንዣበበ ይመስለኛል። ይህንኑ ተረድተን የኦሮሞ ሕዝብና በተለይ የዕድሜና የእውቀት በሳሎች ቢያንስ በራሳችን ልጆች ጥፋት የሚመጣውን አደጋ ለመቆጣጠር የምንችልና የሚገባንም ይመስለኛል። ይህን ለማድረግ ግን አንድ መገንዘብ ያለብን መሠረታዊ ቁም ነገር አለ። ይኸውም በአንድ በኩል ደግሞ የሚከፈለው መስዋእትነት ተገቢ መስዋዕትነት መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ነው።

ለትርፍም ሆነ ችሎታ ከማጣት ውዥንብር መፍጠርና መንዛት፣ በሕዝብ ደም የፖለቲካ ቁማር መጫወት ለነፃነት የሚከፈል ሕዝባዊ መስዋእትነት እንዳልሆነ በውል መገንዘብ አለብን።

ዛሬ የሕዝብ ሰፊ ድጋፍ ያለውን ኦነግን አፍኖ ከላይ የያዘው ቡድን በቤተሰብ፣ በሃይማኖትና በወንዝ ልጅነት የተሳሰረ ከመሆኑም በላይ ለአንድ ሕዝብ ትግል ግብ መምታት እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑ፣ ችሎታና ቆራጥነት የሌለው ነው። ከዚህም በላይ የዘረጋው የጥቅም ሰንሰለት የሚበጣጠስ መስሎ ከታየው ደርግ እንዳደረገው ሁሉ፣ የኦሮሞ ልጆችን በአጠቃላይም አገርና ሕዝብን አጥፍቶ ከመጥፋት የማይመለስ ቡድን ነው። ከምሁራኖቻችን እንኳ እንዳይማር በቁንጮው ላይ የተቀመጡት በሚሲዮን የተጣመመ አመለካከት (Missionary miseducation) የማሰብ ችሎታቸው የተኮላሸ ግለሰቦች ብቻ ናቸው። የአንድ ፀሎት ቤት ልጆች ቡድን አንድ ቀን ተዓምር ይሰራ ይሆናል ብሎ መጠበቁ የፖለቲካ የዋህነት ይመስለኛል።

በእኔ እምነት ሰፊ መሰረት ያለው የኦሮሞ ልጆች ኅብረት መፍጠሪያው ጊዜ አሁን ነው። በመሆኑም እስካሁን የደረሰው ጥፋት ቀላል ባይሆንም ሕዝባችንን ከተጨማሪ አደጋ ለማዳን፣ ለነጃራ፣ ለጀኔራል ዋቆ ቱሉ፣ ለእብስአና ሌሎችም የኦሮሞ ቡድኖች ተቀባይነት ያላቸውና ገለልተኛ ሆነው፣ የፖለቲካ ዕውቀትም ብስለትም ባላቸው የኦሮሞ ምሁራን የሚታገዙ የኦሮሞ የሀገር ሽማግሌዎች ቡድን በማቋቋም እስካሁን የተሰሩት ስህተቶች፣ ጥፋቶችና ወንጀሎችም ጭምር ተለይተው እንዲታወቁና ወደፊትም እንዳይደገሙ፣ ለሕዝባችን ትግል ወደፊት መግፋት የሚያግዝ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለማፍለቅ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በየትኛውም መንገድ የተደራጁም ሆነ ያልተደራጁ የኦሮሞ ልጆችም ቢሆኑ ሊጫወቱት የሚገባ ሚና አለ።

በእስካሁኑ ተሞክሮአችን ኦነግን ጨምድዶ የያዘው የአንድ አካባቢ ቡድን በታኝና ከፋፋይ ብቻም ሳይሆን ችሎታም እንደሌለውና ሊኖረውም እንደማይችል በእርግጠኛነት ለመናገር ይቻላል። ይህ ቡድን በፍጥነት ተወግዶ የኦነግ አመራር ከሁለም የኦሮሞ አካባቢዎች በተውጣጣና ሰፊ መሠረት ያለው አመራር እንዲፈጠር መታገል ያስፈልጋል። ይህም ሲደረግ በምንም መንገድ መረሳት የሌለባቸው ቁም ነገሮች አሉ።

አንደኛ፣ እስካሁን የኦነግን አመራር ለማሻሻል ሐሳቦች በቀረቡ ቁጥር ዋና መከላከያቸው ኦነግ የተመሠረተው "በትግል ጓዶች" እንጅ በፓርላማዊ የአሠራር ሥርዓት ስላልሆነ እንዲህ ዓይነቱን ሐሳብ ማንሳት ይከፋፍለናል፣ ወዘተ የሚሉዋትን የማስፈራሪያ ተረት አለመቀበል፣

ሁለተኛ፣ እንደገና በማዋቀሩ ላይ ስለሥራ ክፍፍል (Division of labour) ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። የውጊያ ችሎታውም ቆራጥነቱም ያላቸውን የኦሮሞ ልጆች ወታደራዊ አመራር እንዲሰጡ፣ የፖለቲካ ዕውቀቱም ብስለቱንም ያላቸው የፖለቲካ ሥራውን እንዲመሩና እግዚአብሔርንም ሰውንም ለምነው ትርፍ ማምጣት የሚችሉ እርዳታ በመሰብሰቡ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ የግድ ነው።

አዲስ የሚዋቀረውን ኦነግን ጨምሮ ሁሉንም የኦሮሞ ቡድኖች የሚያጠቃልል ግንባር መፍጠርና ልዩነትን አቻችሎ አብሮ መሥራት ወቅቱ የሚጠይቀው ነው።

የሁሉም ሕዝቦችዋ እኩልነት በተከበረባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ የኦሮሞ ሕዝብ ጥቅም የሚጎዳበት አንድም ምክንያት ስለሌለ፣ ዴሞክራያዊ ሥርዓት በሀገራችን እንዲሰፍን በሐቅ ከሚታገሉ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋርም ልዩነትን አቻችሎ ሰፊ መሠረት ያለው ዴሞክራሲያዊ ኅብረት መፍጠር ቁልፍ ጉዳይ ነው።

እነዚህ ከተሳኩ፣ በእኔ እምነት የኦሮሞ ሕዝብም ሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሰላም፣ ለብልፅግና ለዴሞክራሲያዊ መንግሥት መፈጠር ያለው ሕልም ዕውን የሚሆንበት ሩቅ አይሆንም።

## በእንግዳ አክባሪነት ስም የራስን ህልውና ማጣት

ኃከሮ -አትላንታ ጆርጂያ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ርህሩህ ጨዋና እንግዳ አክባሪ መሆኑ ከጥንት ጀምሮ የሚመሰክርለት ሕዝብ ነው። ከሀገሩ ውጭም ቢሆን በሄደበት ዓለም ሁሉ የማንኛውንም ሀገር ሕዝብና መንግሥት ህግ አክብሮ ለማንም መንግሥትና ሀገር ሸክም ሳይሆን ጥሮ ግሮ የሚኖር ሕዝብ ነው። በማስረጃ የተደገፈ (Statistics) ባይኖረኝም በተለይ በአሜሪካን አገር የሚኖሩት ኢትዮጵያውያኖች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሁለት ሥራ ይሰራሉ የሚል እምነት ይኖረኛል። ችግራችን ህብረት እንጂ በግልስ ብዙ ተራምደናል ግድየለም እሺ በሉኝ። በሥራዬ አጋጣሚ የማውቃት አንዲት አሜሪካዊት ያለችኝ ትዝ አለኝ። ይህች ሴትዮ ሦስት ስራ ትሰራለችና ሁልጊዜ ስትወጣ አሁን ወደ ሦስተኛ ሥራዬ እየሄድኩ ነው ትለኛለች። አንድ ቀን ስትወጣ ቆም አለችና "You know what?" አለችኝ። እኔም What? ስላት "My friends were asking me that why do you work like Ethiopians?" ጓደኞችዋ ለመጠየቅ የፈለጉት ለምን እንደ ኢትዮጵያውያኖች ብዙ ትሠሪያለሽ ለማለት ነበር። እኔም ውስጥ ውስጤን በጣም ደስ እያለኝ በዚያ በመጥረቢያ አክሰንቴ "I am doing two jobs too!" አልኳት።

ይህንን ፅሁፍ ለመፃፍ ስነሳ እንኳን በውጭ ዓለም ስላሉት ኢትዮጵያውያኖች ሳይሆን በሀገር ቤት ስላለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። በአርእስቱ እንደጀመርኩት በእንግዳ አክባሪነት ሥም የራስን ህልውና ማጣት ወደሚለው ፍሬሃሳብ ልመለስና የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የውጭ ዜጎችንና እንግዶችን አክብሮ የሚኖር ሕዝብ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ግን እንግዳ አክባሪነት ሳይሆን ህልውና ማጣት ነው ብዬ እከራከራለሁ። ለዚህም በቅርቡ አዲስ አበባ ውስጥ ስላሉት የሱማሌ ስደተኞች ሁኔታ ብዙ መረጃ ከሰበሰብኩና በቦታውም ተገኝተው ከሚመሰክሩት የዓይን ምስክሮች በመነሳት ነው። ይህንንም ስል ሕዝቡ በሱማሌ ዜጎች ወይም ስደተኞች ላይ ይነሳ ማለቴ ሳይሆን እንግዳ ማክበርና ህልውናን አሳልፎ መስጠት ፍፁም የተለያዩ መሆናቸውን ለማሳመን ወይንም ለማስገንዘብ ነው። እነዚህ ስደተኞች የተከራዩዋቸውን የኢትዮጵያውያኖች ቤት ስልኩን በህገ ወጥ መንገድ በመጠቀም ኢትዮጵያውያኖችን ከማሳሰር አልፎ በሕዝብ ሆቴሎችና በሕዝብ ስልኮች እጅግ ችግር የፈጠሩና ሴቶቻችንን እስከመድፈር፣ በኢትዮጵያ ያልተለመደውን አደንዛዥ ዕፅ መጠቀም፣ ስርቆትና የፎርጅድ ሥራ በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ። ይህ ሁሉ እንግዳ አክባሪነት ሳይሆን የራስን ህልውና መሸጥ ነው። ኢትዮጵያውያኖች ግን ሱማሌ ውስጥ እንዴት ይኖሩ እንደነበርና ስንት ኢትዮጵያውያኖችም በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሞቱ ማንም ኢትዮጵያዊ እኔ ከማውቀው በላይ ያውቃል። እንደገና አሁንም እዚህ ጋ እንድታስተውሉልኝ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም እኔ የማወራው ስለህልውና ነውና ለብቀላ እንነሳ ማለቴም አይደለም። ግን በኢትዮጵያዊነቴ ቁስሌን አንባቢዎች እንዲረዱልኝና አንዳንዴም ፊት ለፊት ተጋፍጦ ለመብትና ህልውና መከራከር ወይንም መፋለም የአንድ ሀገርና በግልም ቢሆን የአንድ ግለሰብ ግዴታው ነው። ሀገር ማለት ደግሞ ቤተመንግሥቱ ብቻ ሳይሆን ዜጎችም ጭምር ናቸው የኢትዮጵያ መንግሥት አባሎችም ጊዜ ቢኖራቸውና ይህችን ጽሑፌን ቢያነቡልኝ በጣም ደስ ይለኛል። የኢትዮጵያ ሕዝብና የሱማሌ ሕዝብ በመልክና በታሪካዊ አመጣጡ የሚመሳሰልና የአንድ ግንድ ዝርያ መሆናቸውን ታሪክ ቢመሰክርም በየዘመናቱ በሚነሱት ጦርነቶች የተጠባበሰ ሕዝብ ለመሆኑ የጥንቱን የሱማሌ የባንቱ ብሔረሰብና የኢትዮጵያ ኦሮሞዎች ያደረጉት ጦርነት ዋና ማስረጃዎች ናቸው።

ልጅ ሆኜ ከማስታውሳቸው (የቾምቤ) ንግግሮች አንዱ "ግራር የበቀለበት ሥፍራ ሁሉ የራሷ መሬት የሚመስላት ሽርጣም ሱማሌ እስቲ ግራር ሂሊኮፕተሯ ሆኖ ሲዋጋላት እናያለን፤" ይሉ ነበር።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያኖች ከ1960ዎቹ ዓመታቶች ወዲህ መብታቸውን ተገፈው የተሰቃዩበት ሀገር አንድ በራሳቸው ሀገር በኢትዮጵያ ሲሆን በስደት ሀገር ደግሞ ሱዳን፣ ሱማሌና ኬንያ ናቸው። ሱዳና ውስጥም ትልቅ ችግር እንደነበረ የሚታወቅ ነው። እልፍ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያኖች በሱዳን ፖሊሶች መሰቃየታቸውንና አሁንም በመሰቃየት ላይ መሆናቸውን የዓይን ምስክር ነው። ኬንያ ትንሽ ቢሻልም እዚያም ቢሆን ትንሽ አፀያፊ ሁኔታዎች መፈፀማቸው የቅርብ ትዝታችን ነው። እጅግ የሚገርመውና በህይወቴ የማልረሳው ነገር ቢኖር ምንም የህክምና ሙያ የሌለው ግለሰብ ለኢትዮጵያ ስደተኞች ተመድቦ ስደተኞች የእንቅልፍ ታብሌት ሲጠይቁት የሚያነቃ (የማያስተኛ) መድኃኒት እየሰጣቸው ይሰቃዩ እንደነበረ በኬንያ የነበሩ በተለይ ደግሞ (በቲካ) ካምፕ የነበሩት የሚያስታውሱት የሰቆቃና ትልቅ የመብት ረገጣ ጊዜ ነበር።

የኬንያ መርፌ ደግሞ ዝሆን እንኳን ቢወጋ የሚያመው ይመስለኛል። በዚህ የተነሳ ብዙ ኢትዮጵያውያኖች ከመርፌው ቢሸሹም የሆድ ነገር ሆኖ (የህይወት ጉዳይም ሆኖ) ለምሳና ራት በሚሰለፉበት ጊዜ በፖሊስ ጋማ እየተባሉ ያንን (የሻለሙ) ዘጠኝ ቁጥር ሚስማር ምሥጋና ይጣ የሚያሰኝ መርፌ ይቀረቀርባቸው ነበር። ምን እሱ ብቻ ለማስተርጎም ሄዶ የታመመውን ልጅ ሳይሆን ለማስተርጎም የሄደውን ልጅ ሐኪሙ ብዙ ትለፈልፋለህና የታመምከው አንተ ነህ ተብሎ መርፌ የተወጋውስ ያስቃችኋል ወይስ ያሳዝናችኋል? ምን ይደረግ የራሱ መንግሥት ያልወደደውን ህብረተሰብ የሌለው ሕዝብ ሌላው መንግሥት ይወደዋል ብዬ ግምት አይኖረኝም። ግን እኛስ በሀገራችን እንዴት ነን? እዚህ ላይ እንደገና ልብ ማለት ያስፈልጋል። አሁንም የማወራው ስለህልውና እንጂ የእኛ ዶክተሮች ደግሞ የእኛ ዜጋ ተሰቃይቷል ብለው የሌሎች ሀገሮች ስደተኞችን በካቻቢቴ እንዲቦረቡሯቸው አይደለም። ይህ ሁሉ ከላይ በጠቀስኳቸው ሀገሮች ዜጎቻችን ምን ያህል እንደተሰቃዩ ለማሳየት ነው።

ምንም እንኳን የአንድ ሀገር ሕዝብ በፖለቲካና በሌሎች ችግሮች ቢሰደድም መንግሥታቸው በብሔራዊና በዓለም አቀፋዊ ሁኔታ የህሊና ግዴታ ያለበት ይመስለኛል። አንዳንዴ (ቾምቤ) እንጀቴን ያርሰኛል።

ወደ ገጽ 42 ይዞራል

# አዳም ና ሔዋን

አዳምና ሄዋን የተሰኘው አምዳችን የሚያተኩረው በተቃራኒ ጾታዎች መካል በሚኖረው ግንኙነት ላይ ነው። የገጠሙኝ ታሪኮችና አስተያየቶች የመላክለት ይቀርባሉ— በእውነተኛ ገጠመኝ ላይ የተመሠረቱ የፍቅር ታሪኮችንም እናቀርባለን። አምዱን የመወያያና የመማሪያ አምድ ለማድረግ እንዲቻል አንባብያን አስተያየታችሁን እንጠይቃለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡ አስተያየቶችም ሆነ የገጠሙኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩልን መሆኑ ይታወቅልን።

## ዕጣዬ

### ከአብርኸት

"ዕጣዬ" በተሰኘ ርዕስ አብርኸት (የብዕር ስሟ ነው) በስደት ኑሮዋ የገጠማትን በተከታታይ እያቀረበችልን ነው። ይህን እሳዛኝ የፍቅርና የስደት ታሪክ ለአንባብያን ስናቀርብ አቀራረቡን እንዲጥም ከማድረግ በቀር በታሪኳ ላይ የጨመርነው ሆነ የቀነስነው ነገር የለም። እሷ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ አገር በስደት ላይ ናት።

### ክፍል 13

ሰይፍዬ የፃፋቸውን ደብዳቤዎች በእንባ ጭጋግ ተሸፍኜ አነበብኳቸው። በመጣሁ በወሩ ጀምሮ ሳይቋረጥ፣ ተስፋ ሳይቆርጥ የላካቸው ደብዳቤዎች ብዛት ወደ ሃያ ይሆናሉ። ደብዳቤዎቹ ሳይደርሱ ቀርተው ተመላሽ ባለመሆናቸው ተስፋ ሳይቆርጥ ነበር አከታትሎ የላከው። እኔ የላኩዋቸው ደብዳቤዎች ብቻ እንደሚደርሱት ግን የእሱ ደብዳቤዎች እንደማይደርሱኝ የተገነዘበ ይመስላል። እሱ የፃፋቸው ደብዳቤዎች ለእኔ ለምን እንዳልደረሱም ሳይገርመው አልቀረም። አንብቤ እንደጨረስኩ መልሼ ካገኘሁበት ቦታ ላስቀምጠው ወይስ ልውሰደው? የማደርገው ጠፋኝ። ረዘም ላለ ጊዜ ስለማመጣት የነበረችው የእናቴ ልጅ እህቴ ከምወደው ፍቅረኛዬ የተፃፋልኝን ደብዳቤዎች ደብቃ እኔ እንዳላገኝ ማድረጓ በጣሙን አስከፋኝ። አሳዘነኝም። ከሞኝነት በመነጨ የግትርነት ባህርይ እኔን ከሰይፉ ለማለያየት ያደረገችው ነገር ስሜቴን ምን ያህል እንደሚጎዳው መረዳት አለመቻሏ ገረመኝ። የፍቅር ሁሉ ጌታ የሆነው አምላክ ባያጋልጣት ኖሮ እኔን የምወደውን ሰይፉን ለማስረሳት የወሰደችው እርምጃ ቀላል አልነበረም። ቅያሜዬ የከፋ እንደሚሆን ማንም የሚረዳው ነው። ለእኔ እዚህ መምጣት ትልቅ ሚና የተጫወተችውን የእናት አባቴን ልጅ ደግሞ በዚህ ጉዳይ እንዴት ልጣላት? ብጣላትስ ምን መሄጃ አለኝ? ያለሁት በሰው አገር። በዚህ ላይ አገሩንም ምኑንም ገና አልመድኩት። ለጥቂት ጊዜያት በእንባ ጭጋግ ተሸፍኜ የማደርገውን ሳወጣና ሳወርድ ሁሉ ነገር ጨለማ ሆኖ ታየኝ። ደብዳቤዎቹን መልሼ ማስቀመጡ አልታየኝም። ቢያንስ እኔ ማግኘቴን ትወቀው! አልኩና ይዤው መኝታ ቤት ሄድኩ። ድብዳቤዎቹን አንዳንዶቹን ከአልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ እንደገና አነበብኳቸው። ሰይፉ ለእኔ ያለው ፍቅርና ናፍቆት ምን ያህል እንደሆነ የሚያበስሩ ነበሩ። በስሜት ተገፋፍቼ ምንም እርምጃ መውሰድ እንደሌለብኝ ወሰንኩ። የማማክረውም ሰው በቅርቡ የለኝ። በሃሳብ ማዕበል ውስጥ ገብቼ ስባዝን ጥቂት ከቆየሁ በኋላ እንቅልፍ ይዞኝ ሄደ። እህቴ ማታ ስትገባ አልሰማሁዋትም። ጠዋት ግን የቀሰቀሰችኝ እሷው ነበረች። ከእንቅልፌ ስባንን ከራስጌዬ ቆማ አየሁዋት። በምወዳት እህቴ ገፅታ ባሻገር አዕሙ የሚታይ ሰይጣን ታየኝ። እንዳላያት መልሼ አይኔን ከደንኩ። ንዴቴን፣ ብስጭቴን ዋጥ ለማድረግ ከስሜቴ ጋር ግብግብ ገጠምኩ። ደጋግማ ስትጠራኝ ቀና አልኩና "ታዲያስ" አልኳት።

"የሥራ ሰዓት አልረፈደብሽም እንዴ?" አለችኝ። እሷን ማየት አልቻልኩም። ቀና ብዬ የጠረጴዛውን ሰዓት ሳየው ከጠዋቱ ለ9:00 ሩብ ጉዳይ ሆኗል። ሥራ መግባት ያለብኝ በ9:00 ነው። እንድምንም ከአልጋዬ ውስጥ ወጣሁና ወደ መታጠቢያ ክፍል ገባሁ። እሷ እዛው እንዳለች ትቼያት። ገላዬን እንደምንም ተጣጥቤ ስወጣ አልጋዬ ላይ ቁጭ ብላ አገኘሁዋት። ደብዳቤዎቹ ከኮሞዲናው ላይ እንደተውኳቸው ስለነበሩ እንዳየቻው ለማወቅ አላዳገተኝም። በመዳፏ አገጯን ተደግፋ ከርዷን ከጉልበቷ ላይ አሳርፋ ተከዛ መሬት መሬቱን ታይ ነበር። ምንም አላልኩም። ገላዬን አደራርቄ ልብሴን መለባበስ ጀመርኩ። ዞር ብዬ ላያትም አልፈለግሁ። ዝምታ ቤቱን ሞላው። ለባብሼ ጨረስኩና ቦርሣዬን አንስቼ ለመውጣት ወደ በሩ ስሄድ ከተቀመጠችበት ሆና "አብረኸት!" ብላ ስትጣራ ሰማሁዋት። መልስ አልሰጠሁዋትም ዝም ብዬ ወደ ሥራዬ ሄድኩ። እሷም አልተከተለችኝም። አስር ደቂቃ ዘግይቼ ስራ ገባሁ።

የዚያን ዕለት ሥራዬ ላይ ዝርክርክ ብዬ ነበር የዋልኩት። ብሽቀት፣ ዝን፣ ግራመጋባት፣ ወዘተ ... ተፈራርቀውብኝ ለሥራም ሆነ ለሌላ ጉዳይ ሁለቴ ወይም ሶስቴ ካልጠሩኝ አቤት አልልም ነበር። ረጋ ባለ መንፈስ ማድረግ የሚገባኝን ነገር አሰብኩ። በመጀመሪያ ከሰይፉ ለሚላኩልኝ ደብዳቤዎች የተለየ አድራሻ ለመጠቀም ወሰንኩ። ከምሠራበት ቦታ በመጀመሪያ የተዋወቅኳትን ልጅ አነጋገርኩዋት። እህቴ እንዲህ አድረገችኝ ብዬ ማውራቱንም አልፈለግሁም። በደፈናው ደብዳቤዎቼ በእሷ አድራሻ እንዲመጣልኝ አድራሻዋን እንድጠቀምበት ለመንኳት። ምንም ቅር አላላትም። ለምን እንደጠየቅሁዋትም ለማወቅ አልፈለገችም። "ምናለበት እሺ" አለችኝ። የዚያኑ ዕለት ለሰይፉ ደብዳቤ ፃፍኩለት። የነበርኩበትን ሁኔታ፣ ደብዳቤዎቹን መች እንዳገኘኋቸው በአጠቃላይ ችግሩን ሁሉ ዘርዝሬ ፃፍኩለት። የእሱም መምጣት ጉዳይ እንግዲህ እንደ አዲስ የሚጀምር መሆኑንና ጊዜም ሊገፅ እንደሚችል፤ በእህቴ በኩል ያለው ሁኔታ ተስፋ የሚያስቆርጥ ደረጃ ላይ እንዳለ ገለፅኩለት። ሲፅፍልኝም የተለየ አድራሻ እንዲጠቀም አዲሱን አድራሻ ዕፌ የዚያኑ ዕለት ላክሁለት።

የደብዳቤው ጉዳይ በዚህ ከተጠናቀቀልኝ ቀጥሎ ደግሞ ስለእኔ እናኗኗር ማሰብ ነበረብኝ። ከእህቴ ጋር በዚህ ሁኔታ ለረዥም ጊዜ ልኖር እንደማልችል ተረዳሁ። አሁን ባለሁበት ሁኔታ ግን ሌላ ቤት ተከራይቼ ለመውጣት አቅሙ አልነበረኝምና እዚያው መቆየት እንዳለብኝ ወሰንኩ። በስሜት ተገፋፍቶ የሚወሰን ውሳኔ አደጋ ላይ ሊጥል ስለሚችል ጥንቃቄ አደረግሁ። እንግዲህ ያለሁበት ሁኔታ ይታያችሁ— የዚያን ዕለት ቤት የገባሁት ከእኔ ቀድሜ ነበር። በቀጥታ መኝታ ቤት ሄድኩኝ። ደብዳቤዎቹ ከተውኳቸው ቦታ ነበሩ። አልተነኩም። ሰበሰብኳቸውና ሻንጣዬ ውስጥ ከተትኳቸው። ከእህቴ ጋር ሳንነጋገር ሶስት ቀን አለፈ። በሶስተኛው ቀን ቅዳሜ ዕለት ሁለታችንም ሥራ አንገባም ነበር። እኔ እንደልቤ ከተማ ውስጥ ለመዘዋወር መኪና ስለሌለኝና መንዳትም ስለማልችል የምውለው ቤት ነበርና ከመኝታ ቤቴ ሳልወጣ ጠዋት እስከ 10:00 a.m ቆየሁ። አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ የባጡን የቆጡን እሰብ ነበር። እህቴን ምን ብዬ እንደማናግራት ሁሉ ግራ ገብቶ ነበር ያለኝ። ወደ 10:30 አካባቢ የመኝታ ቤቴ በር ተንኳኳ። እሷው ነበረች።

"አልተነሳሽም እንዴ?" አለችና ወደ ውስጥ ገባች። ፊቴን አዞርኩባት።

"በጣም እንደተናደድሽብኝ አውቃለሁ፤ እስከመቼ ድረስ ተኮራርፈን ይሆናል" አለች።

መልስ አልሰጠኋትም። ድምጿን ስሰማ ውስጠመናዬ ሲግል ተሰማኝ። ፊቴን እንዳዞርኩ ዝም አልኩ።

"አንድ ነገር ብቻ እንድነግርሽ ፍቀጅልኝ" አለች። ከአልጋዬ ጫፍ ቁጭ ስትል ተሰማኝ

ዝም አልኳት።

"ለምን እንዲህ እንዳደረግሁ የተረዳሽልኝ አልመሰለኝም" አለች።

አሁንም ዝም አልኳት።

"እኔ ለአንቺ ጥሩ በማሰብ እንጂ ለሌላ አይደለም" አለች።

"ጥሩ ነገር?" አልኳት በጥያቄ መልክ። የመገረም ሳቅ ሳቅሁ።

"ታዲያ አንቺን እህቴን ለመጉዳት ነው?" አለች።

"ከዚህ በላይ ምን ልታደርጊ አሰብሽ?" አልኳት ንዴት በተናነቀው አንደበት

"ሊሆን በማይችል ነገር ጊዜሽን እንዳታጠፊ በማሰብ ነው"

"እሱን እኔ የማላውቅ ሕፃን እኮ አይደለሁም"

"ሕፃን ነሽ አላልኩም። አንቺን ለማስመጣት ስንት ችግር ውስጥ እንደገባሁ የማውቀው እኔ ነኝ። አሁን እሱን ለማምጣት በማይቻልበት ሁኔታ ስለእሱ በማሰብ ጊዜሽን እንዳታጠፊ አስቤ ነው።" አለች።

"እሱን ስለማምጣት ጉዳይ ከእንግዲህ የሚያገባሽ ነገር የለም። በዚያ በኩል ያለሽን አቋም በሚገባ ተረድቼዋለሁ፤ አሁን ምናለ ብትተይኝ?" አልኳት።

"አብረሽት! ለእኔ ከአንቺ ከእናቴ ልጅ የሚበልጥብኝ የለም። አንቺን ማስከፋት በፍፁም የማልፈልገውም ሆነ የማላልመው ነገር ነው። እንዲያም ሆኖ ታዲያ አንቺን የሚጎዳ ነገር፣ አንቺን ችግር ላይ የሚጥል ነገር ማየት አልፈልግም። አንቺ በፍቅር ታውረሽ የምትሠሪውን ነገር የምታውቂ ስላልመሰለኝ ነው ይህን ያደረግሁት። ደግሞ አውቃለሁ እሱን ወዲህ ለማስመጣት በፍፁም አይቻልም። ነገሩ ሁሉ ጠብቋል። አንቺ ብነግርሽም ይህን ልትረጂልኝ አልቻልሽም። ስለዚህ እሱን የምትረሺበትን መንገድ በመሻት ነው ደብዳቤውን እንዳታገኚ ያደረግሁት ለሌላ አይደለም።" አለች።

"ሰይፉን ምን ያህል እንደምወደው ደጋግሜ ነግሬሻለሁ። ፍቅር ደግሞ ኃያል ነው። አንቺስ ቢሆን ይህን መረዳት ያቅትሻል ወይ? ባትረጂሽ እኔን እህትሽን ይህን ያህል የምታስቢልኝ ከሆነ እኔን የሚያስደስት ነገር መፈፀም የለብሽም ወይ?' አልኳት።

"ነገርኩሽ እኮ አብረሽት፤ አንቺ ስለዚህ አገር ኑሮ ገና ብዙም አላወቅሽ። በዚህ ላይ አንቺ ገና አልተቋቋምሽ" አለችኝ።

"ይህ ሁሉ ምክንያት ሽፋን ነው። ቀደም ብለሽ ደጋግመሽ ያልሽኝን ነገር ለምን ትረሺያለሽ?"

"ምን አልኩሽ?"

"የእኔና የሰይፉ መገናኘት ሊሆን እንደማይችል፤ ምክንያቱም ሰይፉን አትውጂውም። ምነው ትርሺያለሽ እንዴ? እሱ አማራ ነው፣ የእኛ ደመኛ ነው ስትይ አልነበረ። አሁን ሌላ ምክንያት አታምጪ!" አልኳት።

"እሱንም ደጋግሜ ብነግርሽ ልትረጂ አልቻልሽም። በእኛና በእነሱ መ ልያለውን ችግር ታውቂያለሽ። ዘመዶቻችን ምን ያህል ጥላቻ እንዳላቸው ታውቂያለሽ። በዚህ ላይ እየተካሄደ ያለውን አለመግባባትና ጦርነት ታውቂያለሽ። የእሱም ሆኑ የእኛ ዘመዶች በማይቀበሉበት ሁኔታ በሁለታችሁ መ ከልየሚኖረው ግንኙነት ሊያመጣ የሚችለውን ችግር ማየት አልቻልሽም" አለችኝ።

"ለመጨረሻ ጊዜ ልለምንሽ። ይህን ነገር ሁለተኛ እኔና አንቺ አናውራው። በዚህ በኩል ፍፁም ልንግባባ አልቻልም። አንቺም ይህን አመለካከት ከየት እንዳመጣሽው በፍፁም ሊገባኝ አልቻለም። እዚህ ከመጣሽ ወዲህ የተጠናውተሽ በሽታ ነው። እኔ ደግሞ ከዚህ አመለካከት ውጪ ነኝ። ስለዚህ ጉዳይ እኔና አንቺ በፍፁም ባናወራ ደስ ይለኛል። ፍቅር ደግሞ ዘር፣ ጎሣ፣ የማይለይ መሆኑን እንኳን እኔ አንቺም ታውቂዋለሽ"

"ምኑን ነው የማውቀው?" አለችኝ።

እሷ የምታወጣውን አሜሪካዊ ጓደኛዋን እንዴት እንደረሳችው ገረመኝ።

"ምነው አንቺ የምትወጪው ከማን ጋር እንደሆነ አጣሽው? ከአሜሪካዊ ጋር። በዘር፣ በጎሣ ከማትገናኚው ጋር አይደለም? የአንቺ ሲሆን ልክ፤ የእኔ ሲሆን ስህተት፤ ምናለ እንደማይረዳ ሰው አድርገሽ ባትቆጥሪኝ።"

"እሱን እኮ ለጥቅም ነው እንጂ ላገባው አይደለም። ይህን ደግሞ ታውቂያለሽ"

"እኔ መቼ ተቃወምኩ። ፍቅር ዘር ጎሣ የማይለይ መሆኑን እረዳለሁ። ለጥቅም ብሎ ደግሞ ግንኙነት መፍጠር በተለይ ገላን ያህል መጠቀሚያ ማድረግ ትክክል አይደለም። ምናለ ስለዚህ ባናነሳ" አልኳት። የበለጠ በተከራከርንና በተጨቃጨቅን ቁጥር ጥላቻ ሊነግስ የሚችል መሆኑን ፍርሃቴን ልደብቃት አልፈለግሁም።

"እና አሁን ምን ልታደርጊ ነው?" አለችኝ።

"አልገባኝም" አልኳት።

"ማለቴ ስለ አንቺ ሁኔታ"

"እሱን ለእኔ ተይልኝ፤ ምንም እንኳ አሜሪካን አገር

ያንቺን ያህል ባልኖር ዕድሜና በተለይም ያለፍኩበት የስደት ኑሮ ብዙ ያስተማረኝ ስለሆነ ከእንግዲህ በእኔ በኩል የማደርገውን ነገር ለእኔ ተይልኝ ልለምንሽ። አንቺንም አላስቸግርሽም። ስለዚህም ጉዳይ አላነሳብሽም፤ አንቺም አታንሺብኝ። ቁርጥ ያለ ነገር ግን ልንገርሽ፣ እኔ ከእንግዲህ ሰይፉን ሊያስረሳኝ የሚችል ነገር ሊፈጠር አይችልምና ስለእሱ መጥፎ ነገር ባታነሺብኝ ደስ ይለኛል።" አልኳት።

"እና እሱን ለማስመጣት እንዴት ትችያለሽ፤ አንቺ ራስሽ ገና የመኖሪያ ፈቃድሽ ጉዳይ አልባት አላገኘም" አለችኝ።

"ስለ ሰይፉ አታንሺ አልኩሽ እኮ፤ ስለእኔ እንግዲህ አንቺ ረድተሽኛል። እግዜር ካለ ይፈቀድልኛል። ካላለም ምንም ማድረግ አልችልም። አሁን ግን ያው ባለኝ የሥራ ፈቃድ መሥራት ነው።" አልኳት። በዚሁ ተስፋ ቆርጣ ትታኝ ሄደች። ከዚያ በኋላ ስለዚህ ጉዳይ አላነሳንም። ግን በእኔና በእህቴ መ ል ትልቅመራራቅ እየተፈጠረ እንደሚመጣ እየተረዳሁ መጣሁ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከሰላምታና አልፎ አልፎ የቤተሰብ ወሬ ካልሆነ በስተቀር ብዙ አናወራም። የአሜሪካን ኑሮ፤ የሥራችንም ባህርይ ድሮውንም ብዙ የሚያገናኝ አልነበረም። በዚያቹ በምንገናኝበት ጥቂት ጊዜያት በውስጣችን መራራቅ እየተፈጠረ እንዳለ ከሁኔታችን ያስታውቅ ነበር። በወሩ ገደማ ከሰይፉ ደብዳቤ ደረሰኝ። የላኩለት ደብዳቤ እንደደረሰው ገለፀልኝ። ያለበትን ችግር፣ እሱም በበኩሉ ባሉት መንገዶች ወደዚህ ለመምጣት የሚያስችለውን ሁሉ እየሞከረ እንዳለ፡ በተለይም ሱዳን ውስጥ እየተፈጠረ የመጣውን መቃቃር ሁሉንም ሰፋ አድርጎ ፃፈልኝ። በቅርቡ የተነሳውን ፎቶም ላከልኝ። በጣም ከስቷል። የነበርኩበትን ሁኔታና በተለይም ከእህቴ ጋር በአመለካከት ልዩነት እየተፈጠረ ያለውን ችግር በመጠኑም ቢሆን በፃፍኩለት ደብዳቤ ገልጬለት ኖሮ በተቻለ መጠን ስሜታዊ የሆነ እርምጃ እንዳልወስድ፣ ነገሮችን ረጋ ብዬ እንድመለከታቸውና እንድፈጽም መልካም ምክሩን በፃ ፈው ደብዳቤ ላይ ለግሶኛል። እኔም ሳይውል ሳያድር ደብዳቤ ፃፍኩለት። ያቻ ለደብዳቤ አድራሻዋን እንድጠቀም የፈቀደችልኝን ልጅ አማክርኳትና ሠርቼ ካገኘሁዋት ጥቂት ገንዘብ በሰው በኩል እንዲደርሰው ላኩለት። በቅርቡም እግዜር ፀሎታችንን ሰምቶ የልባችንን አይቶ እንደሚያገናኘን እንዲያውቅና በእሱም ላይ ምን ጊዜም ቢሆን የማልለወጥበት መሆኑን እንዲረዳም ገለፅ ኩለት። እንግዲህ ኑሮዬ ከእንግዲህ ምን እንደሚመስል ሳትጠራጠሩ አትቀሩም። ከእህቴ ጋር አብሬ ለረዥም ጊዜ የመኖር ዕድሌ በጣም ትንሽ እንደሆነ አውቄዋለሁ። በተለይ ያሰብኩት ዓላማዬ ተሳክቶ፣ ፀሎቴ ሰምሮ ሰይፉ ከመጣ እሷ ቤት ለመኖር እንደማንችል ስለማውቅ ወጪዬን ሁሉ ቀንሼ ገንዘብ ማጠራቀም ጀመርኩ። በዚያች ጓደኛዬም እርዳታ ሌላ ሥራ አገኘሁና ሁለተኛ ሥራ ጀመርኩ። ሁለት ሥራ መሥራቴ ቤት ውስጥ የምውልበትን ጊዜ ሰለቀነሰ ከእህቴ ጋር የምንገናኝበት ጊዜም እየመነመነ ሄደ። አንዳንድ ጊዜ የምንገናኘው በሳምንት አንዴ ወይም ሁለቴ ሆነ። እሷ ስትገባ ወይ እኔ ተኝቻለሁ አለዚያም ሥራ ቦታ ነኝ። እና ይህም ለሌላ ጭቅጭቅና ንትርክ ጊዜ አልሰጠንም። (በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል) ●

## ሁሉን አቀፍ
## (የሲንግል ኑዛዜ)

<u>ከስፔራንቶ ዲያስፖራ (ሴንት ሉስ ሚዙሪ)</u>

ዘር የማይሰማኝ ሸበላ በወል ታሪኬ የምቀናጣ
ማንበቡንም ያደረግሁ በችግር የማልገረጣ
ጥቁርነቴ የሚማርከኝ ቢያነጡኝ የማልነጣ
ፈትገው ቢገሽልጡኝ ቆዳዬ የማይነጣ
ቢገርፉኝ ቢዘለዝሉኝ ሰምበር የማላወጣ
ደፋርና ጭስ ሆኜ መውጪያዬን የማላጣ
እኔ የብሉ ናይል የአባይነሽ ልጅ
እንዴት አርበኛው ሚስት ልጣ።

ትከሻዬን ቢከትቡት ቆዳዬ የማይበጣ
አፍንጫዬም እንደነገሩ ጠጉሬ እንክርድድ ቆንጣጣ
እንደፈኛ የተነፋ ዓይኖቼም ኮከ ፈጣጣ
የእነዚያ የጀግኖች ወገን ሰላይ የሚያየኝ በደፈጣ
እኔንም ይደንቀኛል – ሲንግል የደም ግባት ያለኝ
እኔ እንዴት ሚስት ልጣ።
ትምክህተኛ እንዳትለኝ "ብቻዬን ነው የማለቅሰው"
በሬን ዘግቼ በቀዳዳው ወጪ ገቢውን የምመዝነው
አለዚያም –
ሲክስ ፓክ ሚለር ገዝቼ ዓለም ዙሪያዋን የምቃኘው
በካርሲኖጂን ሲጋራ ጢስ ያለፈውን የምመኘው
በተስፋ የሃሳብ ደመና መጭውን ሁሉ የምቃኘው
ያችን ደሳሳ ቤቴን አፓርትሜንቴን የማውደው
ትጠራኝ ይሆን ብዬ የቴሌፎን እምርታ
በየሴኮንዱ የምቆጥረው።

የስድስት ኪሎው ጠብጣቢ ኳታኝ፣
የለገሐር ንቁ ጎረምሳ
የእግሬ ጠርዝ በውርጭ የነቃ
ፈረስ ጋላቢ አባ መርሳ
እንደሰውም ኃጢአተኛ የአሪት ዘፀአት እንስሳ
ሁሉም ከጽንፍ የሚጠቅሰኝ ምድረ የተንኮል ማሳ
እኔ ኔግሮው ሸበላ ልጅ ጠብ ጭሬ የማላስነሳ
ታታሪው ይሆንልኛል ባዩ ወፍ ሳይጮህ የምነሳ
የዘመናት ኑዛዜን የነገሩኝን የማልረሳ
በጊዜ ሞገድ የምሳፈፍ የምከንፍ እንደግሪሳ።

ጓዜን ጠቅልዬ መጭ የምል ብድር የሌለኝ ጣጣ
እንደዋልያ የምፈናጠር ያልተጫንኩ ነፃ ሌጣ
እኔ ኢትዮጵያዊው ኔግሮ ጠጉሬ ክምክም ጥቁር ፎጣ
መጫሚያዬም የሰቆጣ
እኔ ያባ ጠቋር ልጅ ምዕራቡን የገመገምኩት
ሳልነካቸው ለሚነኩኝ እንደጥይት የምንጣጣ
እኔ የድንቅነሽ ልጅ እንዴት ደፋሩ ሚስት ልጣ።
እንስት አክባሪ በር ከፋች
የአቅሜን የገበናዬን ስትጠይቀኝ የማላጣ
የወንድነቴን የወጉን የማላሳፍር የማላሳጣ
ቀብራራ የደስ ደስ ያለኝ እንዴት እኔ ሚስት ልጣ።

እኔ ኔግሮው ሸበላ ልጅ ልቤ የዲያመንድ ኩይላ
ከታሪክ ትቢያ ተሸከርካሪ ከማዕበሉ የምነሳ

እኔ ጥቁሩ ቀለም መጣጩ ስር መሰረቴን የማልረሳ
በእንዴት ገጥ ቢሎኝ ዓርባ ሞተር የማስነሳ
እኔ የድንቅነሽ ልጅ ባለድርሳን ባለቦርሳ።
የወንድነቴን የወጉን የማላሳፍር የማላሳጣ
ኔግሮ የደም ግባት ያለኝ እንዴት እኔ ሚስት ልጣ።
እኔ ኢትዮጵያዊው ኔግሮ ሕያው የታሪክ ቋንጣ
እንደራሚዲስ አፋሬንሲስ የአፍንጫዬ ቀስት ደፍጣጣ
መንጋጭላዬም እንደነገሩ የጥርሴም ሰልፍ ገጣጣ
ጥቁርነቴ የሚማርከኝ ቢያነጡኝ የማልነጣ
የብሔረ ጉሽ የሚመራኝ የሚሆንብኝ ኮምጣጣ
እኔ ድብልቅ ድፍርሱ ጠላቸውን የማልጠጣ
ሰክረ ጅማቴ ነዝሮ የማልጋበዝ ለሽርላጣ
አስታራቂው ሰላም ወዳጁ እኔ እንዴት ሚስት ልጣ።
"እንዲህ ሆነ" ታሪክ አውጊ፣ የባንዳ ቃፊር ጋሬጣ
የተፈረፈርኩ ባዘላት ቋጥኝ የተጠረብኩ እንደገበጣ
ጀርባዬ የታረሰ እንደቀራንዮ ሞጣ
ለጀስቲስ የተገረፍኩ እኔ ሳይጠሩኝ እንዴት ልምጣ
ኩራት ያለኝ የተፈተግሁ ሳይሰነዝሩ የማልቃጣ
ሽንበቆ መሳይ ደረተ–ሰፊ
እንዴት አደብ እያለኝ ልቆጣ?
ከማርክሰም ከእየሱስም ከአንድ ምንጭ የምጠጣ
በዘር ካንሰር ለሚያሳምሙኝ የምሆን ቃሪያ ሚጥሚጣ
ያልተጫንኩ ነፃ ሀሳቢ ታጣቂ ንቁ ሸንቃጣ
ሲነጥሉኝ የማልነጠል መልኬ እንደነርሱ መጣጣ
ሳንኮፋን ሲናማ ለማየት ጊዜው ሳይደርስ የምመጣ
በዲሴምበር የቆፈን ብርድ ለሩብ ሰዓት የምገረጣ
የወንድነቴን የወጉን የማላሳፍር የማላሳጣ
ኔግሮ የደስ ደስ ያለኝ እኔ እንዴት ሚስት ልጣ።
መነኩሴ የምትመኛኝ ቁመቴ ጆርዳን ወጋግራ
ሰይጣን የሚጠቅሰኝ ከሩቁ ሳሳጣፉ ደሜ መራራ
የእሳት ቁጣ የሚፈጀኝ እንደመስቀል ዝግባ ደመራ
እንደበረሃ ቅጠል የጠወልግሁ
ቅርንጫፌ ጠይም ገራራ
በዋል ፈሰስ ዋልጋ ሆኜ
እንዴት እኔ በሚስት ልገራ።
ዘረኛ የሚፈትነኝ የወገኖቼን ስም የማስጠራ
መንፈሴ ኮርቶ ያበጠ ፍርሃት ራሱን የምፈራ
አንገቴን የማልደፋ ለወገን ሒስ የማልፈራ
እኔ መሸ አዳሪው ከዳገት ዳገት የማቅራራ
የድምጼ ገደል ማሚቶ ተላትሞ የማያባራ
መይሳው ባለፈረሱ ለዘረኞች የዋህ ፋራ
ሳንኮፋን ሲኒማ ለማየት ጊዜው ሳይደርስ የምመጣ
በዲሴምበር የቆፈን ብርድ ለሩብ ሰዓት የምገረጣ
የወንድነቴን የወጉን የማላሳፍር የማላሳጣ
ኔግሮ የደስ ደስ ያለኝ እኔ እንዴት ሚስት ልጣ።
ጆሮ ግንዱ የሚነቃነቅ መቂናጤ የጎሽ መንጋጋ
እንደ ዮጋ ስፖርት የሚያፍታታኝ
የአጥንቴ ሽመል ለግላጋ
የካብኩትን ሲያፍርሱብኝ ድንጉጥ የማልሆን በርዳዳ
ከቀበሌ ጎጥ የማልወግን ፊቴ ሽብሽብ ጨምዳዳ
እንደሳንድዊች በሚሸጥ ድግራ የማልቆጠር የማልፈነዳ
እኔ የኔግሮው አፈር ገፊው የሕሊና ድጋፍ ግርግዳ።
አንዲት ቀን ካልታጠብኩ ጭቅቅቴ የሚፍተለተል
እንደ አድዋ ጦርነት አስካሪ
እንደምርኮኛ የሚግተለተል
የምዕራብ ጭስ የመረዘኝ ሲከፉኝ "በወዳጄ ልቤ"
በአባቶች ታሪክ የምጠለል፣
ያዝ ለቀቅ ለሚያደርግ ለቃላባይ ዘረጥራጣ
በቲዎሪ ለሚቁነጠነጥ ልቡ ሳልረጋ ቀበጥባጣ
ለትችት ግብሩ ገተርታራ ለዲስኩር ልብሱ ሞጥሟጣ
ሳይገነባ ለሚያፈርስ ለዕድገት ሰናይ ጋሬጣ
የማልያዝ የማልጨበጥ ዝላይ የምችል እንደፌንጣ።
በሐሳብ ባህር የምቀዝፍ እኔ የወገኖቼ ናምራ
ሀገሬ ሲታጠል የሚሸተኝ ርቀት ሰብሬ የምንጠራራ
የህዝቤን ጭንቀት የምጨነቅ
በአየር የምበር እንደአሞራ
ስቃያቸው የሚያፍነኝ የሚገለማኝ እንደብርብራ
ሰውነቴ የሚንቀለቀል በጠረራ እንደበርበራ
የህይወቴ ክር ያልተበጠሰ በሎጥ የነፍስ መከራ።
አንዳንዴም ራሴን የምነቅፍ ነገሩ የጠፋብኝ ጀርጃራ
"እኔስ ማንን ሆኜ ነው" ቁንጫ ያይጥ መሐራ
ዝናቸውን ለመጥቀስ የማልችል መቃብር የማልጋራ
ስማቸውን አፌ ሞልቶ ጀግንነታቸውን የማላወራ
የጥቁር ልጅ ስደተኛው ተበታኙ የዲያስፓራ
ቃል የሌለኝ የሰለልኩ ክብር የሌለኝ የጮማ ሞራ
በአባቶች ፊት የምንቀጠቀጥ ኑዛዜያቸውን የምፈራ
ስማቸውን ለመጥራት ያልበቃሁ
የታሪክ ሪኮርድ ጠንጋራ
አንጎሌ ነጭ ከዋጀ መልኬ ጥቁር ጡሩሩ
ምስል ሁለት የሚሆንብኝ ዓይኔ ብሌኔ ሸውራራ።
ካንሰር ይዞኝ ፍንከች የማልል
በሱባዔ ድርሳን የምመካ
ጉድባ ተደፍቼ የምፀልይ አሞኝ እንዳበባ የምፈካ
ካለ ኢንሹራንስ የምኖር ኃጢአታቸውን የማልነካ
በእናቴ ፀሎት የማብብ አፅቄ በእምነት የተለካ
"አንተ ሰውረኝ" ብዬ የምጋልብ በጠፍ ጨረቃ
አያሌ ወጥመድ የምዘል ለኮሽታ የምነቃ
እንደ እባብ ብልጣ ብልጥ ሆኜ ደፈጣዬ የሚያስመረቃ
እርግብም ሆኜ የምኖር ትህትናዬ የህፃን ጮርቃ።
ስቆምላቸው ለሚያከስሙኝ እንደ ደፋር ጭስ የምበረታ
ጭራዬ የማይያዝ ሲከሱኝ የማልረታ
የፈጥኝ የታሰርኩበትን ፈሮ ካለ ቁልፍ የምፈታ
እንደየሱስም አሳ አጥማጅ እንደማርክስም ከርታታ
እንደሆችሚን ብሔራዊ ግንባሬ የማይፈታ
ወገኔ ሁሉ የሚንቀኝ የሚነግፈኝ ከበሬታ።
ርህራሄ ያለኝ ሆደ ባሻ የልቤ መስክ ርግራጋ
ለጥቁር ዘረኛም የማልጨበጥ እጄን የማልሰጥ ሞጋጋ
በድል ታሪኬ ለሚቀኑብኝ ብርሃን የምሰጥ የማነጋ
በካሪዲዮግራም የተጫረ የልቤ ዌቭ የሚለጋ
እንደካራማራ ተራራ የነርቬ ፋይበር ሰግሳጋ
ከባህር ወለል የሚለጠፍ ሲያሰኘው እንደ ጅጅጋ
እንደራስ ዳሽን ተምዘግዝጎ የሚሽቀለቀል እንደመዘጋ
አፈር ላይ ብወድቅ የማልለወጥ የማላጣብቅ እንደሥጋ
ዘር ቆጥሮ የማልደግም ቅይጥ ብሔር ሠረግራጋ
ሳንኮፋን ሲኒማ ለማየት ጊዜው ሳይደርስ የምመጣ
በዲሴምበር የቆፈን ብርድ ለሩብ ሰዓት የምገረጣ
የወንድነቴን የወጉን የማላሳፍር የማላሳጣ
ኔግሮ የደስ ደስ ያለኝ እኔ እንዴት ሚስት ልጣ።

# ኑሮ በአሜሪካ

በአሜሪካ ኑሮአችሁ ምን ገጠማችሁ? ኑሮን ለማመቻቸት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ባሉ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ላይ ለመወያየት ይህ አምድ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለን። በውይይት የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ይቻላል የሚል እምነት አለን። በተጨማሪም በዚህ አገር ኑሮአችን ተሰባስበን በጋራ የምናከናውናቸውን ተግባራት ለማስተዋወቅም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል እንላለን። አንዱ ከሌላው ልምድ ሊማር ይችላልና። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡ አስተያየቶችም ሆነ የገጠሙኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩት መሆኑ ይታወቅልን።

## እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!!

ከአትናትዮስ
ክፍል 7

በአበሻው አካባቢ ደህና ወሬ ብዙ ጊዜ በስፋት ሲነፍስ አይሰማም። አንድ ትንሽ መጥፎ በገር ከሆነ ግን ያንን አጣፍጦ፣ አሳምሮ ከድርጊቱ በላይ ተጨማምሮ ይወራና በሰፊው መንፈስ ይጀምራል።

"ይገርማል እኮ እከሌና እከሊት አብረው ሲወጡ ከቆዩ በኋላ እሷ ከዳችው" ይባላል። ይህ አሁን ምኑ ትልቅ ነገር ሆኖ ይወራበታል? አንድ ወንድና አንዲት ሴት ተፈቃቀዱና አብረው ሲወጡ ቆዩ፤ ስላልተግባቡ ተለያዩ። ይህ ያለ ሂደት ሆኖ ሳለ ወሬዋ ትጣፍጥና ተጨማምሮባት የአንድ ሰሞን ወሬ ትሆናለች። የእኔም እንደዚሁ ነበር። አንድ ቀን ከአሰገደች ከተለያየን አንድ ወር ካለፈ በኋላ አንዱ ጓደኛዬ ይደውልልኝና

"ምንድነው እባክህ የሚወራው?" አለኝና ጠየቀኝ።

"ምን ሰማህ?" አልኩና ጠየቅሁት።

"ያቺ ስታወጣት የነበረችው ልጅ፣ አሰገደች ነው አይደል ስሟ?"

"አዎ ምነው?"

"ልታገባት ጠይቀሃት አይሆንም አለችህ የሚባለው?" አለ።

"እና አንተ አምነህ ነው ይህን የምትጠይቀኝ?" አልኩት።

"ስማ በሰፊው እኮ ነው የሚወራው፤ ከአንድ ሰው ብቻ የሰማሁ አይምሰልህ!" አለኝ።

"እና ቢሆንስ! አይሆንም ብትለኝ ታዲያ ምንድነው ጉዱ?"

"እውነት ነው እንዴ?"

"ምኑ?" አልኩት

"አንተ ለጋብቻ ጠይቀሃት እንቢ ብላህ ከሆነ እኔ ጓደኛህ ሆኜ እንዴት ሳላውቀው ቀረሁ?"

"እወቅህ አላወቅህ ምን ችግር አመጣ?"

"ስማ ጓደኝነት ለመቼ ነው?"

"አንተ ምን ማድረግ ትችላለህ?"

"የማደርገው ነገር አለ ለማለት አይደለም። ጓደኛህ ስለሆንኩ የምስጢር ተካፋይህም ጭምር ነኝ ብዬ ነዋ!" አለኝ።

የሰው ነገር አይገርማችሁም። አሁን እስቲ ምን ሊያደርግልኝ ነው እንዲሁ እሱም ለወሬ ነው እንጂ! "እባክህን ስለእሱ ባታነሳ ደስ ይለኛል" ብዬ ዘጋሁበት።

አሰገደች ምንም ያህል ወሬውን በፈለገችው መልክ ትንዛ፣ ታስወራ እንጂ ውሸት እውነት መስሎ የሚታየው ለጥቂት ጊዜ ስለሆነ ታገስኩ። መልካሙ ተበጀ "ጉድ አንድ ሰሞን ነው" ብሎ የዘፈነው ዘፈን ትዝ አለኝ።

ከአሰገደች ከተለየሁ ለጥቂት ጊዜያት ከአበሻ አካባቢ ጠፋሁ። ወሬውንም ምኑንም ለመሸሽ። አንድ ቀን ምሽት እንጀራ መብላት አማረኝና ከተማችን ካለው የታወቀ የአበሻ ሬስቶራንት ሄድኩ። ምግብ ቤቱ ውስጥ ብዙ አበሻ አልነበረም። አንድ ጥግ ላይ ካለ ጠረጴዛ አንድ ወንድና ሴት ፈረንጆች ላብ በላብ ሆነው ከበርበሬአችንና ከቅመማችን ጋር ትውውቅ ይዘዋል። ፈገግ አልኩ። ከሌላው ጥግ ደግሞ አንድ ወንድና ሴት አበሾች ቁጭ ብለው ያዘዙትን ምግብ በመጠባበቅ ላይ ያሉ ይመስላል። እንደተቀመጥኩ አሳላፊዋ ውሃና የምግብ ሊስት አመጣችልኝ። ደስ የምትል ወጣት ናት። እንደተቀመጥኩ ከእኔ ትንሽ እልፍ ብሎ ሁለት አበሻ ሴቶች ቁጭ ብለዋል። እነሱም ያዘዙትን ምግብ በመጠባበቅ ላይ ያሉ ይመስላል። አንድ ብርጭቆ ቀዝቃዛ ው ጠጣሁናአሳላፊዋን ጠርቼ የምፈልገውን ምግብ አዘዝኩ። አሳላፊዋ እንደሄደች ከእኔ እለፍ ብለው ቁጭ ካሉት ሁለት ሴቶች አንዷ ላይ ዓይኔ አረፈ። የማውቃት ነገር መሰለኝ። እሷም መለስ ቀለስ እያለች ታየኝ ነበር። አጋጣሚውን ጠበቅሁና ከአንገቴ ጎንበስ ብዬ ጤና ይስጥልኝ እንደማለት አልኩ። እሷም እንደዚሁ እጅ ነሳችና ፈገግ አለች። ከዚያም ደፈር አልኩና ወደ መቀመጫቸው ሄድኩ።

"ጤና ይስጥልኝ፣ ... የምንተዋወቅ መሰለኝ" አልኳት

"ሰላም ... እኔም መሰለኝ" አለችና ጨበጠችኝ። ጓደኛዋንም ጨበጥኩ።

"የት እንደሆነ እንጃ፣ ... ወይ ጊዜው ሩቅ ይሆናል" አልኳት።

"ብቻህን ከሆንክ ለምን እኛ ጋ አትቀመጥም" አለችና ጋበዘችኝ።

"እሺ" አልኩና ቁጭ አልኩ። "እንግዲህ ከየት እንጀምር?" አልኳት። የምንተዋወቅበትን ቦታ ለማስታወስ ያልኩት ነበር።

"አንተ እዚህ እስቴት ቆይተሃል?"

"አንድ ሰባት ዓመት አለኝ።"

"ፊት የት ነበርክ?"

"ቦስተን ነበርኩ፤ ትምህርት ቤት"

"ሌላስ ቦታ አልነበርክም?" አለች

"በኑሮ ሳይሆን በትምህርት" አልኳት

"የት?" አለች። ጥያቄዋ ነገድጓድ ሆነብኝ።

"ሚኒሶታ" አልኳት

"ሚኒሶታ አልነበርኩም" አለች።

"እዚሁ ናችሁ?" አልኩና ተራዬን ጥያቄ አቀረብኩ

"እሷ እዚሁ ናት፤ እኔ ግን ከሌላ ቦታ ነኝ። ለጉብኝት ነው የመጣሁት" አለችኝ ያቺው ስንተያይ የቆየነው

ልጅ። እዚህ የኖረችው ሳትሆን እንግዳዋ ቀልጣፋ ሆነችብኝ።
"ከየት አልኩ"
አንድ ላለንበት እስቴት ቅርብ የሆነ እስቴት ጠራችልኝ።
"ታዲያ ከተማችንን ወደድሽልን?" አልኳት
"ገና በደንብም አላየሁትም፤ የመጣሁት ትላንት ነው" አለችኝ።
ጓደኛዋ ዝም ማለቷ ትንሽ ገረመኝ።
"አንቺን አይቼሽ አላውቅም" አልኳት ወደ እሷ እየተመለከትኩ፤
"እኔ ግን አውቅሃለሁ" አለችኝ። "እዚሁ ነኝ ከራርሜያለሁ።"
ትንሽ እንደማፈር ከጀለኝ። "እኔ ግን አውቅሃለሁ" ስትለኝ የተሰማኝ ሌላ ነው። አጅሬት አሰገደች DUMP አደረግሁት ብላ ከተማውን ያዳረሰች በመሆኗ በዚህ ዝናዬ ይሆን የምታውቀኝ ብዬ ለእፍታ አሰብኩ። ግን ግድም አልሰጠኝ። ስም ተለዋወጥን። እዚህ የከረመችው መቅደስ፣ እንግዳዋ ደግሞ ዓይናለም ይባላሉ። ሁለቱም አሜሪካን ከገቡ ከረምረም ያሉ መሆናቸው ያስታውቃል።

"መቼ ነው አሜሪካ የመጣሽው፣ የመጣሽው?" ብሎ መጠያየቁ ወቅቱ ያለፈበት ጥያቄ ስለሆነ ላነሳው አልፈለግሁም እንጂ ብጠይቃቸው ደስ ባለኝ ነበር። እዚህ ከረምረም ባልን አበሾች የሚቀርብ ቀደም ሲል የተለመደ ጥያቄ ነበር። አሜሪካን አገር በመቆያ ጊዜ ርዝመት የሰውን ችሎታና "ዘመናዊነት" ለመለኪያ የምንጠቀምበት አጓጉል ጥያቄ። በአሁኑ ጊዜ እኔ መጥፎነቱን በመረዳቴ አልጠይቅ እንጂ የዚህን ዓይነት ጥያቄ የሚጠይቁ ሞልተዋል። ጨዋታውም ደራ። ምግባችንም መጣ። እየተጫወትን በላን። ዓይናለም ደስ የምትል ልጅ ብቻ ሳትሆን በጣም ተግባቢና ተጫዋች ናት። አትከብድም። የአነጋገር ለዛዋ ይስባል። አጫውቶ የሚያጫውት ቃና ያለው ድምፅ አላት። ደስ ስላለችኝም እንደሆነ አላውቅም ብቻ ሁኔታዋንና አቀራረቧን ወደድኩላት።

"እንዴት ነው ከተማችንን ከወደድሽው ወደዚህ Move ለማድረግ ዓላማ አለሻ?" አልኳት።
"ገና አላየሁትም። ከወደድኩትማ መቼ ይቀራል ብለህ ነው" አለች። ፈገግታ አከለችበት።

"ታዲያ ዕድሉ ቢሰጠኝስ?" አልኳት ተራዬን እኔም ፈገግ ብዬ። አንዳንዴ ቅልጥፍናዬ እኔንም ይገርመኛል። ሴቶች ቀልጣፍ የሚል ወንድ ይወዳሉ የሚል እምነት ካላቸው ሰዎች የምደመር መሆኔን አውቀዋለሁ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተማርኩት ነገር ነው።

"የምን ዕድል ቢሰጥህ?" አለችኝ።
"ከተማችንን የማስጎብኘት" አልኳት።
"ጠባይህ ታይቶ" አለችኝ።
ዞር ብዬ ጓደኛዋን መቅደስን አየሁዋት።
"በጠባዬ መጥፎነት እንኳ አልታማም። እዚህ ነዋሪዎቹ ይመሰክሩልኛል። አይደል እንዴ መቅደስ?" አልኳት።
"ስለ ጠባይህ እኔ ምናውቃለሁ?" አለች መቅደስ እየሳቀች።
"መቼም መጥፎ ጠባይ ቢኖረኝ በዚያ ጠባዬ ታዋቂ ሆኜ አገኝ ነበር" አልኩኝ።
"እና ጥሩ ጠባይ አለኝ ትላለህ?" አለች ዓይናለም አንዴ እኔን አንዴ መቅደስን እያየች።
"በኩራት!" አልኳት
"በራሱ የሚተማመን ወንድ ደስ አይልሽም መቅደስ?" አለቻት። መጀመሪያ የምታሾፍብኝ መስሎኝ ነበር። ዓይናለምን ሲያይዋት ግን የምትናገረው ነገር ሁሉ ከልቧ ይመስላል።
"በል እንግዲህ የተፈቀደልህ ይመስላል። አስጎብኛታ!" አለችና መቅደስ መስማማቷን በፈገግታ ፂምር ገለፀች። ምግባችንን በልተን ስልክና አድራሻ ተቀያየርን በሚቀጥለው ቀን ከሥራ ቀርቼ ላስጎበኛት ተስማምተን ተለያየን።

እንደሌላው ጊዜ ስሜቴ አልተብከነከነም። ድሮ አንዲት አዲስ ሴት ልጅ በተዋወቅሁ ቁጥር አግኝቼአት ከእኔ ጋር እስከምትወጣ ድረስ የሚሰማኝ የመንፈስ ዕረፍት ማጣት፣ የመቅበዝበዝና የጉጉት ባህርይ ዛሬ የለም። ምናልባትም ከልምድ እየተማርኩ በመምጣቴ ስሜቴ እየደነዘ መጥቶ ሊሆን ይችላል። አልያዝና አልገባህ፤ አልጨበጥና አልስማማህ ያለኝ የሴቱ ባህርይ የፈጠረብኝ ስሜት ይሆን?

በሚቀጥለው ቀን በተባባልነው ሰዓት ደወልኩላትና ሂጄ ከጓደኛዋ ቤት ወሰድኳት። ጓደኛዋ ሥራ ገብታ ኖሮ ብቻዋን ነበረች። ግባም አላለችኝ። ከዚያ በመኪና ሆነን ከተማዋን እየተዘዋወርኩ አሳየሁዋት። የምኖርባት ከተማ የምትታወቅባቸውን ቦታዎች በሙሉ አስጎበኘሁዋት። በጉብኝቱ ወቅት ቀልድ አዘል ጨዋታዎቼን እያመጣሁ አስቃት ጀመር። እሷም በዚያ ለዛ ባለው ድምጿ የምታወራቸው ጨዋታዎቿ አይሰለቹም።

ምሳችንን ለመብላት አንድ የሜክሲካን ምግብ ቤት ሁለታችንንም ተስማማንና ሄድን። ለምሳ ምግብ ቤት እስከገባን ድረስ በኋላም ምሳችንን በልተን እስከምንጨርስ ድረስ በአጠቃላይ አዋራት የነበረው ስለከተማችን ጥሩነት፣ እዚህ አገር ስለአበሻው ኑሮ፣ በመሳሰሉት ላይ ነው። ዓይናለም በእርግጥ ደስ ብትለኝም ገና ሳልላመዳት ምንም ነገር ማንሳቱ አልታየኝም። በዚህ ላይ ግልፅነቷና ተጫዋችነቷ ከተለመደው የአበሻ ሴት ባህርይ የሚለይ በመሆኑ ገና ሳልተዋወቃት፣ ወይም የዚህ ዓይነቱን ነገር እሷ ሳትዘጋጅበት ባነሳባት ቀንዴን ትለዋለች ብዬ ስለፈራሁም ፂምር መሰለኝ። በዚህ ላይ ደግሞ ለከተማው እንግዳ በመሆኗ እንግዳነቷንና የእኔን አስጎብኝነት መሣሪያ በማድረግ ከእሷ advantage ለመምታት የተዘጋጀሁ መስዬ ለመታየትም ካለመፈለግ ይመስለኛል።

ምሳችንን በልተን እንደጨረስን ቡና አዘዝንና ለየት ያለ ጨዋታ ጀመርን። ስለእኔ ለማወቅ አንዳንድ ጥያቄ በማቅረቧ ያንኑ መሠረት አድርጌ እኔም የጨዋታውን አቅጣጫ አስቀየርኩ።

"አንተ ይህን ከተማ የወደድክ ይመስላል" አለችና ለርዕሱ መቀየሪያ የሚረዳ ጥያቄ አቀረበች።
"ከአየሁዋቸው ከተሞች ሁሉ ተሽሎኝ ነው መሰለኝ እዚህ ለረዥም ጊዜ የኖርኩት" አልኳት
ስለሥራዬም ጠየቀችኝ። ነገርኳት።
"እንዴት ነው ብቻህን ነህ?" አለችኝ።
የጥያቄው አዝማሚያ ቢገባኝም ግልፅ እንድትሆን በመፈለግ "ብቻህን ስትይ?" አልኳት
"ማለቴ አግብተሃል ወይ?" አለችኝ።
"አላገባሁም፤" አልኳት።
"ምነው?" አለችኝ።

ምን መልስ ልስጥ። ትንሽ ቀልድ ብጤ ጣል ላደርግበት ፈለግሁ። “ገና አንድ ፍሬ ልጅ እኮ ነኝ” አልኳት ፈገግታ እስከትዬ
“እውነቱን እኮ ነው” አለች።
“መልሱን እኔም ራሴ አላውቀውም፤ ምናልባት እንደፈረንጆቹ 'The right one' ስላልመጣች ይሆናላ!” አልኳት።
“ከዚህ ሁሉ ሴት!” ብላ ፈገግታ አከለችበት።
“ከየት ሁሉ? ... ” አልኩና ጥያቄዋን በጥያቄ መለስኩት።
“እሱስ ሞልተዋል። ዓይንህን ከፍተህ ማየት ስላልቻልክ ወይ ደግሞ ሴቶቹን የምታይበት መነፅርህ በደንብ እንዳያሳይ አድርጎ የተሠራ ሆኖ ይሆናል፤ አይመስልህም?” አለችኝ።
“ማሳየትስ ያሳያል፤ መነፅሩ በጣም የጠራውን ብቻ ለይቶ የሚያሳይ በመሆኑ ሳይሆን ይቀራል?”
“እርግጠኛ ነህ? ... የሌላው መነፅርስ አንተን አጥርቶ ማሳየቱን ምን ያህል እርግጠኛ ነህ?” አለች። በአነጋገር የምትሸነፍ ዓይነት አልመሰለችኝም።
“እሱማ ልክ ነሽ። እንግዲህ መጣጣም ካለመቻል ይሆናል?” አልኳት።
“ምን መሰለህ በሁሉ ነገር መጣጣም አይቻልም። መቶ በመቶ perfection መጠበቁ ሞኝነት አይመስልህም?” አለች። በጣም የበሰለ አነጋገር ነበር።
“ልክ ነሽ” አልኳት።
“ይህን perfection በመጠበቅ ስንቱ ዕድሜው እንዳለፈበት ታውቃለህ። እና መጠነኛ መግባባት ካለ ያንን መሰረት አድርጎ ሌላውን አብሮ በመኖር መግባባትና መስማማት ይቻላል።” አለች። ፈገግ እያለች።
“ስለ እኔስ ይህን አልሽ፤ አንቺስ እንዴት ነው?”
“እኔም አላገባሁም። ይህንን ስልህ በአንተ ላይ ብቻ ለመፍረድ አይደለም። እኔም ራሴ በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ እንዲህ ልበል እንጂ በተግባር ለመተርጎም የሚይዘኝ ነገር አለ።”
እንደዚህ ያለ ቁም ነገር በመጀመሪያ ትውውቅ ላይ ከሴት ጋር ሳወራ ይህ የመጀመሪያዬ ነው። ለዓይናለም ያለኝን ግምት ከፍ አደረግሁት።
“እና በአሁኑ ጊዜ ለዚህ ቁምነገር የምታስቢው ሰው አለሽ?” አልኩና ጠየቅኋት።
“እንዲህ ያለ ጥያቄ እኔን ለመጠየቅ ምን አነሳሳህ?”
“እእይ! እንዳው ለማወቅ ብዬ ነው” አልኳት።
“አውቀህስ?”
“ይህን ካወቅሁ በኋላ የምለውን በማውቀው ነገር እወስናለሁ።” አልኳት ፈገግ ብዬ
“እዎ አለ ብልህ ምን ልትለኝ ነው?”
“በእርግጥ አለ?” አልኳት።
“ብልህስ ነው ያልኩት።”
“ብልህሳ ብሎ ነገር የለም። ካለ አለ፣ ከሌለም የለም።”
“እሺ የለም።” አለችኝ።
“ከሌለማ ጥሩ” አልኳት ፊቴን በፈገግታ ሞልቼ።
በውስጤ የተሰማኝን ደስታ ልነግራችሁ አልችልም።

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

---

<u>በእንግዳ አክባሪነት ስም</u> ...

ከገጽ 35 የዞረ

ሲነሳበት “በተለይ እንደዚህ ዓይነት የጎረቤት እብሪተኞችን የሚገባቸው ነገር ቢኖር ዲፕሎማሲ ሳይሆን አፍንጫቸውን ማለት ነው” ሲል ያስደስተኝ ነበር። በተለይ በኬንያ የነበሩ ስድተኞች ለሳምንታት ይከበሩ እንደነበረ ትዝ ይለኛል።

የዚህ ጽሁፌ ዓላማ የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ክብር፣ ባህልና ህልውናውን የሚነኩትን መከላከል መቻል እንዳለበት ለማስታወስ ሲሆን ሕዝቡ የራሱ ንብረትና ባህል ተጠቃሚ መሆን አለበት። የሱማሌ ስደተኞች የተባበሩት መንግሥታትን ህግና የኢትዮጵያን ሕዝብን ባህልና ህግ ጠብቀው (ተገዝተው) በሥነ ሥርዓት እንዲኖሩ መንግሥትና ሕዝብ እንዲነግሩዋቸው ያስፈልጋል። ከዚህ በተረፈ ግን በምንም ዓይነት ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ህልውናውን አሳልፎ መሸጥ የለበትም። ህልውና ደግሞ ባልሳሳት ከኤርትራም ይበልጣል። ኢትዮጵያን እግዚያብሔር ይጥብቃት! አሜን።

---


A TO Z
ELECTRONICS
& GIFTS
220V/110 Volt Appliances
*Audio-Video-Toys-Cameras-Phones-Stereos-Luggage-*
*Fax Machines-Watches-Gift Items* - Etc.
ኤ ቱ ዚ ኤሌክትሮኒክስ
We do Digital Vedeo Coversion
From PAL to NTSC & Vice Versa
ከፓል ሴካም ወደ ኤንቲሲና
ከኤንቲሲ ወደ ፓል ሴካም
ቪዲዮ መገልበጥ
ኢትዮጵያ መስራት የሚችሉ
ባለ 220 ቮልት የኤሌክትሪክ ዕቃዎች
በርካሽ ዋጋ
1713 CHURCH ST., SUIT A-1
DECATUR, GA 30033
*Jayendra Patel & Dipa Patel*
Tel/Fax: (404)299-9196


# ከአበው

## ለንግግር ጥበብ
## የታሪክና ምሳሌዎች አገባብ

ከመጋቤ አዕላፍ መክብብ አጥናው

### የቃላት ትርጉም

1. ታሪክና ምሳሌ ሲባል ተረት ወይም ልብ ወለድ አይደለም። አፈ ታሪክም አይደለም። ለቀልድ፣ ለሳቅ፣ ለሥላቅና ለጨዋታ ብቻም የሚነገር ቧልት ነው ብሎ ማሰብም አደገኛ ስህተት ነው። ነገር ግን ዕውነተኛ "ታሪክና ምሳሌዎች ከንግግር አረቄ ተጨምቀው የሚወጡ ናቸው" በሚለው አነጋገር ሁላችንም ልንስማማበት ይቻላል። ብዙዎቹ ታሪክና ምሳሌዎች የዕውነት ነፀብራቅ ናቸውና።

በመሰረቱ ታሪክ ከዕውነተኛ ድርጊት የሚመነጭ ሲሆን አንዱ ዓይነት ታሪክ ለሌላው ታሪክ ማስረጃ ሆኖ ሲቀርብ ምሳሌ ይባላል። ስለዚህ ታሪክና ምሳሌ ቀደም ሲል በተፈጸመ ወይም ሊፈጸሙ ይችላሉ ተብሎ በሚታመንባቸው ድርጊቶች ላይ የሚመሰረት ነው። ስለዚህም የአንዱ ወቅት ታሪክ ለሌላው ዘመን ታሪክ እንደምሳሌያዊ ማስረጃ ሆኖ ሲጠቀስ በተረት ዓይነት መተርጎምና እንደ ቀልድ አድርጎ መመልከት ስህተት ነው።

በዕርግጥ የሚናገረውም ሆነ የሚፃፈው አንዳንድ ታሪክና ምሳሌ የሚያስቅም የሚያሳዝንም ሊሆን ይችላል። ታዲያ የሚያስቀውን ነገር ሁሉ ተረት ወይም ቀልድ ብለን ካወራነው ወይም እንደቧልት አድርገን የምንወስደው ከሆነ ትርጉማችን ትክክል አይደለም ማለት ነው።

ሌላው ችግር ደግሞ የታሪክና ምሳሌዎችን አጠቃቀም፣ አጠቃቀስና የአገባባቸውን ስልት አለማወቅ ነው። "ጥሩ ድምጽ የሌለው ሰው ሶሆ ባያለቅስ ይሻላል እንዲሉ የታሪክና ምሳሌዎችን አገባብ ያላጠኑ ሰዎች በምሳሌ ለመናገርም ሆነ ለመፃፍ ባይሞክሩ መልካም ነው ቢባል ድፍረት አይደለም።

2. ተረትና ምሳሌ ሲባል ግን አብዛኛው ልብ-ወለድና አፈ ታሪክ መሆኑን ማጤን ይገባናል። ተረትና ምሳሌ ብዙውን ጊዜ በእንስሳትና አራዊት በአዕዋፍና በሌሎችም ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት ወይም በሣር ቅጠሉ፣ በዕፀዋት ሁሉ ተመስለው ወይም እነዚህን ሁሉ በሰዎች አስመስለው አዋቂዎች ሰዎች ማለትም ልዩ ተሰጥዎ ያላቸው ተናጋሪዎች በቃልም ሆነ በጽሁፍ ሳባቸውን የሚገልጡበት ፈሊጥ ነው። ይህን ለመገንዘብ በታላቁ ኢትዮጵያዊ ደራሲ አቶ ዲበለማየሁ "ተረት ተረት የመሰረት" በሚል ርእስ የተፃፈችውን ትንሽ መጽ ፍ ማንበቡ ይበቃል።

በጥንት ግሪክ አፈ-ታሪክ ኤዞፕ ተብሎ የሚጠራ ታላቅ አሽሙረኛና ተረበኛ የሆነ የንግግር ጥበብ ሰው ተረትና ምሳሌን መሠረት በማድረግ የሰዎችን መጥፎ ጠባይ ማረሚያ፣ ድክመትን ከፋትና ተንኮልን፣ ምቀኝነትን፣ ትዕቢትን፣ ከንቱ ትምክህትን ሁሉ ማጋለጫ ሃሳብ ማማንጨት ችሏል። የፖለቲካ መሪዎችን እንኳ ሳይቀር ተችቶበታል። ለማስረጃ ያህል የሚከተለውን አጭር ተረትና ምሳሌ እንመልከት።

"አንድ ጊዜ" አለ ኤዞፕ በመተረብ ሲናገር፤ "አንድ ጊዜ አንዲት ቀበሮ በአንዲት እንስት አንበሳ ላይ መዘባበት ፈልጋ በንቀት የአሽሙር አነጋገር 'ወዲያ እባክሽን አንቺ በአንበሳነትሽ የምትመኪው በከንቱ ነው። እንደእኛ እንደቀበሮዎች መንታ መንታውን መውለድ አትችይም እኮ! ለመሆኑ ከአንድ በላይ ወልደሽ ታውቂያለሽን?' ብላ ጠየቀቻት? እንስት አንበሳይቱም ስትመልስ 'ቁም ነገሩ መንታ መንታውን የቀበሮ መንጋ ከመቀፍቀፉ ላይ አይደለም። እኔ የምወልደው አንድ ብቻ ቢሆንም እንኳ ያው አንዱ የአንበሳ ደቦል መሆኑን አትርሺ' አለቻት በማለት ይተርካል።" ይህም አባባል ወሳኙ ቁም ነገር መታየት ያለበት ከዓይነቱ እንጂ ከብዛቱ አለመሆኑን ይገልጥልናል።

3. ቧልትና ቀልድ የተባሉት ነገሮች ደግሞ ከታሪክና ምሳሌ ከተረትና ምሳሌም የተለዩ ናቸው። እነዚህም ቧልትና ቀልድ መገኘት የሚችሉት እንደነአለቃ ገብረ ና ካሉቧልተኞች ንግግር ነው። ታዲያ ለጊዜያዊ ሣቅ ጨዋታ ያህል እንጂ ለቁም ነገር የሚጠቀሱት በጣም ጥቂቶች ናቸው።

4. ታሪክና ምሳሌዎች አጫጭርና ረጅም የሃሳብ መግለጫዎች ሆነው በሁለት ይከፈላሉ። የረጅሞቹን ታሪክና ምሳሌዎች ለሌላ ጊዜ እንቅጠርና የአጫጭር ታሪክና ምሳሌዎችን ማስረጃዎች ለዓይነት ያህል እንጥቀስ

1. "በሾላ ዛፍ ፍሬ ውስጥ የሚገኝ ትል በውጭ ሌላ ዓለም መኖሩን አያውቅም" (ስለ ሃሳበ ጠባብ ሰው የሚጠቀስ ነው።)
2. እባብ ቀጭን ነው ተብሎ አይረገጥም።
3. ለወዳጁ ማር ወለላ፣ ለጠላቱ እሜኬላ።
4. ልጅህን በክንድህ ሚስትህን በልብህ መያዝ ይገባሃል።
5. በመስከረም የሚያብድ በሰኔ ወር ሱሪውን ከፍ ከፍ ማድረግ ይጀምራል። (ከአበደው ያገረገረው ይበልጣል)።
6. በህይወት ሳሉ በነገር እሾህ መውጋት ሲሞቱ ግን የአበባ ጉንጉን ይዞ እያለቀሱ መሸኘት ምን ይባላል?
7. እንጨት በሌለበት ሀገር ጉሎ በላ ምሶሶም ይሆናል ይባላል።
8. በሞኝ ሰው ክንድ የእባብ ጉድጓድ ይለኩበታል።
9. ግመል መልኳ የተበላሸው በኮሚቴ ተሰርታ ነው። (አንዱ እግሩዋን፣ ሌላው ደግሞ አንገትዋን ሲስብ፣ ሌላው ደግሞ ሻኛ ሲያወጣላት ቅርፁዋ ተበላሸ ለማለት ነው።)
10. በተከፈተ አፍ ባዶ ራስ ይታያል። (ለፍላፊዎች የሚገሰፁበት ኃይለ ቃል ነው።)
11. "ለመሆኑ ሰይጣን ልጅ አለው ወይ?" ለሚል ጥያቄ አንድ አዛውንት ሲመልሱ በተግባር መጥፎነት የሚያውቋቸውን የሁለት ሰዎች ስም ጠርተው "እከሌና እከሌ የበኩር ልጆቹ ናቸው ሌላውማ ስንቱ ተቆጥሮ?" አሉ ይባላል።
12. የሰነፍ ሰው ቁጣ ከድንጋይና ከአሸዋም ይከብዳል። (ምሳ. ሰሎሞን 27:3)።

ይቀጥላል።

# ከዚህም ከዚያም

## ከአገር ቤት ጋዜጦች የተወሰደ

● ሰባ ስድስት ሺህ ኩንታል የምግብ እርዳታ ውል ተፈረመ! መባልን ብሰማ ነው መጠየቄ?

አያልነህ - ከካዛንቺስ

▶ ባለ ቦቃ ታርጋዎቹ የኤርትራ ከባድ መኪናዎች እያሉ እንኳን 76,000 ይቅርና 76,000,000 ኩንታል ውል ቢፈረም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከደረቅ ፊርማ በስተቀር ጠብ የሚልለት ነገር የለም።

● አዲሱ የኢትዮጵያ ባንዲራ ምነው አይውለበለብም?

ስህን - ከጎተራ

▶ መሃሉላይ የደረቱበት የደደቢቱ አሣር የሚያህል ኮከብ እንዴት አድርጎ ያውለብልበው ብለው ነው?

● የመንግሥት ባለስልጣናት ብዙዎቹ ያልተማሩበት ምክንያት ምን ይሆን?

ሐ ብታሙ - ከ6 ኪሎ

▶ ጠ/ሚ/ሩ "ሀገርን ለመምራት ሃምሳ አለቃም ይችላል!" ብለው የዛሬ አራት ዓመት የተናገሩትንብ መርሃ ዊአባባል ተግባራዊ ለማድረግ አስበው ይሆናላ!

● አንድ ሰሞን ጎሹ፣ ጥቁር አንበሳ፣ ከፋኝ ... ስትሉ ነበር። አሁን የት ገቡ?

ከተማ - ከመርካቶ

▶ ዥጉርጉር አንበሳ ሆነው ለመምጣት እየመከሩ ነው።

● የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን ዘንድሮ ምን ዓይነት ጉድ መጣበት?

ዲያቆን ብርሃኑ - ከኡራኤል

▶ "ነገሩ የጠፋው በመፈንቅለ ፓትሪያርክ ሥልጣን የተቀማ ዕለት ነው" እያሉ የተቃዋሚው ሰልፈኞች ሲያሙ የት ነበሩ?

● "በሀገራችን ያለው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ ነው!" እያሉ ሬድዮና አዲስ ዘመን የሚያሰራጩትን ፕሮፓጋንዳ ምን ትለዋለህ?

ደረጀ - ከፒያሳ

▶ "ዶሮን ሲያታልሏት ኪሲንግ ነቀሏት!" የምትለው የአራዳ ልጆች አባባል ይኼኔ ነው የምትጠቀሰው።

● ባለፈው ጊዜ ያዋጣችሁት የፓትሪያርኩ ፎቶ ምነው የቦካሳን መሰለኝ?

ሐረገወይን - ከጉለሌ

▶ ከሁለት ፈረንጆች ጋር የተነሱትን ፎቶ ደግሞ ያወጣን ዕለት "የሆሊውዱን አክተር ራምቦን ከየት ይዛችሁ መጣችሁ?" ሊሉን ነዋ።

● የሬድዮው ጋዜጠኛ የፕሬስ ድርጅት ም/ሥ/ አስኪያጅ መሆኑን ሰማህ?

ሃይማኖት - ከጎጃም በረንዳ

▶ በየዕለቱ የወሬ ቄጠማ እየጎዘጎዘላቸው እንኳን ይህቺንና የም/ቤት ፕሬዚዳንት መሆን ሲያንሰው ነው።

● ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ ከቻይና ጋር ሽብ ረብ ሲያሰኛቸው የከረመው ጉዳይ ምክንያቱ አልገባ ቢለኝ ነው የደወልኩልህ።

ዳኛቸው - ከ4 ኪሎ

▶ የአሜሪካው አክሮባት አልሳካ ሲላቸው እንደ ጆርጅ ዊሃ ወደ ቻይናው ካራቴ መቀየሳቸው ይሆናላ!

● በከተማችን የተውለበለበው ቀይ ባንዲራ የትግል ስሜቴን ቀሰቀሰው።

ኩሪባቸው - ከሳሪስ

▶ ወደ ቻይና ደውለሽ "አኩፓንቸር" መርፌ ተወጊ፤ የእኔ እመቤት።

● የአሜሪካ የውጪ ፖሊሲ ጥቅሟን በማስከበር ላይ የተመሰረተ ነው። የእኛስ ምን ይመስልሃል?

ተስፋዬ - ከእስጢፋኖስ

▶ የእኛ ደግሞ የጥምር ዜጎችንና የባለ ታፔላዎችን ጥቅም ማስቀደም መሆኑን አጡት?

● ፕሬዚዳንት ነጋሶ "እኛ የምናውቀው አንዲት ቻይናን ነው!" ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው ነው?

ለገሠ - ከኮተቤ

▶ አንዲት ኢትዮጵያን ዘንግተው 14 ሽርፍራፊዎችንማ ካወቁ ሰንብተዋል።

● 6 ኪሎ የቀድሞ ባለሥልጣናት ችሎት በሚታይበት ግቢ የዘመነ-ደርግ አውቶቡስ አጥር ጥሶ ገብቶ ሰነድ ማበላሸቱን ሰማችሁ?

ሳራ - ከቤላ

▶ መስማቱንስ ሰምተናል። "በወያኔ ፍርድ ቤት አልቆምም" ያሉት ኮ/ል መንግሥቱ ከጋንሂል ቤተ መንግሥታቸው በሪሞት ኮንትሮል ካላዘዙት በስተቀር የእግዚአብሔር ተዓምር ሊሆን መቼም አይችልም።

● "በሽፍታነት የምትታወቀው የቀድሞዋ የሕንድ ንግሥት ለፓርላማ አባልነት ተመረጠች!" መባልን ብሰማ ነው "ሀሎ ..." ያልኩህ።

ዳንኤል - ከሰንጋ ተራ

▶ እንዲች ዓይነቷ አባባል "የአቶ ዳዊት ም/ቤት በሽፍቶች የተሞላ ነው!" ብለው ቅኔ ለመዝረፍ ዳር ዳር እያሉ መሰለኝ?

● "ለትላትልና ለበራሪ ነፍሳት መርዝ መፍትሔ ተገኘለት!" ስለሚለው ጽሁፍ ምን አስተያየት አለህ?
ከአዲስ - ከጌሻ ሰፈር
▶ እኛን ያስቸገሩን በየቀበሌው የሚርመሰመሱት የፖለቲካ ትሎች እንጂ የተፈጥሮውስ እዳው ገብስ ነው።

● በከተማችን ጎዳና የመኪኖች ጎማ ፍንዳታ ጩኸት የምን ምልክት ይመስልሃል?
እንዬ - ከሸላ
▶ "የወደፊቱ ጦርነት ምልክት ነው!" ብዬ ዘብጥያ ብወርድ ምን ይጠቀማሉ?

● ኩባና ሊቢያ ተወዳጁን ሰማህ?
ኤፍሬም - ከፒያሳ
▶ ክሊንተንን ከወዲሁ አልጎን አዘጋጁ ማለት ይቀላል አይሉኝም?

● የቻይና በአፍሪካ ላይ ማተኮር ምን ይባላል?
ጆኒ - ከ22 ማዞሪያ
▶ የኤምፔሪያሊዝምና የሶሽዮ-ኢምፔሪያሊዝም ሽኩቻ ቢባል ተቃውሞ አሎት?

● ሊቢያ የጦር አውሮፕላኖችን በገፍ ወደ ሀገሯ የምታስገባው ለምን ይመስልሃል?
መንግስቱ - ከ4 ኪሎ
▶ "በሱዳን የመጣ፣ በዓይኔ የመጣ!" ብላ ይሆናላ!

● የውጪ ጉዳይ ሚኒስትራችን ባለፈው ጊዜ "ያልበሰለ መንግሥት" ማለታቸውን እንዴት አየኸው?
ታምሩ - ከቦሌ
▶ የም/ጠ/ሚኒስትሩን ቦታ በመከጀል የተዘረፈች ቅኔ መስሎዎት፣ በእፍ ወለምታ ዘብጥያ ቢወርዱ እኔ የለሁበትም።

● የአፍሪካ ግጭቶች ኮሚቴ መቋቋም በሀገሮች መሃል ሊነሳ የሚችለው ፀብ ሊቀንስ ይችላል ብለህ ትገምታለህ?
እስራኤል - ከተክለሃይማኖት
▶ እኔ የምፈራው ኮሚቴዎች ራሳቸው እርስ በእርስ ተጋጭተው ዓለምን ጉድ እንዳያሰኙ ነው።

● ፕሬዚዳንት ነጋሶ አንድ ሰሞን "የግድግዳ ጌጥ" ሆነው ሰነበቱሳ?
ጌትነት - ከእስራኤል ጋራዥ
▶ "የፖለቲካው ጌጥነት ቢነፈጋቸው፣ እንዴት የግድግዳ ላይ ጌጥነት ይነሳቸው?" እያሉ አሽሙረኞች ሲያሽሙሩባቸው የት ነበሩ?

● አንድ የባህር ማዶ መፅሄት ሳነብ "ዶ/ር ነጋሶ ጀርመናዊት በማግባታቸው ከኢትዮጵያ ይልቅ ለአውሮፓ ጥብቅና ይቆማሉ!" የሚል በማየቴ በጣም ገረመኝ።
አቻምየለህ - ከመርካቶ
▶ ወትሮውንስ "ሴት የላከው ሞት አይፈራም!" አይደል የሚባለው?

● አለቃዬ በወጣ በገባ ቁጥር "ካልሳምኩሽ" እያለ ችክ ይልብኛል።
አስቴር - ከካዛንቺስ
▶ "የ'ኪሲንግ' ዳር ዳሩ ያቺን ደሳሳ ጎጆ ፍለጋ ነው" ሲሉ የባር ሽምስ ጉብሎች ነገሩን ወርሰውታል።

● "ስልሳዎቹ የቀድሞ ባለሥልጣናት ሲረሸኑና ሲቀበሩ በዓይኔ ተመልክቻለሁ!" ያሉት የልዩ አቃቢ ህጉ ምስክር እስከዛሬ ድረስ የት ከርመው ይሆን አሁን ብቅ ያሉት?
ቴዎድሮስ - ከኮልፌ
▶ "ኢህአዴግ ለቁርጥ ቀን ያስቀመጣቸው የቀውጢ ቀን ምሥክሩ ናቸው!" እያሉ የጨርቆስ ሰልቫጅ ነጋዴዎች ያሟቸዋል።

● የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስዩም መስፍን ስለኤርትራውያን የዜግነትና ስራ ጉዳይ ሲጠየቁ "ምናለበት ራሳቸውን ጠቅመው አገራችንንም ቢጠቅሙ" ማለታቸው አላስገረመህም?
ከፍያለው - ከአራ በከንቱ
▶ ከመገረምም አልፌ ወንራዬ ተነስቶብኝ ነበር።

● ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት ከአይሮፕላን ወደ አገራቸው ሲገቡ ወደ እስር ቤት ተጣሉ፣ አቶ ዳዊ ኢብራሂም የኢ.ሠ.ማ.ኮ. ፕሬዚዳንት በ83ኛው ዓለም አቀፍ ሌበር ኮንግረስ ላይ እንዳይገኙ ከአገር መውጣት ተከለከሉ። ይሄ ምን ማለት ነው? ምንስ አገር ላይ ነው ያለነው?
ይገረሙ - ከሳሪስ
▶ መውጣትም መግባትም ከማይቻልበት አገር!

● ኧረ እነዚህን ጉልት ሻጮችና አዟሪዎችን ፖሊስ ምን አድርጉ ብሎ ነው በቆመጥ የሚያባርራቸው?
ጀማል - ከመርካቶ
▶ "ድህነትን ለማጥፋት ድሆችን ማጥፋት" የሚለውን የኢህአዴግን መርህ ለመተግበር።

● ምነው እነዚህ ባለስልጣኖች እርስ በእርሳቸው በቋንቋ አልግባባ አሉ? ዛሬ አንዱ የተናገረውን ነገር ነገ አንደኛው ተነስቶ ማን አለና! አይሆንም ብሎ ያፈርሰዋል። ነገሩ ምንድነው?
ንጉሤ - ከቄራ
▶ እግዚአብሔር የባቢሎንን ሰዎች የበታተናቸው መግባቢያ ቋንቋ አሳጥቷቸው ነበር። የዛሬው ለእኛ መሪዎች ምልክቱ ይሆን?

# እኔ የምለው !

## የሚያበሳጭ ፀባይ

ከውሂብ ጥሩነህ (ዳላስ)

"እንዴት ሠንበታችኋል?" ብዬ በጨዋ ጥያቄ ብጀምርስ? ሰላምታዬ ታዲያ 'ሣሩም ቅጠሉም' እያበሳጨው ቁና ቁና ለሚተነፍሰው ላገር ልጅ እንጂ ይሄ ደረቱን አሳብጦ፣ ፊቱን ከስክሶ፣ አላፊ አግዳሚውን የሚገላምጠው "ጡንቸኛማ" በቃ ... እግር ካላሳመ በደረቁ ሰላምታ አይቀበልም አሉ ... እነ ኮስማኔ!!

እኔ የምለው ጎበዝ ... ይሄ ደረትና ክንድ ክንዱ ላይ "የተቋጠረ ምናምን" የቀበረ የሚመስል ስፖርተኛ ሁሉ ቲኬቱን በጊዜ ቆራርጦ ለተጨማሪ "ስፖርት" ዋሽንግተን መግባቱን ሰማችሁልኝ ወይ? ('ምን እናድርግ ታዲያ?' አትሉኝም ... ክንድና ደረታችሁ ላይ ጡንቻ እንዳይወጣ የተረገማችሁ ኮስማኔዎች!)

ታዲያ በዚች "የበጋ ስፖርት" እያሳበበ "እነ ግርማ ቾሩ"ን ዋሽንግተን ድረስ ተከትሎ የገባ ሌላም አይነት "የሰፈር ስፖርተኛ" አለ አሉ ... ሆድ ዕቃው ላይ የዘመዱን 'የአደራ ዕቃ' ደብቆ ያስቀመጠ የሚመስል!! ባለፈው ዓመት የሆነ ቡድን ተጫዋቾች የሆኑ "ስፖርተኛ" ማሊያቸውን ከዕምብርታቸው ቀዳዳ በታች ስበው ማውረድ ተስኖአቸው የሆድ ዕቃቸው ግማሽ ተገልቦ የቡድናቸው አስራ ሁለተኛ ተጫዋቾች ይመስሉ ነበር አሉ ... ዘንድሮ መቼም የማይሰማ ጨዋታ የለም። ("ቦርጫም ሁላ ብለህ በቃ ይውጣልህ የምትሉኝ ነገረኞች አትጠፉም!)እኔው? ... አይወጣኝም!!

እኔ የምለው ግን ሰዎች ... "ስፖርተኛ" ሆኖ ሰውነት "ማባበጥ" ሲጀምር ፀባይም አብሮ ይቀየራል እንዴ? (ጥጋብም አብሮ ይመጣል ወይ ማለቴ ነው!)

ከአገር ከሰፈሩ ለበርካታ ወራት የጠፋ ጓደኛዎ በስንት ፍለጋ አግኝተውት ቢያዩት ለምን እንደጠፋ ወዲያው ይረዳሉ። አጅሬ ለካስ ብረታ በረቱን "ሲያነሳ ሲያስቀምጥ" ከራርሞ ነው ብቅ ያለው! ስለሰላምተኛነቱ፣ ስለትህትናው ለአገር እንዳላወሩለት አሁን በቃ "ጡንቻ በጡንቻ" ሆኖ ሰላም ሊሉት ዓይን ዓይኑን ቢመለከቱት እንዳው የንቀት አይነት በግልምጫ "ብድግ ቁጭ" ቢያደርግዎና እርስዎ ፊቱ እያሉ አልፎ ተራምዶ ከሌላ "ጡንቸኛ" ጋር ሲተቃቀፍ ቢያዩት ቆሽትዎ አይደብንም ወይ?

"የምን ጥጋብ ነው? ባለጌ! የጭቃ ሹሪ!" ብለው በኮሌታው አይዙት ነገር እናቴ ... ካወጣው ጡንቻ ቀንሶ ቢያካፍልዎ እንኳን አትቻቻሉም! በቃ በሆድዎ "የፈሪዎች እርግማን" ረግመውት ይሄዳሉ .... 'እግዚአብሔር የስራውን ይስጠው' ብለው።

እኔ የምለው ግን ... እንዲህ ያለ ፀባይ የሚቀይር "ስፖርት" አያበሳጭም ወይ? (ጡንቸኛ ጡንቸኛው ይሄኔ "ስፖርት አትስራና የእኔን ጡንቻ እያየህ ተበሳጭ!" ይል ይሆናል።)

ሌላ ደግሞ አለላችሁ ... ከ'ሌጣዎች ከበብ' ፀባዩን አሳምሮ ክረምቱን እንዳልወጣ "እግዜር ታርቆት" እንዲት "ትርንጎ" የሆነች ልጅ ቢይዝ ላጤ ባልንጀሮቹን ሁሉ 'እያባረርኩ ካልገደልኩ'የሚል አይነት ነፍጠኛ!! ታዲያ ጓደኛዬ ብለው ተማምነውበት ቁጭ ያሉት ሰውዬ "ትርንጎዬን" ሲልጥ ለወራት ከላጤዎች ሰፈር ጠፍቶ ይሰነብታል። ታዲያ እግር ጥሏችሁ አንድ ቀን መንገድ ላይ ከ"ትርንጎዬ" ጋር አግኝተውት እንደባለስልጣን ቢ!!ባንንብዎ ጉሮሮውን ካልያዝኩ ብለው ሊነሱ ትንሽ ይቀርዎትና አቅማምተው ይተዉታል ... (ጡንቸኛ ነዋ!!)ታዲያኮ የሚያስደስተው ነገር እንዲህ ቆሽትዎ እንዳረረ አይቀሩም።

"ቀብራሬ"ና "ትርንጎዬ" አንድ ቀን በሆነ ነገር ይጨቃጨቁና አጅሬ ፊቱ አባብጦ መንገድ ላይ ቢያዩት እንጀትዎ ቅቤ ይጠጣል ... ለካስ "ትርንጎዬ"ም ጡንቸኛ ኖራለች!!

ሰው እየበላ እየጠጣ የሚጫወትበት ድግስ ቤት ውስጥ ያገኙት "ዝምተኛ፣ ጨዋ፣ ሰው አክባሪ የሚመስል፤ ሌላኛው ተጋባዥ ደግሞ "ፉት" የሚለውን ነገር ቶሎ ቶሎ እየሳበ የማይጣፍጥ፣ የማያልቅ ጨዋታ አጠገብዎ ተቀምጦ ይጀምራል ... የነገር ጨዋታ!! ወዲያው የ"ዝምተኛው" እንግዳ ፀ ባይ ሲቀያየር ያዩታል። ታዲያ ይኼ ከሰላምታ በቀር ቀርበው የማያውቁት እንግዳ ከፊት ለፊትዎ የተቀመጠችውን እንዲት ተጋባዥ በጣቱ እያመለከተዎ በሐ ሜትወሬ ጥፍር አድርጎ ከያዘዎ የሚያመልጡት ... ያው ድግሱ ሲያልቅ ብቻ ነው!

"ያቺ እዛ ጥግ የምትገለፍጠው ወራዳ ትታይሃለች?" ይልዎታል ሌባ ጣቱን ከሆነ ወንድ ጋር ቁጭ ያለች "አበባ" የምትመስል ኮረዳ ላይ ቀስሮ። በይሉኝታ ራስዎን ሲነቀንቁለት ... በቃ ኮረንቲ ሊጨብጥ ይደርሳል!

"ዕድሜ ለእኔ ትበል ሰው አደረግኳት! አገር አስለምጄ፣ አገር አሳይቼ፣ ሥራ አስይዤ ... እያለ በረጅሙ ከዘረዘረው ለልጅቷ ካደረገላት ውለታ ውስጥ የቀረው ነገር ቢኖር "እናትና አባቷን አስተዋውቄ!" ማለት ብቻ መሆኑን ታዝበዋል። ልጅቷ ለካስ አጅሬው ፈረንጅ አገር አስመጥቶ የተጣላት የድሮ ፍቅረኛው ኖራለች! "ተፈንግለህ ነዋ!" አይሉት ነገር በብርጭቆ ይዞ "ፉት" የሚለው ነገር ደግሞ ሊፈነግለው ትንሽ ቀርቶት ያሳዝናል! (ተፈንግሎ አለቀኮ አትሉኝም?)

"ይቺ ድሃ የድሃ ልጅ ..." እያለ አጅሬ ሲሳደብ ልጅቷ ከጓደኛዋ ጋር የደራ ጨዋታ ይዛ ፈገግ ስትል ድንገት ያያታል። ይሄኔ በቃ ብስጭቱ ግንፍል

ይልበትና “ጥርዷ ይርገፍና ... ከነመፈጠሬም እኮ ረሲታኛለች!” እያለ እርስዎ ዳኛ ሆነው ልጅቷን ‘በስቅላት’ ይቀጡለት ይመስል ብሶቱን በሰፊው ያማውትዎታል። ድግሱ አብቅቶ ተገላገልኩት ብለው ሊሰናበቱት ሲከጅሉማ በቃ በአንድ ቀን ድግስ የልብ ጓደኛ ማግኘቱ አስደስቶት “ኸረ ሌላም የማጫውትህ ነገር አለኝ ይቺ መናጢ የሰራችኝን ሥራ እንዲህ በአንድ ቀን አውርቼው የሚያልቅም አይደል!” ይልዎታል ... ጉሮሮው እስኪደርቅ ድረስ ሲያወራልዎ ቆይቶ እኮ ነው! ይቺን ሲሰሙ ነው ድግስ ቤት እርም ሊሉ የሚከጅልዎ!! እንዳው ግን ይቺ መጠጥ እስጨብጣ ገበና የምትገላልጥ ፀባይ አታባሳዊም ወይ?

በእሱ የእናንተም ፀባይ ሳይቀየርብኝ እርዕስት ብቀይርስ? ኸረ ግን ይሄን ራስ የሚመልጥ የበጋ ፀሐ ይ በምን እየተከላከላችሁነው? (በ‘ስስ ቲሸርትና ገበር በሌለው ቁምጣ!’ አትሉኝም?) “ራስ የሚመልጥ ፀሐይ” ስል ደግሞ ይሄ ፀጉሩ “እንትን” ማለት የጀመረ ጉብል ጥርሱን በብስጭት እያፋጨ ‘ከዚህ በላይ ምን እንሁንልህ?’ እንደሚለኝ አውቃለሁ። “በእፍ ይጠፉ ...” እንደሚባለው ለዛሬው ሳልደበደብ ደህና ሰንብቱ ብልስ? (ጡንቸኛ በበዛበት አገር ...)

---


ADVERTISE ON LANDAFTA

# በላንዳፍታ ድርጅቶን ያስተዋውቁ

1/4 page 3.5" x 4.75 "

1/8 page 3.5" x 2.25 "

1/2 page 7.25" x 4.75 "

**ADVERTISMENT ORDER FORM**

Name: ______________________

Address: ______________________

City: ______________________

St. ________ Zip: ____________

Phone: ______________________

Fax: ______________________

**SINGLE ISSUE RATES**

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $200.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $175.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $140.00 |
| ◯ HALF PAGE | $90.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $65.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $50.00 |

**TWO CONSECUTIVE ISSUES RATE**

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $350.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $300.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $250.00 |
| ◯ HALF PAGE | $150.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $110.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $90.00 |

ላንዳፍታ

Please, enclose: 1. A camera ready copy of your Ad.
2. A check for the Amount marked above.

For Information, Please Call Advertisment Department:
Phone: (404)508-4657 Fax: (404)508-2447 - E-Mail: mgessesse@aol.com

Please, Send check or money order payable to LANDAFTA along with your order.
LANDAFTA, P.O.Box 49301, Atlanta GA 30359

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ

| | | |
|---|---|---|
| ለ6 ተከታታይ እትሞች<br>(Six Consecutive Issues) | U.S. | $16.00 |
| | Canada | $22.00 |
| | Europe | $30.00 |
| | Asia | $38.00 |
| | Institutions | $40.00 |

**የሚላክሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ አገልግሎት ነው።**
**በአካባቢዎ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት ይደርስዎታል።**

## የላንዳፍታ መጽሔት የደምበኝነት ቅጽ
## LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ______________ STATE ______ ZIP ______________

PHONE ( ______ ) ______________

<u>ያለፉትን እትሞች</u> ማዘዝ ከፈለጉ ይህንኑ ይጥቀሱ
ክፍያው ከነመላኪያው ለእያንዳንዱ እትም $2.50 ነው።

**ለጓደኛዎ በሽልማት መልክ ለመላክ ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ይሙሉ።**
Please, send my gift subscription to the following person.

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ______________ STATE ______ ZIP ______________

PHONE ( ______ ) ______________

**እባክዎን ክፍያዎን በመኒ ኦርደር ወይም በቸክ በአድራሻችን ይላኩ።**
*Please, send money order or check payable to LANDAFTA.*

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

# አባይ ምግብ ቤት
# Abbay Restaurant



ከእሁድ እስከ ሐሙስ ከ 11:30 a.m. እስከ 11:00 p.m.
ዓርብና ቅዳሜ ከ11:00 a.m. እስከ 12:00 midnight (ራት)
የሙዝናኛ ፕሮግራም እስከ 2:00 a.m.

ለሠርግ፣ ለቀለበት፤ ለክርስትና፤ ለልደትና
ለመሳሰሉት በልዩ ትዕዛዝ እናዘጋጃለን።



የተለያዩ ባህላዊ ምግቦቻችንን ይወዳሉ።
ብቅ ይበሉና እናስተናግድዎት።

በዕረፍት ቀናት ምሽት
የሙዝናኛ ፕሮግራሞች ይኖሩናል።
ደስ ሲላችሁ እኛንም ደስ ይለናል፤
ስለዚህም በመስተንግዶአችን እናስደስትዎታልን።

## AUTHENTIC ETHIOPIAN RESTAURANT

Have a spicy authentic Ethiopian dinner
and stay for the cultural entertainment on weekends.

3375 Buford Highway # 1050
Atlanta, GA
(404) 321-5808



# MRA'G TRAVEL, *Inc.*

## ሚራዥ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*

92 Piedmont Ave. N.E.
Atlanta, GA 30303



ገነት ፈቀደ - ፕሬዚዳንት
*Genet Fekede, President*

**ለዓለም አቀፍና**
**ለአገር ውስጥ ጉዞዎ አለንልዎ!!**

EXCELLENT SERVICE!
SPECIAL FARE!
GROUP FARE!

**የኢትዮጵያ አየር መንገድ**
**ልዩ ወኪል**

CONSOLIDATOR FOR
*ETHIOPIAN AIRLINES*

የኢትዮጵያ አየር መንገድ
**ETHIOPIAN AIRLINES**
*Fly ETHIOPIAN*

አስተማማኝ ጉዞ
በቅናሽ ዋጋ
ወደ
አዲስ አበባ
አስመራ
ጆሀንስ በርግ
ቴላቪቭ
ኢየሩሳሌም
ፍራንክፈርት
ለንደን
ጃማይካ
(ወዘተ)

Please Call:
Atlanta Area:
Phone: (404) 577-4404
(404) 577-4682
(404) 577-4889
Fax: (404) 222-9305

Also Call:
San Fransisco Area
*Aderaw Yeshiwas*
*Selam Fekede*
Phone: (510) 829-0529
Fax: (510) 829-0529

በተጨማሪ የአገር ውስጥ ትኬት በጥሩ ዋጋ ስላለን ይደውሉልን።
*Special Fare For Local Travel*

Certified Agent For:

Airlines Reporting Corporation

International Airlines Travel Agent Network

Official Travel Agency For The Cruise Industry
1996